ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ሐሙስ

83ኛ ዓመት ቁጥር 269 ግንቦት 29 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# ቋሚ ኮሚቴው ፍርድ ቤቶች የሕዝብ አመኔታን ለማግኘት መሥራት እንዳለባቸው አሳሰበ

• በአስር ወራት ለ143 ሺህ 455 መዛግብት እልባት ተሰጠ



**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በዳኝነት አገልግሎት አሰጣጣቸው የሕዝብ አመኔታን ለማትረፍ መሥራት እንዳለባቸው በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሕግና ፍትሕ ቋሚ ጉዳዮች አሳሰበ፡፡ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ለ143 ሺ 455 መዛግብት እልባት መሰጠቱ ተጠቁሟል፡፡

ቋሚ ኮሚቴው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶችን የ10 ወራት የሥራ አፈጻጸም ትናንት ገምግሟል፡፡

በፌዴራል ፍርድ ቤቶቹ የአገልግሎት አሰጣጥ ቅልጥፍና እና ጥራት ለማሻሻል የተጀመሩ ሥራዎች ጥሩ መሆናቸውን የጠቆመው ቋሚ ኮሚቴው፤ የዳኝነት አገልግሎት አሰጣጡ ግን የሕዝብ አመኔታን አግኝቶ የሚፈለገውን እርካታ እንዳላመጣ አመልክቷል፡፡

እየተሰጠ ያለው የዳኝነት አገልግሎት በሕዝብ ተገማች እንዳልሆነ የጠቆመው ቋሚ ኮሚቴው፤ የነበሩትን የዳኝነት አገልግሎት አሰጣጡን ችግሮች

ቋሚ ኮሚቴው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




## ጉባኤው በኢትዮጵያና በሳውዲ አረቢያ መካከል ያለውን ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ያጠናክራል

ገጽ 4



## የጅምላና ችርቻሮ ንግድ ለውጭ ባለሀብቶች መፈቀዱ ተወዳዳሪነትን የሚያሳድግ ነው

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- የጅምላ እና ችርቻሮ ንግድ ሥራ ለውጭ ባለሀብቶች መፈቀዱ የግሉ ዘርፍ ተወዳዳሪ እንዲሆን በማድረግ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ያሳድጋል ሲሉ አቶ ዘመዴነህ ንጋቱ ተናገሩ፡፡

የምጣኔ ባለሙያው አቶ ዘመዴነህ ንጋቱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የጅምላ እና ችርቻሮ ንግድ ሥራ ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት መደረጉ የግሉን ዘርፍ ተወዳዳሪ በማድረግ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ

የጅምላና ችርቻሮ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# አዲስ የሥራ ባህል የፈጠረው አዲስ ልማት

**ሳሙኤል ወንደሰን**

**ዜና ሐተታ**



ጥቁሩ የአስፓልት መንገድ ምቹ ሆኗል፤ የግራና የቀኝ እግረኛ መንገዱ ሁሌም ሂዱብኝ ሂዱብኝ ይላል፡፡ ሕንፃዎቹ ውበትን ተላብሰዋል፡፡ በተለይ የኮሪደር ልማቱ ከአራት ኪሎ ወደ ፒያሳ የሚወስደውን መንገድ ሁለተናዊ ውበትና ምቹነት አላብሶታል፡፡

የመዲናዋ የኮሪደር ልማቱ የከተማዋን ውበት የሚጨምሩ የሕዝብ መናፈሻ ስፍራዎች፣ ፋውንቴኖችና የአረንጓዴ ስፍራዎች እንዲሁም የመንገድ ሥራዎች እየተጠናቀቁ ነው፡፡ የተጠናቀቁም እንዳሉ ተመልክተናል።

ይህንን ፕሮጀክት በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማጠናቀቅ ከመደበኛ የሥራ ሰዓት ውጪ በምሽት ጭምር የግንባታ ሥራው እየተሠራ እንደሆነ የኢፕድ ሪፖርተሮች ተዘዋውረው ተመልክተዋል። ኮሪደር ልማት ሥራው ላይም የብሎኬት፣ የግንብ፣ የጠርዝ ሥራዎችን ሲሠሩ ያገኘቻቸውን አቶ አባይነህ ናናን አነጋግረናል።

የኮሪደር ልማቱ የመዲናዋን የኢኮኖሚ፣ የኢንቨስትመንትና የቱሪዝም እንቅስቃሴን በማሳለጥ ረገድ ትልቅ ትርጉም ያለው ከመሆኑም በላይ የሥራ ባህላችንን ወደ 7 ቀናት /24 ሰዓት የቀየረ ተግባር ነው ይላሉ አቶ አባይነህ ናና።

“በግንበኝነት ሙያ ከ10 ዓመት በላይ ስሠራ ቆይቻለሁ። በዚህም የብሎኬት፣ የግንብና የጠርዝ ሥራዎች ባለሙያ ሆኛለሁ” ያሉት አቶ አባይነህ፤ የአዲስ አበባ የኮሪደር ልማት የሥራ እድል የፈጠረ ብቻ ሳይሆን የሥራ ባሕልና አስተሳሰብን የቀየረ መሆኑን ይናገራሉ።

አዲስ አበባን የሚመጥን የልማት ሥራ ላይ መሳተፋቸው በውስጣቸው ልዩ ስሜት እንዲፈጠር ማድረጉን የገለጹት አቶ አባይነህ፤ በልማቱ የሠሯቸው የመውጫና መውረጃ ደረጃዎች እንዲሁም ሌሎች ሥራዎች ላይ ነዋሪዎች ሲመላለሱና ሥራውን ሲያደንቁ ሲሰሙ ደስታቸው እጥፍ ድርብ እንደሚሆን ተናግረዋል።

ይህንን ሲናገሩም በፈገግታ ጭምር ነው። የስኬት ሁሉ ምስጢር ያለው የሥራ ባሕል እየተለወጠ መምጣቱ ላይ ነው። ይሄንን ለውጥ ማምጣት የሚያስችል የሥራ ባሕል በቤተሰብና በማህበረሰብ ደረጃ ማጎልበት ያስፈልጋል ነው ያሉት።

የመንገድ ዳር የፍሳሽ መስመር ጥገና ባለሙያ

አዲስ የሥራ ባህል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# አፍሪካ ያላትን ከዓለም 30 በመቶ የማዕድን ክምችት ለመጠቀም ጠንካራ ሥራ ይጠይቃል

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- አፍሪካ ያላትን ከዓለም 30 በመቶ የሚሆነውን የማዕድን ክምችቷን አውጥቶ ለመጠቀም ተግባራዊ የሆነ ስትራቴጂ መንደፍና ጠንካራ ሥራ ማከናወን እንደሚገባ የአፍሪካ ማዕድን ልማት ማዕከል አስታወቀ፡፡

ለዓለም ካርቦን ቅነሳ መሠረታዊ የሆኑ ማዕድናትን ጥቅም ላይ ከማዋል አንፃር የአፍሪካ አቅም የሚያድግበት ሁኔታ ላይ የመከረ ጉባኤ በአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽንና በአፍሪካ ማእድን ልማት ማዕከል አማካኝነት ሰሞኑን ተካሂዷል።



ማሪት ያየህይራድ

የአፍሪካ ማዕድን ልማት ማዕከል ጊዜያዊ ዳይሬክተር ማሪት ያየህይራድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አፍሪካ ከዓለም 30 በመቶ የሚሆነውን የማዕድን ክምችት ብትይዝም በአግባቡ አልተጠቀመችበትም።

የአፍሪካ አህጉር በታሪክ ለአንድ መቶ ዓመታት በማዕድን ማውጣት ተሰማርታ እየሠራች ብትቆይም ከገቢ አንጻር የዜጎችን ሕይወት የሚቀይር መሠረታዊ ውጤት አልተገኘም ሲሉ አስረድተዋል።

ከአህጉሪቷ የማዕድን ልማት ጋር ተያይዞ የሚወጡ መመሪያዎች፣ ደንቦች እና ስትራቴጂዎች ከተግባራዊነት አንፃር ክፍተቶች እንዳለባቸው የጠቆሙት ጊዜያዊ ዳይሬክተሯ፤ በማዕድን ልማቱ ውጤታማ ለመሆን ወደተግባር የሚቀየሩ ሕጎች አስፈላጊነታቸው ወሳኝ መሆኑን አውስተዋል።

ተግባራዊ የሆነ ስትራቴጂ በአፍሪካ ሀገራት ከመንደፍ አንጻር ማዕከሉ ትኩረት አድርጎ እየሠራበት ነው ሲሉ ተናግረዋል።

በአፍሪካ የማዕድን ልማት ጋር ተያይዘው የወጡ መመሪያዎች፤ ስትራቴጂዎችና ሕጎች ላይ የዳሰሳ ጥናት መከናወኑን የገለጹት ዳይሬክተሯ፤ የማዕድን ልማትን ምርታማ ዘርፍ አድርጎ ያለመመልከት እንዲሁም የሚገኘው ገቢ ላይ ሕጋዊ ክትትል ያለማድረግ ችግር በበርካታ አካባቢዎች ይስተዋላል ሲሉ አስረድተዋል፡፡

ማዕከሉ በዋናነት ዓላማ አድርጎ የተነሳው የአህጉሪቱን የማዕድን ዘርፍ በማሳደግ ዘላቂ ልማትና አካታች ዕድገትን ለማምጣት ነው፤ በዚህ ረገድ የሚታዩ ችግሮችን ለመቅረፍ የቴክኒክ እገዛ እያደረገ ይገኛል ብለዋል።



በተጨማሪም በዓለም አቀፍ ደረጃ ከካርቦን ነፃ ኢኮኖሚን ለመገንባት በሚሠራው ሥራ ተፈጥሯዊ ሚናቸው የጎላ ነው ተብለው የተለዩ ማዕድናት መኖራቸውን ጠቁመው፤ በአፍሪካ እነዚህ ለአረንጓዴ ልማት ወሳኝ የሆኑ ማዕድናት በስፋት ይገኛሉ ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በተለይም 70 በመቶ የሚሆነውን ኮባልት ክምችት በዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ ፣ ሊቲየም ደግሞ በብዛት በዙምባቡዌ እንዲሁም ማንጋኒዝ ደግሞ በደቡብ አፍሪካ በስፋት እንደሚገኙ አንስተዋል። በተጨማሪም ኢትዮጵያ እነዚህ ማዕድናት ከሚገኙባቸው ሀገራት አንዷ ናት ሲሉ አስረድተዋል፡፡

ወሳኝ የተባሉ ማዕድናትን ለመፈለግ ሰፊ ጥናት እንደሚያስፈልግ በመግለጽ፤ ማዕከሉ ከማዕድን ፍለጋ ጋር ተያይዞ ለሀገራት የተለያዩ ቴክኒካል ድጋፎችን እያደረገ በመሆኑ ሀገራቱም ዕድሉን በአግባቡ ሊጠቀሙበት እንደሚገባ አመላክተዋል።

ማሪት ያየህይራድ እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ ሰፊ የወርቅ፣ የፖታሽ፣ የታንታለም ክምችት አለ። ይሁንና በሚፈለገው ልክ የማዕድናቱ ፍለጋ አልተካሄደም። አሁን ላይ በሀገሪቱ የከበሩ ማእድናት ኢንዱስትሪ እያደገ ቢሆንም ይበልጥ ውጤት ለማግኘት ማዕከሉ ከኢትዮጵያ ጋር በትብብር እየሠራ ይገኛል።



# ለጽዱ ኢትዮጵያ ንቅናቄ የሚደረገው ድጋፍ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- የመዲናዋን የመጸዳጃ ቤት ተደራሽነት ለማስፋት ወሳኝ ድርሻ ለሚኖረው የጽዱ ኢትዮጵያ ንቅናቄ የሚደረጉ ድጋፎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ የአዲስ አበባ ከተማ ጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ጥሪ አቀረበ።

የኤጀንሲው ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሙላት ተገኝ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የጽዱ ኢትዮጵያ ንቅናቄ በአዲስ አበባ ያለውን የመጸዳጃ ቤት ተደራሽነት ለማስፋትና የጤና አጠባበቅ ሥርዓትን ለማሻሻል አይነተኛ መንገድ ነው።

ከደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ጋር ተያይዞ በከተማዋ የሚታዩ ሕገ-ወጥነቶች ከቆሻሻ ማስወገጃዎች ተደራሽነት ጋር የተያያዘ መፍትሔ እንዳላቸው ጠቁመው፤ በየአካባቢው የሚገነቡ ደረጃቸውን የጠበቁ መጸዳጃዎች የአካባቢን ንጽህና ለመጠበቅ የሚረዱ በመሆናቸው ግለሰቦችና ተቋማት የሚያደርጉትን ድጋፍ አጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል ብለዋል፡፡

የመጸዳጃ ቤትና ሌሎች ቆሻሻ ማስወገጃዎች አስፈላጊ እንደመሆናቸው ንቅናቀው መዲናዋን የዲፕሎማቲክ መቀመጫነት የሚመጥን ሥራ በመሆኑ በገንዘብም ሆነ በጉልበት እንዲሁም በሃሳብ መደገፍ ያስፈልጋል ሲሉ ተናግረዋል።

አቶ ሙላት እንደገለጹት፤ የተጀመረው የጽዱ ኢትዮጵያ መርሀ ግብር እንደከተማ ወስደን ስንመለከተው፤ በየመንገዱ ሽንት የሚሸናው፣ ደረቅ ቆሻሻ የሚጣለውን ችግር ለመቀነስ የሚያግዝ በመሆኑ የመዲናዋ ነዋሪና ባለሀብቶች ንቁ እንደከዚህ ቀደሙ ሁሉ ንቁ ተሳትፎ ሊያደርጉ ይገባል።

አቶ ሙላት እንደተናገሩት፤ የከተማዋን ጽዳት ለማስጠበቅ ኤጀንሲው በተለያዩ ጊዜያት የንቅናቄ መርሀ ግብሮች እና ቁጥጥሮችን በማጎልበት ሲሠራ ቆይቷል፡፡

እስካሁን በተሠሩ ሥራዎች መሻሻሎች ቢኖሩም፤ አሁንም በአካባቢ ንጽህና ጉዳይ ገና የሚቀር ሥራ አለ ያሉት አቶ ሙላት፤ የመኪና ተረፈ ምርቶች፤ በየሰፈሩ የጽዳት ሠራተኞች አጽድተው ከቦታቸው ሳይነሱ ሌላ ቆሻሻ የሚጣልበት እና የቆሻሻ አወጋገድን በተመለከተ የሚታዩ ሕገወጥነቶች ሊታረሙ እንደሚገባ መልዕክት አስተላልፈዋል።

በየአካባቢው ደረጃቸውን የጠበቁ መጸዳጃ ቤቶች ተገንብተው በየመንገዱ በመሽናት አካባቢን የሚያቆሽሹትን ግንዛቤ ከማስጨበጥ ባለፈ በሕግ አግባብ እንዲቀጡ ይደረጋል ብለዋል፡፡

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ እንደተናገሩት፤ ሕገ-ወጥ የቆሻሻ አወጋገድን በተመለከተ እንደየጥፋቱ 32 የሚጠጉ ቅጣቶች አሉ፡፡ በዚህ ረገድ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ማስከበር አገልግሎት ጋር በቅንጅት እየተሠራ ነው፡፡

ከግንዛቤና የቁጥጥር ሥራዎች በተጨማሪ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የተጀመሩት የኮሪደር ልማት ሥራዎች ሲጠናቀቁ የከተማውን ጽዳት ለማስጠበቅ መስሪያ ቤቱ የሚሠራውን ሥራ ይደግፋሉ ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ አቶ ሙላት ገለጻ፤ የኮሪደር ልማቱ ሲጠናቀቅ ከጽዳት አንጻር አጠቃላይ ላለው የቱሪዝም ገቢ ዕድገት ሚናው የጎላ እንደሚሆን ይታመናል፡፡

አዲስ አበባ በዓለም ሦስተኛ የዲፕሎማሲ ማዕከል እንደመሆኗ ከተማዋን ምቹ እና ጽዱ ከተማ ለማድረግ ታስቦ በርካታ የልማት ሥራዎች በመፋጠን ላይ መሆናቸውን ጠቁመው፤ ማህበረሰቡ በልማቱ በባለቤትነት እንዲሳተፍና ለከተማዋ ጽዳት የራሱን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# የግሉ ዘርፍ የዲጂታል ኢኮኖሚ ግንባታ ተዋንያን እንዲሆን ይፈልጋል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- መንግሥት የግሉ ዘርፍ የዲጂታል ኢኮኖሚ ግንባታ ዋና ተዋናይ እንዲሆን ይፈልጋል ሲል የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ገለጸ፡፡

አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ዲጅታል ቴክኖሎጂን ተጠቅመው ምርትና አገልግሎታቸውን እንዲያሻሽሉ የሚረዳ ውይይት ትናንት ተካሂዷል፡፡

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዴኤታ ይሽሩን አለማየሁ (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያን በዲጂታል ኢትዮጵያ ስትራቴጂ መሠረት በ2025 ሁለንተናዊ የቴክኖሎጂ ተጠቃሚነቷን ያረጋገጠች ሀገር ለማድረግ እየተሠራ ነው፡፡ በሀገሪቱ እየተከናወነ ያለውን ሀገራዊ የዲጂታል ኢኮኖሚ ግንባታ በመንግሥት አቅም ብቻ እውን ማድረግ ስለማይቻል መንግሥት የግሉ ዘርፍ የዲጂታል ኢኮኖሚ ግንባታ ዋና ተዋናይ እንዲሆን ይፈልጋል ብለዋል፡፡

በ2025 ዓ.ም የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት 200 ሚሊዮን ይደርሳል ተብሎ ይጠበቃል ያሉት ዶክተር ይሽሩን፤ ከሚኖረው የሕዝብ ብዛት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ኢኮኖሚ ለመገንባትና የሥራ እድል ፈጠራን ለማስፋፋት የግሉ ሴክተር ከመንግሥት ጋር በቅንጅት ሊሠሩ ይገባል ብለዋል፡፡

እንደ ዶክተር ይሽሩን ገለጻ፣ በሀገሪቱ እየተከናወነ ያለውን ሀገራዊ የዲጂታል ኢኮኖሚ ግንባታ በመንግሥት አቅም ብቻ እውን ማድረግ አይቻልም፡፡ የግሉን ዘርፍ በሀገራዊ የዲጂታል ኢኮኖሚ ግንባታ የሚያሳትፍ ፖሊሲንና ሥርዓትን የመዘርጋት ሥራዎች መሠራታቸውን አስታውቀዋል፡፡



ይሽሩን አለማየሁ (ዶ/ር)

በወረቀት መልኩ ሲፈጸሙ የነበሩ የመረጃ ልውውጦችን እና የግብይት ሥራዎችን በኤሌክትሮኒክስ መልኩ እንዲሆኑ ረቂቅ አዋጅ አዘጋጅቶ ተግባር ላይ እንድውል መደረጉ ከተሠሩት ሥራዎች መካከል መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የኤሌክትሮኒክስ የመረጃ ልውውጦችና ግብይቶች ሕጋዊ እውቅና አግኝተው ሥራ ላይ እንዲውሉ መደረጉ ለሀገራዊ የዲጂታል ኢኮኖሚ ግንባታው ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከተ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ ከግሉ ዘርፍ ሰፊውን ድርሻ እንደሚይዙ ገልጸው፤ መንግሥት አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን ለማበረታታት እና ዲጅታል ኢኮኖሚውን ለመገንባት እየሠራ ነው ብለዋል፡፡

መንግሥት የግሉ ዘርፍ የዲጂታል ኢኮኖሚ ግንባታ ዋና ተዋናይ እንዲሆን ይፈልጋል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ የዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂ፣ የኤሌክትሮኒክ ትራንዛክሽን አዋጅ፣ የዲጂታል መታወቂያ አዋጅ፣ የግል ዳታ ጥበቃ እና ሌሎችም በዲጂታል ኢኮኖሚ ግንባታ ውስጥ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የተዘጋጁ መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡

ዲጂታል ቴክኖሎጂ ሀገራዊ ኢኮኖሚን ለመገንባት፣ ለሥራ ዕድል ፈጠራና የአገልግሎት አሰጣጥን የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ተረድተን በዘርፉ የሚያጋጥሙትን ችግሮች በቅንጅት ሠርተን በመፍታት ሀገራዊ የኢኮኖሚ ግንባታውን እውን ማድረግ ይጠበቅብናል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የግል ዘርፉ የመረጃ ኮሚኒኬሽን ኩባንያ ማህበር ፕሬዚዳንት ይልቃል አባተ በበኩላቸው፤ አነስተኛና መካከለኛ ኩባንያዎች ዲጂታል ቴክኖሎጂን ተጠቅመው ምርትና አገልግሎታቸውን ማሳደግ እንዲችሉ ከመንግሥትና የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እንሠራለን ብለዋል፡፡

በኢትዮጵያ ከሁለት ነጥብ ሦስት ሚሊዮን በላይ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች እንዳሉ ገልጸው፤ እነዚህን ኢንተርፕራይዞች በዲጅታል ቴክኖሎጂ መደገፍ ከተቻለ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ለማሳደግ እና የሥራ እድል ፈጠራውን ለማስፋፋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል ብለዋል፡፡

የውይይት መድረኩ አነስተኛና መካከለኛ የንግድ ድርጅቶች የዲጂታል ቴክኖሎጂን በመጠቀም ምርታቸውን እንዲያሳድጉ፣ አገልግሎታቸውን እንዲያዘምኑ፣ ፈጠራ እንዲያክሉበት እና የዲጂታል ኢኮኖሚ ግንባታ ላይ የራሳቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ያለመ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

# የኮርፖሬሽኑ ዓመታዊ ገቢ ከ11 ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር በላይ ደረሰ

## - በዘጠኝ ወራት ከአንድ ቢሊዮን ብር በላይ ትርፍ አገኘ

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን ዓመታዊ ገቢውን ከ11 ቢሊዮን ብር በላይ ማድረስ መቻሉን አስታወቀ፡፡ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ከአንድ ቢሊዮን ብር በላይ ትርፍ ማግኘቱም ተገልጿል፡፡

የኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ክፍሌ ወልደማርያም የተቋማቸውን የ2016 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት አፈጻጸም አስመልክተው ትናንት ለመንግሥት ልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ባቀረቡት ሪፖርት፤ ኮርፖሬሽኑ በግብርናው ዘርፍ ለበርካታ ዓመታት በተናጠል አገልግሎት ሲሰጡ የቆዩ ነባር ድርጅቶችን በማዋሃድ በመላ ሀገሪቱ ባሉት 25 ቅርንጫፎችና አራት የኦፕሬሽን ዘርፎች አገልግሎት እየሰጠ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ዓመታዊ ገቢው ከ11ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር በላይ መድረሱን አስታውቀዋል፡፡

ኮርፖሬሽኑ በተቀናጀ የሜካናይዜሽን አገልግሎት ከመሬት ዝግጅት እስከ ጎተራ የሚዘልቁ የግብርና ሥራዎችን እያከናወነ እንዳለ የገለጹት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ ለግብርና መዘመንና ለምርታማነት እድገት የላቀ አስተዋጽኦ ያላቸውን ምርጥ ዘር፣ የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ የአፈር ማዳበሪያዎችን፣ የጸረ ተባይ ኬሚካሎችንና የእንስሳት መድኃኒቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለተጠቃሚዎች በማቅረብ ተልዕኮውን በመወጣት ላይ ይገኛል ብለዋል፡፡

ለግብርና ምርታማነት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ፣ ለዘመናዊ እርሻና አግሮ ኢንዱስትሪ መስፋፋት መሠረት የሆኑ የእርሻ ቴክኖሎጂና ግብዓቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ ሀገራዊ ልማትና እድገትን ለማፋጠን በትኩረት እየሠራ እንዳለም አመላክተዋል፡፡

እንደ ዋና ሥራ አስፈጻሚው ገለጻ፤ በበጀት ዓመቱ አጠቃላይ ከኦፕሬሽን 10 ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር እንዲሁም በዘጠኝ ወራት ወደ ስድስት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር ለማግኘት አቅዷል፡፡ በዘጠኝ ወራት አፈጻጸም ከሰባት ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ ተገኝቷል፡፡ ይህ ከወቅቱ አፈጻጸም ጋር ተያይዞ የስምንት በመቶ ብልጫ ያለው ሆኗል፡፡

ከሽያጭ የተገኘ ገቢን በሚመለከት በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ አንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን ዶላር፣ እንዲሁም በዘጠኝ ወራት 882 ሺህ ዶላር ለማግኘት ታስቦ በዘጠኝ ወራት ብቻ አንድ ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ዶላር ተገኝቷል፡፡ አፈጻጸሙንም ሙሉ በሙሉ አሳክቷል ነው ያሉት፡፡

ከታክስ በፊት ትርፍን በሚመለከት አንድ ነጥብ አንድ ቢሊዮን ታቅዶ፣ በዘጠኝ ወራት ውስጥ መከናወን ከነበረበት 812 ሚሊዮን ውስጥ አንድ ቢሊዮን 28ሚሊዮን ማሳካት ችሏል፡፡ ጠንካራ የአሠራር ሥርዓት መኖሩ ለላቀ አፈጻጸም ገንቢ ሚና እንደነበረውም ተገልጿል፡፡

በአሁኑ ወቅት ዓመታዊ ምርቱም 420 ሺህ ኩንታል መድረሱን ዋና ሥራ አስፈጻሚው አስታውቀዋል፡፡ ምርጥ ዘር ከማምረት ጎን ለጎን የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ከማሳደግ አኳያ በሰብል ምርት በመሰማራት የሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎችና የሰብል አቅርቦትን ለመደገፍ እንቅስቃሴ እየተደረገ እንዳለም ጠቁመዋል፡፡

የግብርና ምርትን በጥራትና በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ፤ በተጨማሪም የማዳበሪያ፣ የአግሮ ኬሚካል፣ የእርሻ መሳሪያ አቅርቦትና የሜካናይዜሽን አገልግሎት በመስጠት እንዲሁም ዓለም አቀፍ የንግድ ትስስር በመፍጠር ዘርፉ ላይ አዎንታዊ ሚና እየተወጣ እንዳለም በሪፖርታቸው ገልጿል፡፡

ኮርፖሬሽኑ የጀመረውን ጠንካራ የአሠራር ሥርዓትን በስፋት በመተግበር ለሀገር ኢኮኖሚ የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ አጠናክሮ እንዲቀጥልም የቋሚ ኮሚቴ አባላት አሳስበዋል፡፡

# የድጋፍ ስምምነቱ በኩላሊት ሕመም ለሚሰቃዩ ታካሚዎች እፎይታን የሚሰጥ ነው

**አማን ረሺድ**



አዲስ አበባ፡- ከሜድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ጋር የተደረገው የኩላሊት ዕጥበት ማሽን ግዢና የመድኃኒት አቅርቦት ስምምነት በኩላሊት ሕመም ለሚሰቃዩ ታካሚዎች እፎይታን የሚሰጥ መሆኑን የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ አስታወቀ፡፡ ግሩፑ የኩላሊት እጥበት ለሚከታተሉ ታካሚዎች የሚውል የ128 ሚሊዮን ብር የድጋፍ ስምምነት ከአዲስ አበባ ጤና ቢሮና ከኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ ድርጅት ጋር በትናትናው ዕለት ተፈራርሚል።

የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ዮሐንስ ጫላ በወቅቱ እንደተናገሩት፤ የተደረገው የድጋፍ ስምምነት በዳግማዊ ምኒልክ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በኩላሊት ሕመም ለሚሰቃዩ ታካሚዎች እፎይታን የሚሰጥ ነው።

የሜድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ከዚህ ቀደም 40 ሚሊዮን ብር በላይ በመመደብ ሆስፒታሉን ለስድስት ወራት ሲደግፍ መቆየቱን ገልጸው፤ የአሁኑ ስምምነት 10 የኩላሊት እጥበት ማሽን ግዢና ለሕክምናው የሚያስፈልገውን የመድኃኒት አቅርቦትን የሚያካትት መሆኑን ጠቁመዋል።

ለከተማ አስተዳደሩ በነጻ እየሰጠ ያለውን የሕክምና አገልግሎት ለማጠናከርና በዘላቂነት ለማስቀጠል የሚያስችል መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የሜድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ የማህበራዊ ኃላፊነትና የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አምባሳደር አሊ ሱለይማን በበኩላቸው፤ ድርጅቱ ለበርካታ ጊዜያት በተለያዩ ዘርፎች የማህበራዊ ኃላፊነቱን እየተወጣ እንደሚገኝ ገልጸው፤ የዛሬው ድጋፍ ለ180 ዜጎች የሚውልና ለሦስት ዓመት የሚቆይ ነው ብለዋል።

እንደ አምባሳደር አሊ ገለጻ፤ ለኩላሊት እጥበት የሚውሉ ግብዓቶች ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቁ መሆናቸው ለዜጎች ሕክምናውን ለማግኘት አስቸጋሪ አድርጎታል፡፡

መኖር እየቻሉ ሕይወታቸው የሚያልፉ ዜጎችን መታደግ እንደሚገባ ጠቁመው፤ በቀጣይም የሜድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ችግር ውስጥ ላሉ የማህበረሰብ ክፍሎች ድጋፍ እንደሚያደርግ ገልጸዋል።

አሁን ላይ በርካታ ዜጎች የኩላሊት ሕመም ተጠቂ መሆናቸውን አውስተው፤ ለነዚህ ዜጎች በጊዜ በመድረስ ችግራቸውን መቅረፍ ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት የመድኃኒት ግዢ አስተዳደር ዘርፍ ምክትል ዳይሬክተር አቶ ሰለሞን ንጉሴ በበኩላቸው፤ ድጋፉ ከጊዜ ወደ ጊዜ በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ የመጣውን የኩላሊት እጥበት አገልግሎትን ምላሽ ለመስጠት እንደሚያስችል ተናግረዋል፡፡

ግዢ የሚፈጸምላቸውን ማሽኖችና ግብዓቶች በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲገዙና አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ በትኩረት እንደሚሠራ አስረድተዋል።

መሰል የበጎ አድራጎት ተግባራት ላይ ሌሎችም ድርጅቶች ሊሳተፉ እንደሚገባ አቶ ሰለሞን አመላክተዋል።

# ለነፍሰ ጡሮችና ለሚያጠቡ እናቶች የአልሚ ምግብ ድጋፍ እየተደረገ ነው

## - በመዲናዋ የአፍሪካ ሕፃናት ቀን ሰኔ 9 ይከበራል

**ሳሙኤል ወንደሰን**




አዲስ አበባ፡- ከ10 ሺህ 800 በላይ ለሚሆኑ ነፍሰ ጡሮችና የሚያጠቡ እናቶች የአልሚ ምግብ ድጋፍ እየተደረገ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሴቶች ሕፃናት እና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ አስታወቀ። በመዲናዋ የአፍሪካ ሕፃናት ቀን ሰኔ 9 እንደሚከበርም ገልጿል።

የቢሮው ምክትል ቢሮ ኃላፊ እመቤት ተስፋዬ በሰጡት መግለጫ እንደተናገሩት፤በመዲናዋ ለነፍሰጡሮች፣ ለሚያጠቡ እናቶችና እስከ ሦስት ዓመት ለሚሆናቸው ሕፃናትን የሚያሳድጉ ቤተሰቦችን ማዕከል ያደረገ የቀዳማይ ልጅነት ፕሮግራም ተግባራዊ እየተደረገ ነው።

ፕሮግራሙ ልጆቻቸውን የተመጣጠነ ምግብ መመገብ የማይችሉ ቤተሰቦች በቀጥታ የሚደገፉበት ነው ያሉት ምክትል ቢሮ ኃላፊዋ፤ አሁን ላይ ከ10 ሺህ 800 በላይ የሚሆኑ ነፍሰ ጡሮችና የሚያጠቡ እናቶች የአልሚ ምግብ ድጋፍ እየተደረገላቸው ይገኛል ብለዋል።

ልጆቻቸውን በሕፃናት ማቆያ ከፍለው ማቆየት የማይችሉ ቤተሰቦችን ፕሮግራሙ ተጠቃሚ የሚያደርግ መሆኑንና ወጪው ሙሉ በሙሉ በመንግሥት እንደሚሸፈንም ጠቁመው፤ ፕሮግራሙ የሕፃናትን ቤተሰቦች ተጠቃሚ የሚያደርግ፣ ወላጆች ልጆቻቸውን ለማኖር ብቻ ሳይሆን ተወዳዳሪ ዜጋ እንዲሆኑ የሚያስችል መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ቢሮው በየበጀት ዓመቱ ሁለት ጊዜ የሕፃናት ሁለንተናዊ ተሳትፎ፣ ቤተሰባዊና ማኅበረሰባዊ ጥበቃ እና መብት ደኅንነታቸውን ከማስከበር አኳያ ሁለት ጊዜ ደማቅ ፌስቲቫሎችን ያካሂዳል ያሉት እመቤት፤ ኅዳር 11 ዓለም አቀፍ የሕፃናት ቀን እና ሰኔ 9 የአፍሪካ ሕፃናት ቀን እንደሚከበር ጠቁመዋል።

በያዝነውም ዓመት የአፍሪካ የሕፃናት ቀንን በአፍሪካ ለ34ኛ እንደ ሀገር ለ33ኛ ጊዜ "የሕፃናትን ትምህርት፣ ተሳትፎ እና ጥራት ለማሳደግ ጊዜው አሁን ነው" በሚል መሪ ቃል በመዲናዋ እንደሚከበር ተናግረዋል።

በቢሮው የሕፃናት መብት ደህንነት ማስጠበቅ ዳይሬክተር አቶ አንዷለም ታፈሰ በበኩላቸው፤ ሕፃናት በየትኛውም ረገድ ቢሆን መብት ደኅንነታቸው ተጠብቆ፣ ምቹ አካባቢ ተፈጥሮላቸው፣ በዕውቀትና በሥነምግባር የታነጹ እንዲሆኑ እና ለነገ ጥሩ ተወዳዳሪ ሆነው እንዲወጡ ለማስቻል ዛሬ ብዙ ልንሠራ ይገባል ብለዋል።

ሕፃናት የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በትክክለኛው ዕድሜ መጀመራቸውን ማረጋገጥ እና መሰል የመብት ማስጠበቅ ተግባራትን እያከናወንን እንገኛለን ያሉት አቶ አንዷለም፤ የሕፃናት የጉልበት ብዝበዛ ምጣኔን፣ ያለዕድሜ ጋብቻ ምጣኔን፣ ከሕፃናት ጥቃት እና ሌሎች መሰል ሥራዎችን በ119 ወረዳዎች መረጃ በመሰብሰብ የዳሰሳ ጥናት መሥራት ተችሏል ብለዋል።

ቢሮው በከተማዋ ለሚገኙ ሕፃናት መብታቸውን ከማስጠበቅ እና ደኅንነታቸውን ከማረጋገጥ አንጻር በርካታ ሥራዎች እየተተገበሩ ይገኛሉ ያሉት አቶ አንዷለም፤ 477 ሺህ 220 ሕፃናት በጤና እንዲኖሩ አስፈላጊ ክትባቶችን ስለመከተባቸው ክትትል መደረጉን ተናግረዋል።

# ጉባኤው በኢትዮጵያና በሳውዲ አረቢያ መካከል ያለውን ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ያጠናክራል

ሞገስ ጸጋዬ



አዲስ አበባ፡- የኢትዮ ሳውዲ የኢንቨስትመንትና ንግድ ጉባኤ በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለውን ኢኮኖሚያዊና ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ለማጠናከር እንደሚረዳ የፕላንና ልማት ሚኒስትር ዶክተር ፍፁም አሰፋ አስታወቁ፡፡

79 አባላት ያሉት የሳዑዲ አረቢያ የኢንቨስትመንትና የንግድ ልዑካን ቡድን በአዲስ አበባ የኢትዮ-ሳዑዲ የኢንቨስትመንትና የንግድ ጉባዔ ትናንት ተካሂዷል፡፡

በጉባኤው ወቅት ንግግር ደረጉት የፕላንና ልማት ሚኒስትር ዶክተር ፍፁም አሰፋ እንደተናገሩት፣ ጉባኤው በኢትዮጵያና በሳውዲ አረቢያ መካከል ያለውን ኢኮኖሚያዊና የሁለትዮሽ ግንኙነት ለማጠናከር ይረዳል፡፡ በርካታ የሳውዲ ባለሀብቶች በኢትዮጵያ በተለያዩ የኢንቨስትመንት መስኮች በመሰማራት ለበርካታ ዜጎች ጊዜያዊና ቋሚ የሥራ እድል ፈጥረዋል፡፡ ጉባኤው የሁለቱን ሀገሮች የቆየውን የሁለትዮሽ ግንኙነት ወደ አዲስ ምዕራፍ ለማሸጋገር ወሳኝ ነው፡፡

ሁለቱ ሀገራት ታሪካዊ ግንኙነት እንዳላቸው የገለጹት ሚኒስትሯ፤ ወደፊት በሁሉም ዘርፍ የበለጠ ትብብር እንዲኖር የኢትዮጵያ መንግሥት ቁርጠኛ ነው። ኢትዮጵያ ባለፉት አምስት ዓመታት ሀገር በቀልናሌሎች የኢኮኖሚ ማሻሻያዎችን በማድረግ ለአልሚዎች ምቹ ሁኔታን ስለመፍጠሯ ገልጸዋል፡፡

በቂ የኤሌክትሪክ ኃይል መኖሩ፣ መሥራት የሚችል በርካታ የሰው ኃይል መኖሩና ኢትዮጵያ ወደ አፍሪካ እንደ መግቢያ በር የምታገለግል መሆኗ ኢትዮጵያ በውጭ አልሚዎች እየተመረጠች መምጣቷን ገልጸዋል፡፡

እንደ ሚኒስትሯ ገለጻ፤ ሳዑዲ አረቢያ ለኢትዮጵያ ምርቶች መዳረሻ ሀገር ናት፡፡ ከእነዚህ ምርቶች መካከልም አበባ፣ የስጋና የቡና ምርቶች በዋናነት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ወደፊትም የተለያዩ ምርቶችን ወደ ሳውዲ በመላክ ጠንካራ የንግድና ኢንቨስትመንት ትስስር ይኖራል፡፡

ኢትዮጵያ በአፍሪካ በፍጥነት በማደግ ላይ ካሉ ሀገራት በግንባር ቀደምትነት ተጠቃሽ መሆኗንም ጠቁመው፤ ጉባኤው በሁለቱ ሀገራት መካከል ትርጉም ያለው ውይይት በማድረግ የጋራ ፍላጎቶችን ለመለየት ያስችላል ብለዋል፡፡

ሚኒስትሯ እንዳሉት፤ ጉባኤው ባለሀብቶችም መሰማራት በሚፈልጉባቸው ዘርፎች በቂ መረጃ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ በኢትዮጵያና በሳውዲ መካከል ጠንካራና የቆየ የሕዝብ ለሕዝብ ትስስር በመኖሩ የሁለቱ ሀገራት ግንኙነት ዘርፈ ብዙ ነው፡፡ ይህም በንግድና ኢንቨስትመንት ዘርፍ ውጤታማ ግንኙነት ለመመስረት ያግዛል፡፡

የሳዑዲ አረቢያ የንግድ ምክር ቤት ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ሁሴን ሙጂብ በበኩላቸው፤ ልዑካን ቡድኑ በኢንቨስትመንትና በንግድ የሁለቱን ሀገራት ግንኙነት ለማጠናከር በማሰብ ወደ ኢትዮጵያ መምጣቱን ገልጸው፤ የኢትዮጵያና የሳዑዲ አረቢያ የንግድ ግንኙነት ረጅም ጊዜ ያስቆጠረና የሁለቱ ሀገራት የጋራ ጥቅም ያስጠበቀ ነው፡፡ ወደፊት ግንኙነቱን ለማጠናከር ዝግጁ መሆናቸውን ተናግረዋል።

የሳዑዲ አረቢያ ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን ግንኙነት ለማጠናከር ቁርጠኛ ናት ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ጉባኤው የኢንቨስትመንት አማራጮችን ለማስፋትና በኢትዮጵያ ያለውን የኢንቨስትመንት እድል ለመጠቀም ይረዳል ነው ያሉት፡፡

በርካታ የሳውዲ ባለሀብቶች በኢትዮጵያ እያለሙ ነው፤ በቀጣይም የአልሚዎች ቁጥር እንዲጨምር ለማድረግ በርካታ ሥራዎች እየተሠራ ነው፡፡ ኢንቨስትመንትንና ንግድን በማጠናከር የሁለቱን ሀገራት ሁለንተናዊ ግንኙነት ቀጣይነት ለማረጋገጥ መሥራት እንደሚያስፈልግ በመግለጽ፤ የሳውዲ መንግሥት ዝግጁ ነው ብለዋል፡፡

የሳውዲ ንግድ ምክር ቤት ከኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ጋር የመግባቢያ ስምምነት የተፈራረመ ሲሆን፤ ይህም የሁለቱን ሀገራት የንግድ ግንኙነት ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር ትልቅ ምዕራፍ ነው ተብሏል።

ስምምነቱን የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የቦርድ አባል ዶክተር አይናለም አባይነህና የሳዑዲ አረቢያ የንግድ ምክር ቤት ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ሁሴን ሙጂብ ፈርመውታል።

## ቋሚ ኮሚቴው...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በአንድ ጊዜ መቅረፍ ባይቻልም የሚሰጡ ውሳኔዎች ማህበረሰቡ የሚረካበት እንዲሆን በትኩረት መሥራት እንዳለበት አሳስቧል፡፡

የዳኝነት አገልግሎት አሰጣጡን ለማዘመን የሚሠሩ የምዘና ሥራዎች እንዲሁም ፍርድ ቤቶችን በቴክኖሎጂ ለማዘመን እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች መቀጠል እንዳለባቸውም ተጠቁሟል፡፡ የተጀመሩ ሥራዎችን ለማስቀጠል እና ተጨባጭ ለውጥ ለማምጣት ከፍተኛ አመራሮች በቁርጠኝነት መሥራት እንዳለባቸውም ቋሚ ኮሜቴው አመላክቷል፡፡

ከሌሎች የፍትህ አካላት ጋር ያላቸው ግንኙነት ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለባቸው በሰጠው አስተያየት የጠቆመው ቋሚ ኮሚቴው፤ ለክልል ፍርድ ቤቶች የሚያደርጉትን ድጋፍም አጠናክረው መቀጠል አለባቸው ብሏል፡፡

በሦስቱም የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ከፍተኛ የሠራተኛ ፍልሰት መኖሩ የተጠቆመ ሲሆን፤ ፍርድ ቤቶቹ የሕፃናት ማቆያ ማመቻቸት እንዲሁም ለሠራተኛው ለሥራ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር የሠራተኛውን ፍልሰት መቀነስ አለባቸው ተብሏል፡፡

ግልጽ ችሎቶች የሚካሄዱባቸውን ቦታዎች ቁጥር መጨመሩ የሚደነቅ ነው ያሉት የቋሚ የሕግና ፍትሕ ቋሚ ጉዳዮች ሰብሳቢ ወይዘሮ እጸገነት መንግስቱ፤ አሁንም ግልጽ ችሎቶች የሚደረግባቸው ቦታዎች እያሉ ቢሮ ውስጥ ዳኝነት የሚሰጡ ዳኞች በመኖራቸው ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል ብለዋል፡፡

የፌዴራል ፍርድ ቤት እግድ ሲሰጥ በስም መመሳሰል ንጹሐን ዜጎች እንግልት እየደረሰባቸው በመሆኑ ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት ገልጸዋል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ቴዎድሮስ ምህረት በምክር ቤቱ በመገኘት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶችን የ10 ወራት የሥራ አፈጻጸም ባቀረቡበት ወቅት እንደገለጹት፤ በተያዘው በጀት ዓመት በፌዴራል ፍርድ ቤቶች በአስር ወራት ውስጥ እልባት ለመስጠት ከታቀደው 126ሺህ 767 መዛግብት ለ143 ሺህ 455 መዛግብት እልባት በመስጠት 133 በመቶ አፈጻጸም ተመዝግቧል፡፡

በሁሉም ደረጃ ባሉ ፍርድ ቤቶች የዳኞች የጋራ ፎረም ተቋቁሞ በሚለዩ ጉዳዮች ላይ ዳኞች ምክክር እንዲያደርጉ መደረጉን የገለጹት ፕሬዚዳንቱ፤ ለስልጠና መነሻ የሚሆኑ ግብዓቶች መገኘታቸውን ተናግረዋል፡፡

ግልጽ ችሎት የሚካሄድባቸው ቦታዎች 5 ብቻ እንደነበሩ አስታውሰው፤ አሁን ላይ ከ12 እስከ 13 በማድረስ በተቻለ መጠን ችሎቶች በግልጽ እየተደረጉ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በአንድ ሺህ 500 መዛግብት የቀረቡ አቤቱታዎች በቪዲዮ ኮንፍረንስ ለማከራከር ታቅዶ አንድ ሺህ 222 ተገልጋዮችን ተደራሽ ያደረገ አንድ ሺህ 555 የቪዲዮ ኮንፍረንስ አገልግሎት መሰጠቱን ገልጸው፤ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ ችሎት 2ሺህ 175 የቪዲዮ ኮንፍረንስ ማካሄድ መቻሉን ተናግረዋል ፡፡

በሦስቱም ፍርድ ቤቶች የሠራተኛ ፍልሰት መኖሩን ተናግረው፤ ፍልሰቱን ለማስቀረት የሠራተኛ ደመወዝና ጥቅማጥቅም ማሻሻያ እየተዘጋጀ መሆኑንና ይህም ሲጠናቀቅ ለምክር ቤቱ እንደሚላክ ተናግረዋል፡፡

ለዳኞች የተለያዩ ክፍተቶች ላይ ስልጠና መሰጠቱን ገልጸው፤ የመዝገብ ቁጥርና የዳኞችን ቁጥር ለማመጣጠን እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

ከቋሚ ኮሚቴው ለቀረቡት ጥያቄዎች የፌዴራል ፍርድ ቤቶቹ አመራሮች ምላሽ እና ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

## የጅምላና ችርቻሮ ንግድ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ያሳድጋል፤ የዋጋ ግሽበት ችግርን ለመፍታትም የራሱ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ታሪክ ከአምስት አስርት ዓመታት በኋላ የውጭ ባለሀብቶች በሀገር ውስጥ የጅምላ እና የችርቻሮ ንግድ ላይ እንዲሰማሩ መንግሥት መፍቀዱን አውስተው፤ ይህም የግሉን ዘርፍ በሀገር ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪነቱን በማሳደግ የሀገር ኢኮኖሚ ዕድገት ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል ብለዋል፡፡

ለኢትዮጵያ ዜጎች ብቻ ተከልሎ የነበረውን የጅምላ እና የችርቻሮ ንግድ ሥራን መንግሥት ለውጭ ዜጎች መፍቀዱ የሀገር ውስጥ ንግድ እንዲያድግ፤ የምርት ጥራትና ተወዳዳሪነት እንዲኖር ያደርጋል ያሉት ባለሙያው፤ የተወሰኑ አስመጪ፣ ላኪና አከፋፋዮች መቶ በመቶ ትርፍ ካላገኘን በሚል የሚያደርሱትን የዋጋ ግሽበት ለመቅረፍም ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ሀገሪቱ በጅምላ እና በችርቻሮ ንግድ ሥራ ላይ የውጭ ባለሀብቶች እንዲሠሩ መፈቀዱ ለኢኮኖሚ እድገቷም ትልቅ አስተዋጽኦ አለው ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ በአጠቃላይ ሀገራዊ ምርት (ጂዲፒ) ከአፍሪካ አምስተኛ ከሳራ በታች ካሉት የአፍሪካ ሀገራት ሦስተኛ ናት፤ ጂዲፒዋን የበለጠ ለማሳደግ ያላት የሰው ሀብት ላይ ኢንቨስት የማድረግ ሥራ መሥራት አለባት ያሉት ባለሙያው፤ ኢንዱስትሪውን ለማስፋፋትና ምርታማነቱን ለማሳደግ የጀመረችውን አበረታች ሥራም አጠናክራ ማስቀጠል እንደሚኖርባት ተናግረዋል፡፡

ከዛሬ ሦስት አራት ዓመት በፊት ከ75 እስከ 80 በመቶ የሚሆነው የባንክ ፋይናንስ ለመንግሥትና ለመንግሥት ልማት ድርጅቶች እንዲውል ይደረግ እንደነበር አስታውሰው፤ በአሁኑ ጊዜ ከ80 በመቶ በላይ ለግል ዘርፉ እንዲውል የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው፤ ይህም የግሉ ዘርፍ የተሰጠውን ትኩረት የሚያሳይ ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

በንግድ ዘርፉ ላይ የውጭ ዜጎች እንዲሳተፉ መደረጉ የኢትዮጵያ የግሉ ዘርፍ ወደደም ጠላም ተወዳዳሪ እንዲሆን ያስገድደዋል፤ ተገዶ ተወዳዳሪ መሆኑም ለሀገር ኢኮኖሚያዊ እድገት ትልቅ ጥቅም አለው ሲሉ ገልጸዋል

የኢትዮጵያ የግሉ ዘርፍ ታዳጊ በመሆኑ ብዙ ድጋፍ ይጠይቃል፤ መንግሥትም አስፈላጊውን ድጋፍ እያደረገ ነው፤ ዘርፉ የሚደረግለትን ድጋፍ ግምት ውስጥ በማስገባት ከውጭ ዜጎች ጋር ተወዳዳሪ ሆኖ መሥራት ይጠበቅበታል ብለዋል፡፡

የጅምላና የችርቻሮ ንግድ ሥራ ለሀገር ውስጥ የተወሰኑ ነጋዴዎች ብቻ ክፍት ሆኖ መቆየት የዋጋ ግሽበት እንዲከሰት ምክንያት ሆኗል ያሉት አቶ ዘመዴነህ፤ ዘርፉ ለውጭ ዜጎች ክፍት መደረጉ ችግሩን ለመፍታት መፍትሔ ይሆናል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የውጭ ዜጎች በተፈቀደላቸው የንግድ ሥራ ለመሰማራት ሲመጡ የሚገጥሟቸውን ተግዳሮቶች ከግምት ያስገቡ መሆን እንዳለባቸውም ጠቁመዋል፡፡

## አዲስ የሥራ ባህል...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አቶ አቡ ደረጃው በበኩላቸው፤ የኮሪደር ልማቱ በምሽት የመሥራት ባህል እየጎለበተ እንዲሄድ እና ግንባታዎች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብና በጀት እንዲሁም በጥራት እንዲጠናቀቁ እድል መፍጠሩን ተናግረው፤ እንዲህ ያለው ጥረት ለጠንካራ የሥራ ባህል መሠረት የሚጥል መሆኑን ይናገራሉ።

በኮሪደር ልማቱ የቆሸሹ ቦታዎች ጽዱ እንዲሆኑ እያደረግን ነው። በዚህም አዲስ አበባን ውብ እያደረግናት ነው ያሉት አቶ አቡ፤ በሦስት ወራት የሚጠናቀቁ ሥራዎችን በኮሪደር ልማቱ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ እየተጠናቀቁ ይገኛሉ ብለዋል።

የኅብረተሰቡን የመሠረተ ልማት ጥያቄ እየተመለሱ ባሉበት ወቅት ቀጥተኛ ተሣታፊ በመሆናቸው መደሰታቸውን የተናገሩት አቶ አቡ፤ በመንገድ ዳር የፍሳሽ መስመር ጥገና ባለሙያነት ከስምንት ዓመት በላይ አገልግለዋል። በስምንት ዓመታት ውስጥም የነበራቸውን ሙያ እያሻሻሉ መምጣታቸውን ነው የገለጹት።

በኮሪደር ልማቱ የሚሠሩት ሥራ ከቀድሞው አሠራር በጥራትና በሥራ ባህል የተለየ መሆኑን ተናግረው፤ ሥራው ሳምንቱን በሙሉ ጠዋትና ማታ የሚሠራ በመሆኑ በሠራተኞች ዘንድ አዲስ የሥራ ባህል እንዲኖር አስችሏል ብለዋል።

የልማቱ ተጠቃሚ ማህበረሰብም በአካባቢው የተሠራውን ማንኛውንም ልማት በተገቢው መንገድ በመንከባከብ መጠቀም እንዳለበት መልዕክት አስተላልፈዋል።

በምሽት ሥራውን መሥራታቸው ፕሮጀክቱን በአጠረ ጊዜ እንዲጠናቀቅ እንደሚያደርግ እና ተጨማሪ ገቢ ማግኘት እንዲችሉ ማድረጉን የተናገሩት ደግሞ አናጺ አቶ ወንዳለ ሙላዴ ናቸው። በተፈጠረላቸው የሥራ ዕድል በሚያገኙት ገቢ ቤተሰቦቻቸውንና ራሳቸውን እያስተዳደሩ መሆኑን ገልጸዋል።

በኮሊደር ልማቱ የ24 ሰዓት ሥራ ነው የምንሠራው። በኮንስትራክሽን ዘርፉ ይሠሩ የነበሩ ሥራዎች የተጓተቱ እንደነበሩ አንስተው፤ ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ በአናጺነት ሙያ ላይ ተሰማርተው እንደቆዩ እና አሁን ላይ ሥራዎችን በፍጥነት የማከናወን ባህል በዘርፉ ላይ እየተስተዋለ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

“የኮሊደር ልማቱ ሁለ ገብ ሙያተኛ እንድሆን አድርጎኛል። ይህም ከአናጺነት ባሻገር የግንበኛና የለሳኝ ሙያ እንዲኖረኝ አድርጎኛል” ያሉት አቶ ወንዳለ፤ በልማቱ የምንሠራው ሥራና የሚከፈለን ደመወዝ አይመጣጠንም። የሚመለከተው አካል ይህንን ጉዳይ ሊመለከተው ይገባል ብለዋል።

ከመደበኛ የሥራ ሰዓት ውጪ የመሥራት ባህል በኢትዮጵያ ብዙም ያልተለመደ መሆኑን ጠቅሰው፤ በሌሎች የሥራ ዘርፎች የተሰማሩ ዜጎች ቀንና ሌሊት በመሥራት የሥራ ባህል ለውጥ በማድረግ ለሀገራቸው ዕድገት መሥራት እንዳለባቸው መልዕክት አስተላልፈዋል።

ይህን ባህልና እሴት ለማስቀጠል የአሁኑ ትውልድ ያገኘውን ዘመናዊ ትምህርትና ክህሎት በመጠቀም የሥራ ባህሉን ማጠናከር እንዳለበትም ተናግረዋል።

ከንቲባ አዳነች አቤቤ በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ላይ ባስተላለፉት መልዕክት እንዳሉት ፤በኮሪደር ልማት ሥራው ከ48 ኪሎ ሜትር በላይ የተሽከርካሪ የመንገድ ልማት፣ 4 የመሬት ውስጥ የእግረኛ መንገዶች፣ 96 ኪሎ ሜትር ሰፋፊ የእግረኛና 100 ኪሎ ሜትር የብስክሌት መንገዶች፣ 5 ኪሎ ሜትር የመሮጫ ትራክ ያካተተ ነው፡፡

እንዲሁም 48 የትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጡን የሚያሳልጡ የአውቶቡስ እና የታክሲ ተርሚናሎችንና መጫኛ ማውረጃ ስፍራዎች፣ በጥቅሉ ከ240 ኪሎ ሜትር በላይ የሚሆን የመንገድ እና ተያያዥ መሠረተ ልማት፤ 70 የከተማን ውበት የሚጨምሩ የሕዝብ መናፈሻ ስፍራዎች፣ ፋውንቴኖችና የአረንጓዴ ስፍራዎች፣ የመዝናኛና የመናፈሻ ስፍራዎች፣ የልጆች መጫወቻና የሕዝብ ፕላዛዎች፣ 120 የሚሆኑ የመጸዳጃ ቤቶች እንደሚያካትትም ጠቅሰዋል።

ይህም አዲስ አበባን እንደ ስሟ ውብ፣ ለነዋሪዎቿ ምቹ ከማድረጉም ባሻገር ለበርካታ ዜጎች የሥራ ዕድል የፈጠረና የሙያ ባለቤት እያደረገ መሆኑን ባለሙያዎቹ ምስክርነት ሰጥተዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## በፕሮጀክቱ አፈጻጸም የሚታየው ሁለንተናዊ መነቃቃት የመበልጸግ ተስፋችን ማሳያ ነው !

አዲስ አበባን ለነዋሪዎቿዋ የተመቸች ፤ ለዘመናዊ አኗኗር የተሻለች ፤ ለኢትዮጵያ ከዚያም ባለፈ ለአፍሪካ የኩራት ምንጭ የምትሆንበትን እድል ለመፍጠር የተጀመረው ከተማዋን የማደስ የኮሪደር ልማት ፕሮጀክት በተያዘለት ጊዜ ለማጠናቀቅ ሌት ተቀን እየተሠራ ይገኛል። በእያንዳንዱ ቀን የሚታየው ለውጥም በርግጥም አዲስ አበባ ሥሟን በሚመጥን ደረጃ እየታደሰች ፤ እየተዋበች ስለመሆኑ በተጨባጭ አመላካች ነው።

ከተቆረቆረች ከ120 ዓመታት በላይ ያስቆጠረችው አዲስ አበባ፤ ገና ከጠዋቱ ጀምሮ ባጋጠሟት የተለያዩ ፈተናዎች የዕድሜዋን ያህል ልታድግ ፤ለነዋሪዎችዋ ፍላጎት የተመቸች ልትሆን አልቻለችም ። የሀገሪቱ ርዕሰ ከተማ፤ የአፍሪካውያን መዲና ከመሆኗ አኳያም የነበረችበት የከተሜነት ደረጃ የሚመጥናት ሳይሆን ብዙ ዓመታትን አስቆጥራለች።

ከተማዋ ልታመነጭ የምትችለውን ሀብት በአግባቡ መሰብሰብ እና ለከተማዋ ልማት ማዋል አለመቻል፤ለከተማዋ እድገት ሁለንተናዊ በሆነ መንገድ ትኩረት ሰጥቶ አለመሥራት ፤ የአመራር እና የአመራር ቁርጠኝነት ክፍተት ... ወዘተ ለከተማዋ አሁናዊ ኋላ ቀር ገጽታ በዋነኛነት የሚጠቀሱ ናቸው።

በከተማዋ ዘመናዊ ሕይወትን ለመምራት የሚያስችሉ የተሟሉ የመሠረተ ልማት ግንባታዎች አለመኖር ፤ በነዋሪዎቿ ላይ ዘመናዊ የከተሜነት ስነልቦና መፍጠር አለመቻል ፤ ዘመኑን የሚዋጅ የከተማ አስተዳደር አለመገንባት ከሁሉም በላይ ከተማዋን በባለቤትነት መንፈስ የሚመራ የፖለቲካ አመራር ክፍተት ከተማዋ የዕድሜዋን ያህል እንዳታድግ አድርጓት ቆይቷል ።

በየወቅቱ የሚደረጉ የከተማዋን የማልማት ሥራዎችም ቢሆኑ መጪ ጊዜያትን ታሳቢ ያደረጉ ፤ ከተማዋ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚጠቀሱ የዲፕሎማሲ ከተማዎች አንዷ መሆኗን ከግምት ውስጥ ያስገቡ ፤እንዲሁም የከተማዋን እና የነዋሪዎቿን ፍላጎቶች ታሳቢ ያደረጉ አለመሆናቸው ፤ ለከተማዋ አሁናዊ ዘርፈ ብዙ ችግሮች ተጠቃሽ ተደርገው የሚወሰዱ ናቸው።

በከተማ በዝቅተኛ ደረጃ የሚሰበሰበው ሀብትም ቢሆን አግባብ ባለው መንገድ ለልማት የሚውልበት ጠንካራ የአሠራር ሥርዓት አለመኖሩ ፤ የከተማዋ ሀብት በአንድም ይሁን በሌላ ለተበላሸ አሠራር እና ለብክነት የተዳረገ መሆኑ ለከተማዋ ዕድገት ማነቆ ሆነው ቆይተዋል።

እነዚህን የተጠራቀሙ የከተማዋን ችግሮች በመፍታት፤ከተማዋ በአዲስ የለውጥ እና የልማት ጎዳና ውስጥ መኳዝ እንድትጀምር የለውጥ ኃይሉ ወደ ስልጣን ከመጣ ማግስት ጀምር ግዙፍ የቤት ሥራዎችን ወስዶ እየሠራ ይገኛል። በዚህም እየተመዘገበ ያለው ውጤት ተስፋ ሰጪ እየሆነ ነው።

በአንድ በኩል ከተማዋ ልታመነጭ የምትችለውን ሀብት በአግባቡ ለመሰብሰብ ሰፊ ጥረቶችን እያደረገ ይገኛል፤ ለዚህም የከተማዋን ገቢ የማመንጨት አቅም የሚያጎለብቱ በዓለም አቀፍ ተሞክሮዎች የተደገፉ ሥራዎች እየተሠሩ ነው። በዚህም የከተማዋ ገቢ በየዓመቱ ከፍ ባለ ደረጃ እያደገ ይገኛል።

ከዚህ ጎን ለጎን ከከተማ የሚሰበሰበውን ሀብት ለከተማዋ ዕድገት ለማዋል የሚያስችሉ የተለያዩ ፕሮጀክቶች በከተማዋ አስተዳደር እና በፌዴራል መንግሥት በኩል በቅንጅት እየተካሄዱ ነው። ከነዚህም አሁን ላይ በዋነኛነት የሚጠቀሰው ከተማዋን የማደስ እና የኮሪደር ልማት ፕሮጀክት ተጠቃሽ ነው ።

ከተጀመረ ጥቂት ወራት ያስቆጠረው ይህ ፕሮጀክት ከተጀመረ ማግስት ጀምሮ ከፍተኛ በሆነ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ውስጥ ቢያልፍም "እውነት እና ጉም እያደር ይጠራል" እንደሚባለው፤አሁን ላይ የብዙ ውሸታሞችን አፍ ያዘጋ ፤ ብዙዎችን በአግራሞት እጃቸውን በአፋቸው ያስጫነ ፤ የሚታይ እና የሚጨበጥ ፍሬ እያፈራ ይገኛል። በአጠቃላይ የብዙዎችንም ቀልብ ስቦ ትልቅ ሀገራዊ የልማት አጀንዳ ሆኗል።

ፕሮጀክቱ እየተመራበት ያለው መንገድ ፤በርግጥም ሀገሪቱ ለልማት ቁርጠኛ አመራር ካገኘች፤በለውጡ ዋዜማ እንደ ሀገር ተስፋ ያደረግነው በልማት የመበልጸግ ተስፋችን ከተስፋ በላይ ሊጨበጥ የሚችል እውነት ስለመሆኑ አመላካች ነው። ድህነትን ታሪክ ለማድረግ የጀመርነው ትግልም በብዙ መልኩ ተስፋ ሰጪ እንደሆነም ማሳያ ተደርጎ የሚወሰድ ነው።

ከተማዋን በማደስም ሆነ በኮሪደር ልማቱ ፕሮጀክቱ ዜጎች ተጎጂ እንዳይሆኑ በመንግሥት በኩል የተወሰደው ጥንቃቄ ፤ልማቱን በራሱ በጠንካራ የሥራ ዲሲፕሊን ለመምራት በከፍተኛ አመራሩ በኩል የታየው ቁርጠኝነት ፤ የከተማዋ ነዋሪም በፕሮጀክቱ ዙሪያ በስፋት ለተካሄደው የጥፋት ፕሮፓጋንንዳ ጆሮውን ሳይሰጥ ለፕሮጀክቱ ስኬት እያሳየ ያለው ተነሳሽነት የሚበረታታ ነው ።

ፕሮጀክቱ ከዚህም ባለፈ በሀገሪቱ ለዘመናት የቆየውን ደካማ የሥራ ባህል በመቀየር ፤አዲስ ዘመኑን የሚዋጅ የሥራ ባህል በመፍጠር ሂደት ውስጥ ትልቅ አቅም ተደርጎ የሚወሰድ ነው። በፕሮጀክቱ የሚሳተፉ ዜጎችም ፕሮጀክቱ በጥራት እና በፍጥነት ተጠናቆ ለማየት ያላቸው ጉጉት፤ ከዚህ ጉጉታቸው የሚመነጨው የሥራ ተነሳሽነታቸው እንደ ሀገር የአዲስ የሥራ ባህል ጅማሬ ተደርጎ የሚወሰድም ነው!


አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

ኢፕድ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4200

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**

ወርቁ ማሩ

Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## አሳሳቢው የመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች የሙስና ችግር

ዳንሮባ ከባሴ ጎባ

በቅርቡ ፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት"ማንይጠየቅ?" በሚል ርዕስ የዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ የአሠራር ጥሰቶችን የሚያስመለክት የምርመራ ዘገባ ሠርቷል። የዘጋቢ ፊልሙ ማጠንጠኛ በዩኒቨርሲቲው የተፈጸመን የሕግ ፤ የአሠራር ጥሰትን እና የሙስና ድርጊትን ይመለከታል። ዩኒቨርሲቲው የተማሪ ዜጋ የሚፈራበት ተቋም ከመሆን ይልቅ ግለሰቦች ሀብት የሚያፈሩበት ወደመሆን እንደተሸጋገረ ያስመለክተናል።

ኢትዮጵያ ለሙስና ወንጀሎች ያላት ተጋላጭነት በየጊዜው እየጨመረ እንደመጣ ተደጋግሞ ሲነገር ይሰማል። ከሁሉም በላይ በዩኒቨርሲቲዎች የሚፈጸሙ የሙስና ወንጀሎች እጅጉን አሳሳቢ እየሆነ መምጣቱም አብሮ ይነሳል። ይህ በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ላይ የተሠራው ዘጋቢ ፊልም ብዙ ነገሮችን በግልጽ እንድንመለከት አድርጎናል ማለት ይቻላል።

በዩኒቨርሲቲው የሕዝብና የመንግሥት ሀብትና ንብረት ከሚመዘበርበት መንገድ አንዱ የአበል ጣሪያን በማብዛት የሚፈጸም ክፍያ አንዱ ነው። በተቋሙ በወንበር ላይ የሚገኙ አመራሮች ከሕግ ውጪ የተጋነነ አበል እየወሰዱ ስለመሆናቸው ለመታዘብ ተችሏል ። ለምሳሌ የዩኒቨርሲቲው የፋይናንስ ቡድን መሪ የሆኑ ሁለት ግለሰቦች በስድስት ወራት ብቻ የሁለት ሺህ 430 ቀን ወደ አንድ ሺህ 490 ቀን ማለትም ከአንድ ሚሊዮን 600 ሺህ ብር በላይ አበል እንዲከፈላቸው ተደርጓል።

ሌላው አስደንጋጩ መረጃ ከ1 ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ በዩኒቨርሲቲው እየተሠራ ያለው የኦክስጂን ማምረቻ ማዕከል የመስሪያ ገንዘብ ከፋይናንስ እውቅና እና ከሕግ ውጪ ሲንቀሳቀስ ነበር። የግንባታው ሥራ የተሰጠው ድርጅትም በኮንስትራክሽን ዘርፍ እውቅና የሌለው ስለመሆኑ በምርመራ ዘገባው ተመላክቷል። በአንድ ተቋም ብቻ በዚህ ደረጃ የሕዝብና የመንግሥትን ሀብት ሲመዘበር ማየት ልብን ያደማል።

ይህ የዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ቅሌት በሀገራችን በመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች የሚፈጸም የሙስና ወንጀል ወደ አሳሳቢነት ደረጃ እየተንደረደረ እንደሆነ እንደመስታወት ያስመለክተናል። በየዓመቱ የሚቀርቡ የበጀት ዓመት የኦዲት ሪፖርት ውጤቶችም ዩኒቨርሲቲዎች ከፍተኛ የሆነ የበጀት ምዝበራና ብክነት የሚፈጸምባቸው ቀዳሚ ተቋማት መሆናቸውን ያሳያሉ።

ዩኒቨርሲቲዎች የተሻለ እውቀትን ከመልካም ሥነ ምግባራዊ ቁመና ጋር ያዋሃደ ወጣት ትውልድ በመቅረጽ ረገድ ቁልፉና አዎንታዊ ሚና እንደሚጫወቱ ይታመናል። በሥነ - ምግባር የታነፀ ትውልድ አስተምረው በማስመረቅ ሀገር ከድህነት ቀንበር እንዲያወጡ ይጠበቃል። መንግሥትም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ለማጠናከር ከፍተኛ ሀብት በመመደብ ዘርፉን ለማጎልበት የሚያስችሉ በርካታ ፕሮጀክቶች እንዲተገበሩ ድጋፍ እያደረገ ይገኛል። ነገር ግን ፕሮጀክቶቹ ለገንዘብ ምዝበራው እንደ ዋነኛ መደላድል ሆነው እያገለገሉ ነው።

የማህበረሰብን ችግር ይፈታሉ ተብለው ሲጠበቁ የጥቂት ግለሰቦች የሀብት ምንጭ ሲሆኑ ታዝበናል።የመንግሥት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማቱን በአካባቢያዊነት ፤ በዘመድ አዝማድ የሚፈጸመው ቅጥር ፤ የመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎቹን ወደ ሌብነት መንደርነት አውርዷቸዋል። በተቋማቱ ተጠያቂነት ያለ እስከማይመስል ድረስ የሕዝብ ሀብት ያለአግባብ እየባከነ እና እየተበዘበዘ ይገኛል። ጥቂት በማይባሉ የመንግሥት ከፍተኛ ዩኒቨርሲቲዎች የሚወጡ የኦዲት ሪፖርቶች ይሄንኑ የሚጠቁሙ ናቸው።

እንደ ማሳያ በኅዳር 12 ቀን 2016 ዓ.ም. ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ጋር ውይይት አድርጎ ነበር። ዩኒቨርሲቲው ባለፉት ዓመታት እርምጃ ያልወሰደበት ከ46 ሚሊዮን ብር በላይ የሚሆን የበጀት ጉድለት መኖሩን፤ ማስተካከያ የተደረገበት የበጀት ጉድለት አንድ በመቶ እንደማይሆን ከመጠቆም ውጪ ተጠያቂ ለማድረግ የተሄደበት ርቀት ኢምንት ነው ። ይህ አይነቱ አካሄድ በተቋማቱ ችግሩ እንዲባባስ፤ የሕዝብና የመንግሥት ሀብት በማናለብኝነት እንዲዘረፍ ትልቅ ምክንያት ሆኗል ለማለት ያስደፍራል።

በመንግሥት በኩል ችግሩን ለመቅረፍ እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች እንዳሉ የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ ፤ በተለያዩ መድረኮች ዩኒቨርሲቲዎች የእውቀት ማዕከሎች ፤ የብዙ ደሃ ሕዝብ ሀብት የሚፈስባቸው ቦታዎች ናቸው። ከምንም ነገር በላይ የዚህ ሕዝብ ሀብት የሆነ ተቋም በሌብነት እና በሙሰኝነት የተጨማለቀ አስተዳደር ሊኖረው እንደማይገባ ሲናገሩ ይደመጣል።

የዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት አመራረጥ በሚመለከት አዲስ መመሪያዎች እየተዘጋጁ እንደሆነ፤ ከዚህ ባሻገር የገንዘብ ሚኒስቴር ሦስት ጊዜ መጥፎ የተባለ ኦዲት ካለው ዩኒቨርሲቲውን የሚመሩ ሰዎች ከቦታቸው እንደሚነሱ ፤ በሕግ የሚጠየቁበት ሁኔታም ካለ በሕግ እንደሚጠየቁ ሲናገሩም ተሰምተዋል።

በመንግሥት ደረጃ ችግሩን ለመፍታት ያለው ቁርጠኝነት ከፍ ያለ ቢሆንም፤ በየዓመቱ የሚወጣው የኦዲት ሪፖርት ግን የሕጉን ተፈጻሚነት ጥያቄ ውስጥ ያስገባል። የሀገርን ሁለንተናዊ ቁመና ይበይናሉ ተብለው ተስፋ የሚደረግባቸው ዩኒቨርሲቲዎቻችን፤ በዚህን መጠን ወደሚገለጽ የዝቅጠት ደረጃ መግባታቸው በተቋማቱ ዙሪያ ያለውን የቤት ሥራ ክብደት የሚያመላክት ነው።

አሁን ላይ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት አካባቢ የሚታዩት ብልሹ አሰራሮችን በፍጥነት መንገድ ለማስያዝ ካልተሞከረና እና ልጓም ካልተበጀላቸው ችግሩን መልክ ለማስያዝ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። በተቋማቱ በሚፈጸሙ ሕገወጥ ተግባራት ላይ ተጠያቂነት መስፈን አለበት ።

ሪፖርቶችን ማውጣት ብቻ ሳይሆን ሌቦቹንም ወደ ተጠያቂነቱ ማምጣት ይገባል ። በዋናው ኦዲተር ሪፖርት የበጀት ብክነት ያስከተለ ምዝበራ ስለመፈጸማቸው የሚያመለክቱ መረጃና ማስረጃ የቀረበባቸውን የዩኒቨርሲቲዎቹ ባለድርሻ አካላት ሕግ ፊት በማቅረብ ለጥፋታቸው የሚመጥን ቅጣት እንዲሰጣቸው የማድረግ ጉዳይ ይዋል ይደር የሚባል አይደለም።

" እናቴ በእንቁላሉ ጊዜ ብትቀጪኝ ፤ በሬ አልሰርቅም ...." እንዳለው በየተቋማቱ ያሉ ሌቦች ነገ በሬ ከመስረቃቸው በፊት ዛሬ በእንቁላሉ ጊዜ ቆንጠጥ ማድረግ ይገባል። መንግሥትም ሕግን ማስከበር ሕዝብ አደራ የሰጠው የውዴታ ግዴታው ነው። በየ ተቋማቱ የምዝበራ መሪ ተዋንያን የሆኑትን አካላት ለሕግ በማቅረብ የተጠያቂነት አሠራር መኖሩን ወይም አለመኖሩን ለሕዝቡ ማረጋገጥ ጭምር ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል ።

ስለሆነም መንግሥት ከታሪክ ተወቃሽነት የሚያድነውን የእርምት እርምጃ በመውሰድ ፤ ተቋማቱን ለሀገር አለኝታ የሆነ ቁመና እንዲላበሱ ማድረግ ይገባል። በሌላ በኩል የፌዴራል ጠቅላይ ኦዲተር መስሪያ ቤት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱን አስተዳደራዊ ንቅዘት ይፋ በማውጣት ረገድ በየጊዜው የሚያደርገው ጥረት ተጠናክሮ መቀጠል አለበት፡፡

በአጠቃላይ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሀገሪቱን ከሚፈታተኗት የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ እንዲሁም የማህበራዊ ችግር መገለጫ ድክመቶች መፍትሔ እንዲያመጡ ይጠበቅባቸዋል። ይሁንና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱን አጠቃላይ ቁመና ለስማቸው በሚመጥን አስተዳደራዊ ብቃትና የመልካም ሥነ ምግባር እሴት ላይ እንዳልሆነ መናገር ያስደፍራል።

አብዛኛዎቹ ዩኒቨርሲቲዎቻችን የሙሰኞች መፈንጫ በመሆን፤ ለሀገር እድገት ሳይሆን ስጋትን እየፈጠሩ ናቸው። ስለዚህ በአብዛኛዎቹ የመንግሥት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ከፉኛ የተባባሰውን የሞራል ኪሳራና የሥነ-ምግባር ዝቅጠት በቅጡ የመፈተሽ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል!!

# ነፃ ሃሳብ

## ንግዳችንን ከሴራ ወደ ስራ

ከጥንት እስከዛሬ የሀገራችን የንግድ እንቅስቃሴ አስመጪዎችና ሻጮች የነገሱበት፣ ከውድድር ይልቅ በድርድርና ከመጠን በላይ ትርፍ መዛቅ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ የሸማቹን ኑሮ ከድጡ ወደ ማጡ እያደረገው ነው። ሶስትና አራት እጥፍ ማትረፍ፤ ማጭበርበር እንደ ሕገ-መንግስታዊ ድንጋጌ ወይም መብት ተቆጥሮ የሚፈፅም ተግባር ከሆነ ቆይቷል፡፡

ፈጣሪያቸውን ፈርተው፣ ሕዝባቸውን ወደው፣ ስማቸውን አክብረው የሚሰሩ ነጋዴዎች ግን በንግድ ሰንሰለቱ ውስጥ የሚቆዩበት ጊዜ አጭር ነው። በአድማ ወይም በክስረት ከፍ ሲልም በጉልበት ከገበያው እንዲወጡ ይደረጋል። ይህንን ሴራና አሻጥር ብዙ ጊዜ ሰምተነዋል፤ አይተነዋልም።

የሕዝቡ ጨዋነት፣ የመንግስትን ትእግስት ከመጤፍ ያልቆጠሩ ነጋዴዎችም እንደፈለጉ ሰው ሰራሽ የምርት እጥረትና ውጥረት ሲፈጥሩ ነበር። ትንሹ በመካከለኛው፣ መካከለኛው በትልቁ፣ ትልቁ በጠቅላይ አከፋፋዩ ከዚያም በብቸኛ አስመጪው እያሳበቡ ኑሯችን እንደሮኬት አስወነጨፉት። በመንግስት የሚወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎችና ማስተካካዮችም ወደ እሳት እንደገባ ቅቤ ሕዝብ ጋር ሳይደርሱ ሲቀልጡ እየተመለከትን እንገኛለን ።

የኑሮ ውድነትን ለመቋቋም በተለይም በከተሞች አካባቢ ብዙ ስራዎች ሲሰሩ እናያለን። ከመንግስት ካዝና ብዙ ቢሊዮኖች ፈሰስ መደረጉን እንሰማለን። ነገር ግን የኑሮ ሁኔታው ብዙም መሻሻል ሲታይበት አንመለከተውም። በሂሳብ ትምህርት ብቻ የምናውቃቸውና የምንማራቸው የነበሩ አንዳንድ በተግባር ግን የሌሉ ይመስሉን የነበሩ ቁጥሮች አሁን አሁን በቀላሉ የሚጠሩ የእቃዎች ዋጋ ሆነውም እያገናቸው ነው። የኑሮ ውድነት አልቀመስ ብሏል የሚሉ ድምፆችን መስማት ተለማምደነዋል። ወርሀዊ ደመወዝ የሚያገኝ ሰው ደመወዙን በቀዳዳ ኪስ ያስቀመጠው ያህል እየሆነበት አልበረክት ብሎት ተቸግሯል። የሌላውም ኑሮ እንደዚሁ ምግብ ለስራ ሆኖበታል።

በሌላ በኩል ደግሞ በቀደመው ጊዜ የበሬ መግዣ በሆነ ብር አሁን ለአንድ ኪሎ ስጋ ሲከፍል ምንም የማይጨንቀው፤ በየስጋ ቤቱ እንደፈለገ የሚሆን እና ዓለም ጠባው የሚቸገር፤ ለራስ ምታት ወደ ዱባይ የሚሄደው ሰው ቁጥር እንደዚሁ ብዙ ነው። በከተማችን የሚነዱትን የተሽከርካሪ አይነትና ብዛት ስንመለከት፣ የሚገነቡ ቤቶችንም ስናይ አንዳችም ችግር የሌለብን ያህል እንመስላለን። እንደዚህ አይነቱ እድገትና የኑሮ ልዩነትን ኢኮኒሚስቶቹ ‹‹ዲስቶርትድ›› ወይም የተበላሸ እያሉ ይጠሩታል። በተለይ የኑሮ ልዩነት መስፋቱ አንድ ቀን ብዙሀኑ ጥቂት ቁጥር ባለው የኅብረተሰብ ክፍል ላይ እንዲነሳ ያደርጋል።

በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን መንግስት ኃላፊነቱን ለመወጣት ከሌማት ትሩፋት ጀምሮ የሰንበት ገበያዎችን፣ የሸማች ማኅበራትን፣ ምግብ ማጋራትን፣ የትምህርት ቤት ምገባን ጨምሮ ብዙ ጥረቶች ሲደርግ ይታያል። በርካቶችም ተጠቃሚ እና ተመራጭ ሆነዋል። በተለይ የትምህርት ቤት ምገባ ሚሊዮን ብቁ ሀገር ተረካቢ ተማሪዎችን ከማፍራት በዘለለ በቤተሰቦቻቸው ላይ ጫና የፈጠረውን የኑሮ ውድነት በማገዝ ረገድ ትልቅ ሚና እየተጫወተ ይገኛል።

ነገር ግን በዚህ መልኩ ማኅበረሰቡን የሚጠቅሙ ፈሰሶች በተለያየ መንገድ ተመልሰው ሀብታሞችን የበለጠ ሀብታም እንዳያደርጉ ልዩ ጥንቃቄ ይሻሉ። በትክክልና ግልፅ በሆነ መስፈርት ድሀውን ተጠቃሚ በማድረግ የኑሮ ውድነቱን እንዲቋቋም ማድረግ ያስፈልጋል። በእነዚህ ስፍራዎች ላይ የተሰጣቸውን አደራና ኃላፊነት ለግል ጥቅማቸው የሚያውሉ ኃላፊዎችን በመለየትና በማጣራት በተለየ መልኩ አስተማሪ እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል።

እንዲህ ካልሆነ የዜሮ ድምር/"ቪሺየስ ሰርክል" ጉዞ ወይም በቀዳዳ በርሜል ውሃ የመሙላት ያህል የመንግስትንም ጥረት ከንቱ ያደርገዋል። ሕዝቡንም ተስፋ ያስቆርጠዋል። እናም መንግስት ከሚሰራቸው ስራዎች እኩል ቁጥጥሩን በደንብ ሊያጠብቅ ይገባል።

**ለነገሩ እናቀርብም**
ቢሉ እንኳ መንግስት የንግድ ምህዳሩን በማስፋት የውጭ ባለሀብቶች እንዲገቡበት የወሰነው ውሳኔ መፍትሄ ይዞ መጥቷል። ውሳኔው ንግዳችንን ከሴራ ወደ ስራ፣ ከፉክክር ወደ ድርድር፣ ከነጋዴ ነጋሲነት ወደ ሸማች ንጉስነት ይለውጠዋል ብለን ተስፋ እናደርጋለን

በሌላ በኩል እንደማኅበረሰብ በእኛ ስም የመጣ ድጎማም ይሁን የኑሮ ውድነቱን ለማቃለልና የዋጋ ንረቱን ለመቆጣጠር የተዘየደ መላ አላግባብ ተግባራት እየተከናወኑበት እያየን ዝም ማለት አይገባንም። ዋጋን በማናር ጥቂቶች የማይገባቸውን ቢሊዮኖችን እንዲያገኙ እንደመተባበር ይቆጠራል። የዋጋ መናር የማይመለከተው ሰው ስለማይኖር የኔ ጉዳይ ነው ብለን ልንከላከል ይገባል። እግረመንገዳችንም መብታችንን የማስጠበቅ ባህላችንን እናዳብራለን።

የዓለም ባንክና፣ የዓለም የገንዘብ ድርጅት የሚያወጧቸው ዓመታዊ ሪፖርቶች ውስጥ ሰፊውን ቦታ የሚይዘው ‹‹ኢንፍሌሽን ሬት›› ዋጋ ንረት የሚሉት ነው። እርግጥ የዋጋ ንረት መገለጫው ብዙ ነው። መኪና የተወደደበት እና ጫማ የተወደደበት እኩል አይደሉም፤ ውስኪ የተወደደበትና ነዳጅ የተወደደበትም እንደዚሁ። ሌላው ቀርቶ ልብስ የተወደደበት እና ዳቦ የተወደደበትም አይነፃፀሩም።

መሰረታዊ ፍላጎት የሚሏቸው ልብስና መጠለያ እንዳሉ ሆነው የመኖርና አለመኖር ጥያቄ የሆነው የምግብ መወደድ ግን ከሁሉም የከፋው እንደሆነ ሪፖርቱ ያትታል። የምግብም ይሁን የሌሎች ነገሮች መወደድ በሁሉም ዓለም በማንኛውም ጊዜ የሚከሰት ቢሆንም ሁልጊዜ ግን ጠንካራ ክንዱን የሚያሳርፈው እያደጉ በሚገኙ ሀገራት ላይ ነው። ሕዝባቸው ብዙ የሆነ፣ በአየር ንብረት ለውጥ ተደጋጋሚ ድርቅ በሚያጠቃቸው፣ በውጭ ጣልቃ ገብነትም ሆነ በውስጣዊ ምክንያቶች ግጭቶች በማያጧቸው ሀገራት ደግሞ ጉዳቱ እጥፍ ድርብ ይሆናል፡፡

ሸቀጦች ሲበዛ ገበያው ላይ መወደድ በምርትና ምርታማነት ማሳደግ ላይ የተሰሩ ስራዎች አናሳ አሊያም አሻጥር በበዛባቸው መንገዶች የተተበተበ መሆኑን ያመላክታል። በመፍትሄነትም በዘርፉ ላይ ያሉ አሳሪ ችግሮችን በመቅረፍ ምርትን በማሳደግ በቀጥታ ተጠቃሚው ጋር እንዲደርስ ማድረግ ያስፈልጋል።

በእርግጥ ይህን በአግባቡ የተረዳው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እያከናወነ ያለው ተግባር ለዜጎች ጭንቀት አፋጣኝ ምላሽ የሰጠ ነው። እየተስተዋለ ላለው የኑሮ ውድነት አይነተኛ ችግር ፈቺ ፕሮጀክት ቀርፆ ወደ ስራ አስገብቷል። ፕሮጀክቱ ከ6 ነጥብ 3 ቢሊዮን ብር በላይ የሚጠጋ በጀት ተመድቦለት በመዲናይቱ በሚገኙ በኮልፌ፣ በንፋስ ስልክ፣ በአቃቂ ቃሊቲና በለሚ ኩራ ክፍለ ከተሞች ላይ የግብርና ምርቶችን ማከፋፈያ የገበያ ማዕከላት ተገንብተዋል። ማዕከላቱም ምርትን በቀጥታ ከአምራቹ ወደ ሸማቹ እያደረሱ ይገኛሉ።

የኅብረተሰቡን የኑሮ ውድነት በማቃለሉ ረገድ ትልቅ እፎይታን የሚሰጡት እነዚህ የገበያ ማዕከላት የተለያየ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ። በገበያ ማዕከላቱ እየተገለገሉ ያሉ ሸማቾች መሰረታዊ የምግብ ፍጆታ ፍላጎት አቅርቦቶቻቸው ከመጠን፣ ከጥራትና ከዋጋ አንፃር ተመጣጣኝ መሆናቸውን ሲናገሩ ይሰማል። ማዕከላቱ ከሌሎች የገበያ አካባቢዎች 50 በመቶ ድረስ ዋጋ የሚቀንሱ አቅርቦቶች አሏቸው፡፡

የገበያ ማዕከላቱ የሕብረተሰቡን ኑሮ ከማረጋጋት አኳያ ትልቅ እገዛ እያደረጉ ይገኛሉ። የተለያዩ ምርቶቻቸውን በብዛትም በጥራትም ለማቅረብ እና ማዕከላቱን የሚያንቀሳቅሱ ዜጎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሊሟሉላቸው የሚገቡ የመሰረተ ልማት ስራዎች እንዳሉ ይጠቀሳል። ውሃ፣ መብራት፣ የተስተካከለና የተሳለጠ መንገድ ያስፈልጋቸዋል። መብራት ባለመኖሩ አገልግሎት የሚሰጡበት ሰዓት የተገደበ እንዲሆን አድርጎታል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሕብረተሰቡን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጫናን ከመቅረፍ አኳያ እየሰራ ያለው ስራ ይበል የሚያሰኝ ቢሆንም እነዚህ በመዲናችን በሚገኙ አምስት በሮች ላይ የተገነቡት ዘመናዊ የግብርና ምርቶች ማከፋፈያ የገበያ ማዕከላት የተቀላጠፈ ስራ እንዲሰሩ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ይገባዋል።

ለነጋዴውና ለሸማቹ ሕብረተሰብ የምርት አቅርቦት ሰንሰለቱ በመንግስት በኩል የተመቻቸባቸው እነዚህ ግዙፍ የገበያ ማዕከላት ጊዜውን በሚመጥን የቴክኖሎጂ ልኬት ዘመናዊነታቸውን ጠብቀው የተገነቡ ናቸው። በመደበኛ ወይም በባዕላት ቀናት የሚፈለጉ የምግብ ፍጆታዎች በተመጣጣኝ ዋጋ ለሕብረተሰቡ በአይነትና በጥራት የሚቀርብባቸው በመሆኑ የኑሮ ውድነት ጫናን እንደሚቀንሱ ጥርጥር የለውም።

የአደጉ ሀገራት መሰል ችግሮችን የሚያስወግዱበት የዳበረ ልምድና ጠንካራ ትከሻ አላቸው። በችግሩ እንደ እስፖንጅ ቢጨመቁም ተመልሰው መፍታታት ይችላሉ። የዳበረ ኢኮኖሚያቸው ብዙ አማራጮችን የመፈለግ ብቃት አለው፣ ቴክኖሎጂያቸው ብዙ መፍትሄን ያመጣላቸዋል፣ ተቋማቶቻቸውም ጠንካራ እና ለሕዝብ ጥቅም የቆሙ ናቸው። ከዚህ ጋር በተያያዘ የሸማች ማሕበራትና ዩኒየኖቻቸው በተለየ የሚጠቀስ ስራ አላቸው። ማሕበራት ከማለት ይልቅ ጠበቆች፣ ተከራካሪዎች፣ መከታዎች፣ ቤዛዎች ቢባሉ ይቀላል፡፡

እነዚህ ማሕበራት ባሉባቸው ስፍራዎች ሁሉ ዋጋ ጣሪያ ነካ፣ ኑሮ ተወደደ፣ ስግብግብ ነጋዴ የነቀዘ ስንዴ፣ ሙሰኛ፣ አሻጥረኛ የሚሉ የሰለቹን ቃላት የሉም። ከመንግስት በላይ መንግስት የሆኑ የሸማቹ መከታ ናቸው። ወይ ገዝተው መልሰው በመሸጥ አሊያም ነጋዴው ላይ ማዕቀብ በመጣል ገበያውን ፀጥ ኑሮውን ቀጥ ያደርጉታል።

በሕዝቡ፣ ከሕዝቡ፣ ለሕዝቡ የተቋቋሙ ናቸውና መነሻቸውም መድረሻቸውም የሕዝብ ጥቅም፣ የገበያ መረጋጋት ብቻ ነው። በዚህም ውጤታማ ናቸው። አሜሪካ፣ ህንድ፣ ቻይና፣ ጀርመን፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ኬኒያና ሌሎችም ሀገራት ላይ አሉ።

በሀገራችንም እነዚህ ማሕበራት አሉ። ነገር ግን ገበያውን ማረጋጋት ላይ የሉበትም ማለት ይቻላል። አቅም ይሁን፣ ፍላጎት አልያም ልምድ ብቻ የሆነ ነገር ጎድሏቸዋል። ጥቂቶቹ ብቻ በጥቂት ነገሮች ውጤታማ ሲሆኑ ብዙሃኑ ግን ስማቸው ብቻ ነው የተረፈን። መንግስት እህልን ከአርሶ አደሩ ገዝታችሁ ለሸማቹ አቅርቡ ብሎ ቢፈቅድም፣ ብዙ ነገር ቢያመቻችላቸውም ይህንን ለማድረግ አልፈለጉም፣ ወይም አልቻሉም፣ አልያም ራሳቸው አሻጥሩ ውስጥ ተዘፍቀው የወንጀሉ ዋና ተዋናኝ ሆነዋል።

በጥርና በሀምሌ፣ በጥቅምትና በግንቦት መካከል የዋጋ ልዩነት የለም። ምርቱ ገብቷል በተባለበት ጥር ላይ ያልረከሰ መቼ ሊረክስ ነው? ማህበራት ወዴት ናችሁ እስኪ አቤት በሉ። ዓለም ለሚሳኤል ፅረ ሚሳኤል እንዳዘጋጀች ሁሉ ለማሕበራትም ሌላ ተቆጣጣሪ ማሕበራት ተቋቁመውም ቢሆን እህሉን ያቅርቡልን!

ለነገሩ እናቀርብም ቢሉ እንኳ መንግስት የንግድ ምህዳሩን በማስፋት የውጭ ባለሀብቶች እንዲገቡበት የወሰነው ውሳኔ መፍትሄ ይዞ መጥቷል። ውሳኔው ንግዳችንን ከሴራ ወደ ስራ፣ ከፉክክር ወደ ድርድር፣ ከነጋዴ ነጋሲነት ወደ ሸማች ንጉስነት ይለውጠዋል ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

እነዚህ ታላለቅ ኩባንያዎች ለስማቸው ይጠነቀቃሉና፤ ቢያንስ ጥራት የጎደለው እቃ አምጥተው በገዛ ገንዘባችን በሽታ አያሸምቱንም ብለን እናምናለን። ለስራ ባህላችን መነቃቃትን፣ ለወጣቶቻችን የስራ እድልን፣ ንግድ ማለት ዘረፋ ለሚመስላቸው ብዙዎቹ ነጋዴዎቻችን የትርፍ ህዳግን፣ ለሚያመናጭቁን የደንበኛ አያያዝን ያስተምሩልናል።

በጥራትም፣ በአቅርቦትም፣ በመስተንግዶም የምንረካበት የንግድ ስርዓት እንዲመጣና የተመኘነው ምኞት እንዲሰምርልን መንግስት በፖሊሲ ደረጃ ያፀደቀውን ውሳኔ በፍጥነት ወደ ተግባር ሊለውጠው ይገባል። ይህ ሲሆን የለም፣ ጠፍቷል፣ ተወዷል፣ ጨምሯል የሚሉ ከስግብግብነት ባህሪ የሚመነጩ ቃላት ከመስማት ማረፍ እንችላለን። ይሄ የሁሉም ችግራችን ብቸኛ መፍትሄ ባይሆንም ቢያንስ የጥጋብ ፊኛን የሚያስተነፍስ፣ የሚሸሽ ሸማችን የሚያንቀሳቅስ ተስፋ ነውና መንግስት ሆይ ፍጠን!

# ወቅታዊ

# ‹‹ለሀገራዊ ምክክሩ ስኬታማነት የሚዲያው ሚና የማይተካ ነው››

- ጥበቡ በለጠ

- የኢትዮጵያ ሃገራዊ ምክክር ኮሚሽን የሚዲያ ፎረም ም/ሰብሳቢ

እፀገነት አክሊሉ

በየትኛውም ዓለም የፖለቲካ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ሽግግር ውስጥ የሚዲያ ሚና በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ሚዲያው በአግባቡ ጥቅም ላይ ከዋለ ለሀገር ዕድገትና ለዜጎች ብልጽግና መጎልበት የራሱን በጎ አሻራ ማሳረፍ ይችላል። ባልተገባና ጥንቃቄ በጎደለው ሁኔታ ጥቅም ላይ ከዋለም ደግሞ በዛው ልክ የሚያስከትለው መዘዝ በቀላሉ የሚታይ አይሆንም።

እንደ አገርም ሕዝብን ለልማትና ዴሞክራሲ በማነሳሳት ችግሮች ሲያጋጥሙም ተገቢ በሆነና አግባብነት ባለው መልኩ በመፍታት በኩል የበኩሉን ሚና መወጣት ይችላል። እስካሁንም ቀላል የማይባሉ የሚዲያ ውጤቶች በኢትዮጵያ ልማት እንዲፋጠንና ዴሞክራሲ እንዲተዋወቅ የማይተካ ሚና ተጫውተዋል፡፡

በሌላም በኩል ግጭትና አለመግባባትንም በመፍጠር የኢትጵያን ችግር የሚያወሳስቡ ሚዲዎችም በርካቶች ናቸው። ቀን ከሌት ግጭትና ብጥብጥን የሚሰብኩና ዜጎችን አብሮነት የሚያውኩ መረጃዎችን የሚለቁ በርካታ ሚዲያዎች አሉ። እነዚህ ሚዲያዎች ገንዘብ ያግኙ እንጂ የዜጎች በሰላም ውሎ ማደርና በሕይወት መቆየት አያሳስባቸውም። የሀገር ሕልውናና በሰላም መቆየት ግድ አይሰጣቸውም። ይህ ደግሞ በሌሎች ሀገራት እንደታየው ሁሉ ውጤቱ የከፋና በቀላሉም ለማረም የማይቻል ነው፡፡

እነዚህን ሁለት የሚዲያ ገጽታዎች በመገንዘብና በተቻለም መጠን በጎ ጎናቸውን ለሀገር ጥቅም እንዲያውሉት በማሰብ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምክክር ኮሚሽን ሚዲያው በሀገራዊ መግባባቱ ላይ የራሱን በጎ አሻራ እንዲያሳርፍ የበኩሉን ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

ሚዲያ በሕግ የበላይነትና ዲሞክራሲ ግንባታ ላይ ወሳኝ ሚና እንዳለው ሁሉ አገርን ከአንድ ምዕራፍ ወደሌላ ምዕራፍ ያሻግራል ተብሎ በብዙ ታምኖበት በርካታ ባለሙያዎችና ምሁራን እውቀታቸውን ጊዜያቸውን አቅማቸውን ሁሉ አሟጠው እየተሳተፉበት ያለውን የምክክር ሂደትም ለሕዝብ በማድረስ እና የሕዝቡንም ተሳትፎ በማሳደግ በኩል ትልቅ የቤት ስራ የተሰጠው ሆኗል።

ሚዲያ በሀገራዊ ምክክር ላይ ትልቅ አስተዋፅኦ እንዳለውም እንዲሁም ሚናውን ይበልጥ በተጠናከረና በዳበረ መልኩ ይወጣ ዘንድ በጥቅምት ወር የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን የሚዲያ ፎረም በሚል አንጋፋና ወጣት ባለሙያዎች ከግልና ከመንግስት ተቋም ተሰባስበው እንዲመሰረት ሆኗል።

ይህ ፎረም ኮሚሽኑ የሚሰራቸውን ስራዎች ወደ ሕህዝብ የማድረስ ብሎም ራሱ ነጻና ገለልተኛ ሆኖ ለአገር ይጠቅማል ያለውን ሃሳብ ላይ አቅዶ በመስራት ብዙዎችን መንገድ ሲያሳይም ቆይቷል። ይህ ደግሞ ሚዲያዎች ለአገር ሊያበረክቱ ከሚገባቸው አስተዋጽዖ አንዱና ዋነኛውም ነው።

በምክከር ኮሚሽኑ የስራ እንቅስቃሴም ሆነ አገር ምክክር ላይ ያለች እንድትመስል በማድረጉ በኩል ሚዲያው እስከ አሁን የሰራው ስራ የሚናቅ ባይሆንም አሁንም ግን ስራው የተጠናቀቀ ባለመሆኑ ከፍ ያለ ተሳትፎን ማድረግም እንደሚጠበቅና እንደሚያስፈልግ ይነሳል።

ሚዲያዎቹ በቀጣይ ለሚመጡ ለውጦችም ይሁን እንደ አገር የጀመርነው የምክክር ሃሳብ ዳር ደርሶ እንደ አንድ አገር ሕዝቦች በአንድ አፍ ተናጋሪ በአንድ ልብ መካሪ እስከንሆን ድረስ ሚናቸው ይቀጥል ዘንድም የቤት ስራው እየተሰጣቸው ነው።

መገናኛ ብዙሃኑ ለሕዝብ ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ በማቅረብ ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ የሚያበረክቱትን አስተዋጽኦ እንዲያጠናክሩም ምክክር ኮሚሽኑ የሚችለውን የሚዲያ ተቋማቱም በገንዘብ በሰው ኃይል በጊዜ ሊረባረቡም እንደሚገባቸው ይነሳል።

መገናኛ ብዙሃን በስራዎቻቸው በሕብረ-ብሔራዊ አንድነትን የሚያጠናክሩ ስራዎችን እንዲያከናውኑና የሀሰት መረጃዎችን በመመከት የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ ያስፈልጋል። በቀጣይ የሚከናወነው ብሔራዊ ምክክር የተሳካ እንዲሆን መገናኛ ብዙሃን አወንታዊ ሚናቸውን እንዲወጡ ጥሪ እየቀረበላቸው ነው።

በተለይም ጽንፈኝነትን እና አግላይነትን በማከም በኩል ባለፉት ጊዜያት የተሰሩት ስራዎች ጥሩ ቢሆኑም አሁንም ለሕህዝቡ ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ በማቅረብ ሕብረ ብሔራዊ አንድነትን ማጠናከር ያስፈልጋል።

በሀገር ግንባታ ሂደት የሕብረተሰቡን ተሳትፎ ሊያጎለብቱ የሚችሉ ስራዎች መስራት ከሚዲያ የሚጠበቅ ኃላፊነት ከመሆኑም በላይ የአገራዊ ምክክር ሂደትን ከሚያደናቅፉ ተግባራት በመቆጠብ ለስኬቱ አዎንታዊ ሚና መጫወት ያስፈልጋል። መገናኛ ብዙሃን የአገራዊ ምክክር ሂደትን ከሚያደናቅፉ ተግባራት በመቆጠብ ለምክክሩ ስኬት አዎንታዊ ሚና መጫወት አለባቸው የሚለው የሁሉም ሃሳብ ከመሆኑም በላይ በተለይም የተቋቋመው ፎረም ይህንን በማድረጉ በኩል ሚናው ከፍ ያለ ነው።

እኛም የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን የሚዲያ ፎረም ምክትል ሰብሳቢ የሆኑትን አቶ ጥበቡ በለጠን በእስከ አሁኑ የሚዲያው ተሳትፎ እንዲሁም በቀሩት ጥቂት ወራቶች ውስጥ ሊተገበሩ ስለሚገባቸው ጉዳዮች ቃለ ምልልስ አድርገናል።

**አዲስ ዘመን - መገናኛ ብዙሃን ሀገራዊ ምክክሩን ውጤታማ በማድረግ በኩል ያለው ሚና እንዴት ይገለጻል**

**አቶ ጥበቡ በለጠ፡-** መገናኛ ብዙሃን ሰላምና ዴሞክራሲን በማስፈን እና ቀጣይነት ያለው ልማት እንዲረጋገጥ የማይተካ ሚና ይጫወታሉ። በተለይም በዜጎች መካከል የሃሳብ ልውውጥ እንዲኖርና የተግባባ ማኅበረሰብ እንዲፈጠር በማድረግ በኩል ድርሻቸው የጎላ ነው፡፡

አሁን ያሉት አለመግባባቶች ተወግደው በፍቃደኝነት እና በመግባባት ላይ የተመሰረተች ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ ምክክሩ የማይተካ ሚና አለው። ሀገራዊ ምክክሩ ከዘመን ወደ ዘመን ሲንከባለሉ የመጡ ችግሮችን ለመፍታትና የመወያየትና የመነጋገር ባሕልንም ለማዳበር ይረዳል። በመወቃቀስ ላይ የሚያተኩረውንም የፖለቲካ ባህላችንንም ወደ መነጋገር፤ መተባበርና መደጋገፍ እንዲመጣ ያደርጋል። ይህ እውን እንዲሆን ደግሞ ሚዲያው የአንበሳውን ድርሻ ይወስዳል።

ይህንን ሚናቸውን ለመወጣት ደግሞ መገናኛ ብዙሃን ኮሚሽኑ የሚያከናውናቸውን ተግባራት ለሕዝቡ ተደራሽ በማድረግ፣ ሕብረተሰብን የሚያስተሳስር ድልድይ በመሆን ሚናቸውን ማሳደግ አለባቸው።

አገራዊ ምክክሩ የአገር ፕሮጀክት በመሆኑ መገናኛ ብዙሃን ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ይህ ፕሮጀክት እንዲሳካ በኃላፊነት መስራት አለባቸው። በዚህም መገናኛ ብዙሃን የአገራዊ ምክክር ሂደትን ከሚያደናቅፉ ተግባራት በመቆጠብ ለምክክሩ ስኬት አዎንታዊ ሚና መጫወት ይኖርባቸዋል ፡፡

**አዲስ ዘመን ፡- አገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ከሚዲያው ጋር በምን አይነት መልኩ ነው እየሰራ ያለው ?**

**አቶ ጥበቡ ፡-** አገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ እንደተቋቋመ በርካታ ዘርፎች ነበሩት አንዱ ደግሞ የሚዲያው ዘርፍ ነው። ይህንን ዘርፍ ተባብሮ መስራት ከተቻለ ማሳደግ እንደሚቻል ታምኖበት በጥቅምት ወር 2016 ዓ.ም በአዳማ ከተማ ላይ የመገናኛ ብዙሃን ስብሰባ ተደርጎ ስራውን በተቀናጀና በተናበበ መልኩ ያለመቆራረጥ የሚሰራ አንድ ስብስብ ሊኖር ይገባል በመባሉ የአገራዊ ምክክር ኮሚሽን የሚዲያ ፎረም ተቋቋመ።



**አ**ገራዊ ምክክሩ የአገር ፕሮጀክት በመሆኑ መገናኛ ብዙሃን ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ይህ ፕሮጀክት እንዲሳካ በኃላፊነት መስራት አለባቸው

ፎረሙ ሲቋቋምም በዋናነት በአገሪቱ ትልልቅ የሆኑና ለሕዝብ ተደራሽነታቸውም ሰፊ የሆነ የመንግስትና የግል የሚዲያ ተቋማት እንዲካተቱበት ተደርጓል። ከስብስቡና ከምስረታው በኋላ ፎረሙ የተለያዩ የወረቀት ስራዎችን ሲያከናውን ነው የቆየው፤ በዚህም አንደ መገናኛ ብዙሃን የእኛ ሚና ምንድን ነው? ኮሚሽኑን እንዴት እናግዝ ? ሙያችንን በመጠቀም የዜግነት ግዴታችንን እንዴት እንዴት መወጣት እንችላለን ? የሚለውን ሃሳብ በብዙ ከተወያየንበት በኋላ እንደዜጋ በሙያችን የሚጠበቅብንን ማድረግ አለብን በማለት ስምምነት ተደርሶ ነው ወደ ስራ የተገባው።

ሚዲያው እንደ አንድ ትልቅ ተቋም ሰላም ላይ፤ አንድነትና መረጋጋት ላይ የመስራት ስነ ምግባራዊ ጉዳዮች ስላሉት በዛ መልኩ ሙያችን ላይ አተኩረን እንስራ በሚል ሚዲያዎችን የሚያስተባብር ሰነድ እንዲዘጋጅ ተደርጓል። በመቀጠልም ሚዲያው የሚተዳደርበትንና የሚገዛበትን ሕግ በማፅደቅ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡

ከዚህ ሁሉ በላይ ግን ከሁሉም ሚዲያዎች የተውጣጡ ትልልቅ ኃላፊዎች ስለነበሩ የአገራዊ ምክክር ኮሚሽኑን አጀንዳ በደንብ እንዲሰራበት አድርጓል። በዚህም ከጥቅምት ጀምሮ የተሰሩት ስራዎች ሰፊ ተቀባይነትን አግኝተዋል።

**አዲስ ዘመን፡- ከጥቅምት ወር ወዲህ በመገናኛ ብዙሃኑ በኩል ስለ ምክክር የተሰሩትን**

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

## ‹‹ለሀገራዊ ምክክሩ ስኬታማነት የሚዲያው...

ከገጽ 7 የዞረ

**ስራዎች እንዴት ይገመግሟቸዋል?**

**አቶ ጥበቡ፡-** እውነት ለመናገር ብዙ ስራዎች ተሰርተዋል፤ የአብዛኞቹ ትልልቅ ሚዲያዎች ኃላፊዎችም በፎረሙ ውስጥ ስላሉ ኮሚሽኑ የሚያዘጋጀውንም ሆነ በራሳቸው እቅድ ይዘው የተለያዩ የዘገባ ስራዎችን በሚገባ ሰርተዋል። መስራትም ብቻ ሳይሆን ሞጋች የሆኑ ነገሮችንም በማንሸራሸር በኩል በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል። በተለይም የሚስተዋሉ ችግሮች እንዲታረሙ በማድረግ በኩል በአደባባይ ሲጽፉም ሲናገሩም ነበር፤ ይህ ደግሞ ኮሚሽኑን ከማጠናከሩም በላይ ምን መስራት እንዳለበት ውጤትን በምን መልኩ እንደሚያገኝ ያመላከተ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡ - በኢትዮጵያ የሚስተዋሉ ችግሮች አሁን የተከሰቱ ሳይሆኑ ሲንከባለሉ የመጡ ናቸው። እነዚህን ችግሮች በማስገንዘብ በኩል የሚዲያው ሚና እንዴት ይገለጻል ?**

**አቶ ጥበቡ በለጠ፡-** ኋላ ቀሩ የፖለቲካ ባኅላችን በርካታ ችግሮችን አስከትሎብናል። ከመነጋገር ይልቅ በር ዘግቶ መወቃቀስና አልፎ ተርፎም ነፍጥ እስከማንሳትና መገዳደል ድረስ አድርሶናል። ያለፈን ታሪክ በማንሳት መወቃቀስና አልፎ ተርፎም ወደግጭት መግባት የትም አያደርሰንም። ከዚያ ይልቅ ቁጭ ብሎ በመመካከርና በመነጋጋር የተፈጸሙ ችግሮች ካሉ እንኳን አስተካክሎ ካልሆነም ይቅር ተባብሎ ወደ ፊት መቀጠሉ ለሁሉም ወገን አዋጭ ነው። ይህንን እና ሌሎች የታሪካችን ጠባሳ የሆኑ ጉዳዮች ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እልባት እንዲያገኙ ሚዲያው ሲሰራ ቆይቷል፤ ወደፊትም መስራት ይጠበቅበታል።

በመሰረቱ የኢትዮዳያ ችግር ረጅም ዓመት ሲንከባለል ቆይቶ የመጣ ነው አሁን በሰራነው ስራም ብቻ ይፈታል ብሎ ማሰብም ቀልድ ነው፤ የሚሆነው ነገር ግን ሚዲያው የምክክር ኮሚሽኑን ስራ ለማገዝ እየተጋ ያለበትን ሁኔታ አጠናክሮ በመቀጠል እሱም አቅድ ይዞ በመስራትና በማሰራት ውጤት ማምጣት ይገባል።

ከዚህ ባለፈ ግን ከጥቅምት ወር ጀምሮ የተሰሩ ስራዎች በጣም ብዙ ውጤትም የታየባቸው ናቸው ማለት ይቻላል። እንደው እውነት ለመናገር ኮሚሽኑ ፈልጎት አልያም ሕብረተሰቡ ጋር መድረስ አለበት ተብሎ ታምኖ ያልተሰራ ስራ የለም። ከዚህ በተጨማሪ እንደውም ሌሎች ዋና ስራቸው አድርገው ፕሮግራም ቀርጸው የውይይት መስመሮችን እየከፈቱና ተወያዮችን እየጋበዙ ሰርተዋል። ይህ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት፡ ፡

**አዲስ ዘመን፡- ጋዜጠኞች የስራውን ክብደት ምን ያህል ተገንዝበውታል ?**

**አቶ ጥበቡ ፡-** በጣም ጥሩ ጥያቄ ነው። ይህ ስራ በጣም ተፈላጊና ዘላቂ ከመሆኑ አንጻር ጋዜጠኞች ስለምክክርም ሆነ ስለ ምክክር ኮሚሽኑ በቂ እውቀትና ግንዛቤ ኖሯቸው ይሰሩ ዘንድ ሕጉን፤ ደንቡን፤ ዓላማውን እንዲረዱ ማድረጉ የሚጠበቅ ስራ ነው። እነዚህ በዚህ ልክ የተረዱ ባለሙያዎች ደግሞ ስለጉዳዩ የሚመለከተውን ሰው ቁጭ አድርገው ልክ እንደ ኢኮኖሚ፤ ፖለቲካ፤ማኅበራዊ ጤና ጉዳዮች የሚሞግቱ ጋዜጠኞችን ማፍራት አለብን።

በመሆኑም ከዚህ በኋላ በየቢሮው የሚሰጡ ስልጠናዎች ይህንን መሰል ባለሙያ ለማውጣት የሚያግዙ እንዲሆኑም ይሰራል። ምክንያቱም ምክክሩን ሁነቶችን እየፈለጉ ከመዘገብ ባሻገር በጥልቀት መስራት ከሕግና ከሌሎች ነገሮች ጋር እያዛመዱ መተንተንም ቀጣይ ሊኬድበት የሚገባ ጉዳይ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ማኅበራዊ ሚዲያውን ጨምሮ ሌሎች በጋዜጠኝነት ስም የሚንቀሳቀሱ አካላት ሚናቸው ምን መሆን አለበት ?**

**አቶ ጥበቡ፡-** ሀገራዊ ምክክሩ እንዲሳካ የማድረጉ ጉዳይ ለእዚህ፤ ለእዚያ ተብሎ የሚተው አይደለም። የግልም ሆነ የመንግስት ሚዲያዎች ወይንም ማኅበራዊ ሚዲያው ላይ የሚሳተፉ አካላት በሙሉ ሀገራዊ ምክክሩ እንዲሳካ መስራት አለባቸው። ሚዲያውም ሆነ ሌላው አካል ሊኖር የሚችለው ሀገር ስትኖር ነው፡፡

ሆኖም ሁሉም አካል በእኩል መጠን እተንቀሳቀሱ ነው ማለት አይቻልም። እንደዚህ ዓይነት ነገሮች ይኖራሉ፤ በተለይም በማኅበረሰብ ትስስር ገጾች ላይ ከአንድነት ይልቅ ልዩነትን የሚሰብኩ፤ ከሰላም ይልቅ ጥላቻን የሚዘሩ ግለሰቦች ሊኖሩ ይችላሉ። ምክንያቱ ደግሞ ማኅበራዊ ትስስር ገጹን የሚያንቀሳቅሱት ግለሰቦች በመሆናቸው ተቋም ስለሌላቸው ኤዲቶሪያል ፖሊስ ወይም ሌላ የሚገዛቸው ሕግ ስለማይኖራቸውና አንጻራዊ ነጻነትም ስላላቸው ከብሄራዊ ምክክሩ ዓላማ ያፈነገጡ ነገሮችን ሊሰሩ ይችላሉ። ነገር ግን በሂደት በተለይም የምክክር ኮሚሽኑን ዓላማና ግቦች በማስረዳት ማስተካከል የሚቻል ይመስለኛል። ደግሞ ልዩነትም መኖሩን መጥላት አያስፈልግም ዋናው ነገር ግን መሰረታዊውን ነገር አለመሳት ብቻ ነው።



ኋላ ቀሩ የፖለቲካ ባህላችን በርካታ ችግሮችን አስከትሎብናል፡፡ ከመነጋገር ይልቅ በር ዘግቶ መወቃቀስና አልፎ ተርፎም ነፍጥ እስከማንሳትና መገዳደል ድረስ አድርሶናል፡፡ አሁን ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት ግጭት፤ ጦርነትና መወነጃጀል ሳይሆን ውይይትና ምክክር ብቻ ነው

**አዲስ ዘመን፡- ኮሚሽኑ የስራ ጊዜውን ሲያጠናቅቅ አስር ያህል ወራቶች እንደቀሩት ይነገራልና እንደው በእነዚህ ወራቶች ውስጥ የሚዲያው ሚና ምን ሲሆን ይገባል እንዴትስ ነው መቀጠል ያለበት?**

**አቶ ጥበቡ፡-** አዎ እንደተባለው የቀሩት ጊዜያት በጣም ጥቂት ናቸው። እነዚህን ጊዜዎች ደግሞ ለአገር የሚጠቅሙ ስራዎች የሚሰሩበት ነው ብዬ አምናለሁ። ምክክር ኮሚሽኑም ባለፉት ዓመታት የለፋባቸውን ነገሮች ዳር እንዲያደርስ የሚያግዙትን ስራዎች መስራት ይጠበቅብናል። እስከ አሁን ከመጣንበት በተለየ እና በተጠናከረ መንገድም መስራት ከሁሉም የሚዲያ አካላት የሚጠበቅ ኃላፊነትም ነው።

በሌላ በኩልም የምክክር ኮሚሽኑ ያስቀመጣቸው እቅዶች አሉ፤ እነሱን መሰረት በማድረግ ሕብረተሰቡ ጋር ሊደርስ የሚችል፤ ደርሶም ውጤት የሚታይበትን ስራ መስራት ያለባቸው ከመሆኑም በላይ ሚዲያዎች እስከ አሁን ከመጡበት አካሄድ ለየት ባለ ሁኔታ የራሳቸውን እቅድ ይዘው መስራት አለባቸው።

ለምሳሌ የኢትዮጵያ ችግር ምንድን ነው? የቱስ ጋር ነው? የቱ ጋር ነው የተበላሸነው? ለምን ሰላም አጣን? ለምንድን ነው እዚህም እዚያም ሰዎች በጦርነት የሚያልቁት? ለምን መነጋገር አቃተን? ምንድነው ችግሩ? እያሉ እየሰሩ ግን ደግሞ ወደዋናው የምክክር መድረክ የሚመጣበትን መንገድ ሁሉም ቁጭ ብሎ የሚነጋገርበትን አውድ መፍጠር የሚጠበቅ ነው።

ምክንያቱም ዛሬ ጋዜጠኛ ሆነን የተለያየ ቦታ እንደልባችን ሄደን ዘገባ የምንሰራበት ወቅት ላይ አይደለንም፤ ይህ ሁኔታ በራሱ ሚዲያው የምክክሩ አካል እንዲሆን ያስገድደዋል፤ በመሆኑም እነዚህ ነገሮች ሁሉ ከግምት ውስጥ በማስገባት በጣም በጥልቀት ሰርቶ የምክክር ኮሚሽኑን የሶስት ዓመት የስራ እቅድ በቀሩት አስር ወራት ውስጥ ስኬታማ ማድረግ ይገባል።

የምክክር ኮሚሽኑ የተሰጠውን ጊዜ ሊያጠናቅቅ የቀረው 10 ወራት ብቻ ቢቀሩትም በአግባቡ ከተጠቀምንባቸው እነዚህ አስር ወራት ለኢትዮጵያውያን ወሳኝ ጊዜያት ናቸው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡

ቀሪዎቹ አስር ወራት ከፍተኛ የሆነ ስራ የሚሰራባቸው ጊዜያት ናቸው። እስከ አሁን የነበረው ስራ ቢያንስ በምክክሩ የሚሳተፉ ሰዎችን የመለየት ነው። ይህ ሂደት በራሱ እስከ ወረዳና ቀበሌ ድረስ መውረድን የሚጠይቅ በመሆኑና ሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍሎች ወደፊት ማምጣት ስለነበረብን ረዘም ያለ ጊዜን ወስዷል። ሌላው ፓርቲዎችን ወደዚህ ምክክር ማምጣቱ በጣም አስቸጋሪ ሆኖ ስለቆየ ኮሚሽኑ ሰፊ ጊዜን ወስዶበታል። ከዚህ በኋላ ያሉትን ጊዜ በአግባቡ ለመጠቀም ሁሉም ዜጋ ለብሔራዊ ምክክሩ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በቀሪዎቹ ጊዜያት ከእያንዳንዱ ዜጋ ምን ይጠበቃል ?**

**አቶ ጥበቡ በለጠ፡-** ኋላ ቀሩ የፖለቲካ ባህላችን በርካታ ችግሮችን አስከትሎብናል። ከመነጋገር ይልቅ በር ዘግቶ መወቃቀስና አልፎ ተርፎም ነፍጥ እስከማንሳትና መገዳደል ድረስ አድርሶናል። አሁን ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት ግጭት፤ ጦርነትና መወነጃጀል ሳይሆን ውይይትና ምክክር ብቻ ነው።

ስለዚህም ችግሮችን በውይይት የመፍታት ባሕልም እንደሀገር ሊጎለብት ይገባል። የስልጣኔም አንዱ መለኪያም ይኸው ነውና። በኢትዮጵያ የፓርቲ ፖለቲካ ሥራ ውስጥም ሆነ በሌሎች መስኮች የተሰማሩ ወገኖች፣ ለውይይት ቅድሚያ መስጠት አለባቸው። ሀገራዊ ምክክሩን እንደ ዕድል ሊጠቀሙበት ይገባል፡፡

እንደ ሕዝብም የታሪካችን አንዱ ክፋይ ሆኖ ዘመናትን የተሻገረውን ጦርነትና ግጭትን ለማስወገድና የተረጋጋች፤ ሰላሟ የተጠበቀ እና የበለጸገች ኢትዮጵያን ለመጭው ትውልድ ለማውረስ ሀገራዊ ምክክሩ ይዞ የመጣውን ዕድል መጠቀም ሀገርን የማሻገር አንዱ ተልኮ ነው፡፡

ስለዚህም በየትኛውም ጫፍ ያለ ኢትዮጵያዊ በዚህ የምክክር ሂደት መሳተፍና የመፍትሄው አካል መሆን ሀገርን ማዳን መሆኑን ሊረዳ ይገባል።

አካታች አገራዊ ምክክሮችን ማድረግ የተሻለ አገራዊ መግባባትን ይፈጥራል። ኢትዮጵያውያን በዘር፤ በሃይማኖት፤ በጾታና በአካባቢያዊ ርቀት ሳይገደቡ ስለሀገራቸው መጻኢ ዕድል ሊመክሩ ይገባል፡፡

ብሄራዊ ምክክሩ ከሞላ ጎደል ሁሉም ሃሳብ አለኝ የሚል የሕብረተሰብ ክፍል ሃሳቡን ያለምን ገደብ የሚሰጥበትና በመደማመጥ ጉዳዮች እልባት የሚያገኙበት ይሆናል የሚል ተስፋ መጨበጥ አለብን።

**አዲስ ዘመን ፡- ስለነበረን ቆይታ በጣም አመሰግናለሁ።**

**አቶ ጥበቡ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## በኤሌክትሪክ የሚሰሩ መኪኖችን በመገጣጠም ስራ የተሰማሩት የኢትዮጵያ ኩባንያዎች

**ፍሬሕይወት አወቀ**

መንግሥት የአምራች ኢንዱስትሪውን ተወዳዳሪነትና ተሳታፊነት ማረጋገጥ የሚያስችሉ የተለያዩ ሥራዎችን እየሠራ መሆኑ ይታወቃል። አምራች ኢንዱስትሪዎች ውጤታማ በመሆን ከውጪ የሚገቡ ምርቶችን በአገር ውስጥ ምርት መተካት እንዲችሉ በሚደረገው ጥረት የ‹‹ኢትዮጵያ ታምርት›› ንቅናቄ ትልቅ ድርሻ እንዳለው ይታመናል።

ከዚህም ባለፈ መንግሥት በ2022 ኢትዮጵያን የአፍሪካ ብልጽግና ተምሳሌት የሚያደርጉ የተለያዩ ዕቅዶችን በማውጣት እየሠራ ይገኛል። ይህም አምራች ኢንዱስትሪውን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ማድረግ የሚችል ዕቅድ እንደሆነ ይታመናል።

እነዚህ ምቹ ሁኔታዎች አምራች ኢንዱስትሪዎች ከመቼውም ጊዜ በበለጠ መነቃቃት እንዲፈጠርባቸው አድርገዋል። በተለይ በ‹‹ኢትዮጵያ ታምርት›› ንቅናቄ ተነቃቅተው ውጤት ማስመዝገብ የቻሉ አምራች ኢንዱስትሪዎችም ቀላል ግምት የሚሰጣቸው አይደሉም። በአሁኑ ወቅትም በአገሪቱ በሁሉም ዘርፎች ተስፋ ሰጪ ተግባራት እየተከናወኑ ሲሆን፤ በተለይም በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ እየታየ ያለው ለውጥ ይበል የሚያሰኝ ነው።

አበረታች ውጤት እያስመዘገበ ባለው በዚህ አምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ከተሰማሩ ኢንዱስትሪዎች መካከልም ሀገሪቱ ለነዳጅ የምታወጣው የውጭ ምንዛሬ የሚያስቀሩትን፣ ለአካባቢ ተስማሚ የሆኑትን የኤሌክትሪክ መኪኖችን በአገር ውስጥ በመገጣጠም ለገበያ ለማቅረብ እየሰሩ ያሉ የአገር ውስጥና የውጭ አገር ባለሃብቶች ይገኙበታል።

በአገር ውስጥ ከሚገኙ አምራች ኢንዱስትሪዎች መካከል በቡና ምርትና ኤክስፖርት እንዲሁም በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ የሚታወቀው ቀርጫንሼ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ድርጅት አንዱ ነው።


የድርጅቱ መስራችና ባለቤት አቶ እስራኤል ደገፋ ኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ መኪናን መጠቀም የሚያስችል ፖሊሲን ተግባራዊ ማድረጓን ጠቅሰው፣ በማኅበረሰቡም ዘንድ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን የመጠቀም ፍላጎት ከፍ እያለ መምጣቱን ጠቅሰዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ የተለያዩ ድርጅቶች ፖሊሲውን መሰረት በማድረግ እንዲሁም ይህን የተጠቃሚዎችን ፍላጎት ከግምት ውስጥ በማስገባት የኤሌክትሪክ መኪኖች በአገር ውስጥ አገልግሎት ላይ እንዲውሉ እየተሠራ ነው። የኤሌክትሪክ መኪኖቹን ከውጭ ወደ አገር ውስጥ ከማስገባት ይልቅ በአገር ውስጥ ገጣጥሞ ለተጠቃሚዎች ማቅረብ የበለጠ አዋጭና ተመራጭ ሲሆን፤ በተለይም በውጭ ምንዛሪ እጥረት ለምትፈተን አገር የጎላ አበርክቶ ይኖረዋል።

በአሁኑ ወቅት በነዳጅ ከሚሰሩ መኪኖች ይልቅ በኤሌክትሪክ የሚሰሩ መኪኖች እየተበራከቱ መምጣታቸውን የጠቀሱት አቶ እስራኤል፤ የኤሌክትሪክ መኪኖቹ አዋጭና ተመራጭ መሆናቸውንም ይናገራሉ፤ ድርጅታቸው በአሁኑ ወቅት የኤሌክትሪክ መኪኖችን በአገር ውስጥ በመገጣጠም ወደ ገበያው ለመግባት እየተንደረደረ መሆኑን አመላክተዋል። የኤሌክትሪክ መኪኖቹን በአገር ውስጥ የመገጣጠሙን ሥራ ከውጭ ድርጅት ጋር እንደሚሰራ ጠቅሰው፣ ይህም በመገጣጠሙ ስራ ውጤታማ ለመሆን የተሻለ መንገድ መሆኑን አስታውቀዋል።

‹‹አምራች ድርጅቶች አዳዲስ ምርቶችን ወደ ገበያ ይዘው በመምጣት የአገሪቷን የማምረት አቅም ማሳደግ አለባቸው›› የሚሉት አቶ እስራኤል፤ ኢትዮጵያ እስካሁን የዓለም ሸቀጥ ማራገፊያ ሆና ቆይታለች። ይህንን ለመቀየር ደግሞ ጊዜው አሁን ነው ብለዋል። አምራች ኢንዱስትሪዎች ጥራት ያላቸውና ተወዳዳሪ ምርቶችን በማምረት ከአገር ውስጥ አልፎ በውጭ ገበያ ተደራሽ ለመሆን መስራት እንዳለባቸውም አስገንዝበዋል። ይህን በማድረግ በግብርና ምርቶች ኤክስፖርት ብቻ የምትታወቀው ኢትዮጵያ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፉም ተሳታፊ መሆን አለባት፤ ለዚህም የመንግሥት ድጋፍና ክትትል ወሳኝ መሆኑን አመላክተዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ በርካታ ሀገራት የኤሌክትሪክ መኪኖችን ምርጫቸው በማድረግ ተጠቃሚ ሆነዋል። እንደ ኢትዮጵያ የውጭ ምንዛሪ እጥረት የሚፈትናቸው አገራትም ቢሆኑ የኤሌክትሪክ መኪኖችን መጠቀማቸው



አዋጭነቱ አያጠያይቅም። ድርጅቱ በአገር ውስጥ የሚገጣጥማቸውን የኤሌክትሪክ መኪኖች ወደ ገበያው ከማስገባቱ አስቀድሞ ይጠቀምባቸዋል። በቀጣዩ ዓመት ድርጅቱ እንደ ድርጅት ሙሉ ለሙሉ የኤሌክትሪክ መኪኖችን የሚጠቀም ይሆናል። በዚህም ከነዳጅ ጋር ተያይዘው ያለአግባብ የሚመጡ ከፍተኛ ወጪዎችን መቀነስ ይቻላል።

‹‹ኢትዮጵያ በየዓመቱ በቢሊዮኖች የሚቆጠሩ ዶላሮችን ለነዳጅ ታወጣለች›› ያሉት አቶ እስራኤል፤ ይህን ከፍተኛ የአገሪቷ ወጪ መቀነስ እንደሚገባም ገልጸዋል። በአሁኑ ወቅት በነዳጅ የሚንቀሳቀሱ ዘመናዊ ተሽከርካሪዎችን በኤሌክትሪክ ለመቀየር እየተደረገ ያለው እንቅስቃሴ እጅግ የሚበረታታና ውጤታማ እንደሆነ ጠቅሰዋል። በተያያዘም ለነዳጅ የሚወጣውን ከፍተኛ ወጪ በመቀነስ ለሌሎች የልማት ሥራዎች እንዲውል በማድረግ የአገርን ኢኮኖሚ ማሳደግ ይቻላል ብለዋል።

የኤሌክትሪክ መኪኖችን ቻርጅ ለማድረግ ቢበዛ 30 ደቂቃ እንደሚወስድ አቶ እስራኤል አስታውቀው፣ ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ ነዳጅ ለመቅዳት በየማደያው ከሶስት ሰዓታት በላይ መቆም የግድ የሚሆንበት ሁኔታ እንዳለም ተናግረዋል። ማንም ሰው የኤሌክትሪክ መኪኖቹን በቤቱ ሆኖ በፈጣን ቻርጀር ለ30 ደቂቃ ቻርጅ በማድረግ ከ800 እስከ 1000 ኪሎ ሜትር መጓዝ እንደሚችልም አመልክተዋል። ይህን በተግባር ማየት ችያለሁ ሲሉ ጠቅሰው፣ መኪናቸውን በሳምንት አንድ ጊዜ ለ30 ደቂቃ በፈጣን ቻርጀር ቻርጅ እንደሚያደርጉና በቀላሉ የሚያልቅ እንዳልሆነም ተናግረዋል። የነዳጅ ወጪያቸውን በከፍተኛ መጠን መቀነስ መቻላቸውንም አስታውቀዋል።

አቶ እስራኤል እንዳብራሩት፤ የኤሌክትሪክ መኪኖች ወጪ ከመቀነሳቸው ባለፈ ጬኸት ወይም ድምጽ እና ጭስ የሌላቸው በመሆኑ ከተማን አይበክሉም። ንጹህ አየር መተንፈስ ያስችላሉ። ቴክኖሎጂው እጅግ አስፈላጊና ተስማሚ ስለመሆኑ እስካሁን በሚገባ አላየንም፤ አሁን ግን አይናችንን ከፍተን ልናየው የሚገባ ትልቅና ዘርፈ ብዙ አበርክቶ ያለው ነው።

የኤሌክትሪክ መኪኖቹ በዋናነት የሚፈልጉት የኤሌክትሪክ ኃይል እንደመሆኑ የኤሌክትሪክ መኪኖቹን ቻርጅ ለማድረግ ብዙ ቦታ አይፈልግም፤ በትንሽ ቦታ ላይ እንደ ሞባይል ስልክ ቻርጅ ማድረግ ይቻላል። በከተማ ውስጥ የተለያዩ ቦታዎች ላይ ቻርጅ ማድረጊያ ማዕከላት ሊኖሩ ይገባል። ለዚህም ድርጅታቸውም ከከተማ አስተዳደሩ ጋር እየተነጋገረ ይገኛል። ከተማ አስተዳደሩም ፈጣን ቻርጅ ማድረጊያ ማዕከላትን በቅርቡ ያመቻቻል የሚል ዕምነት አለ።

ቀርጫንሼ ትሬዲንግ አሁን እየገጣጠማቸው ከሚገኙት የኤሌክትሪክ መኪኖች መካከል የሕዝብ ማመላለሻ አውቶብሶችን ጨምሮ የቤት አውቶሞቢሎች ይገኙበታል። በአሁኑ ወቅትም የመገጣጠም ስራቸው የተጠናቀቀ ለገበያ ሊቀርቡ የተዘጋጁ 100 የኤሌክትሪክ አውቶሞቢሎች አሉ። እነዚህ አውቶሞቢሎችም ለሜትር ታክሲ ወይም ለራይድ አገልግሎት መዋል የሚችሉ ናቸው። ተሽከርካሪዎቹ ወጪ ከመቆጠብና የአየር ብክለትን ከመከላከል ባለፈ ለሥራ ዕድል ፈጠራም የሚኖራቸው አስተዋጽኦ የላቀ ነው።

ሌላኛው የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን እየገጣጠመ ያለው የበላይነህ ክንዴ ግሩፕ የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ሰጠኝ እንግዳው እንዳሉት፤ ኩባንያው የኤሌክትሪክ መኪኖቹን በአገር ውስጥ መገጣጠም የጀመረው ከ2015 መገባደጃ አንስቶ ነው።

እ.አ.አ ከ2019 ጀምሮ የኤሌክትሪክ መኪኖች በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ቁጥራቸው እየጨመረ መጥቷል። በአሁኑ ወቅትም ከ25 ሚሊዮን በላይ የኤሌክትሪክ መኪኖች ዓለም ላይ ይገኛሉ። እነዚህን መኪኖች በመያዝ ትልቁን ድርሻ የምትይዘው ቻይና ናት፤ 60 በመቶ ያህሎቹ የኤሌክትሪክ መኪኖች እየተመረቱ ያሉትም በቻይና ነው።

ኢትዮጵያ ውስጥ በበላይነህ ክንዴ ግሩፕ የሚገጣጠሙት የኤሌክትሪክ መኪኖችም ቻይና ውስጥ ባሉ የጎልደን ድራገን ብራንድ የሚመረቱ መሆናቸውን አቶ ሰጠኝ ጠቅሰው፣ ኩባንያው በሕዝብ ትራንስፖርት ላይ ከፍተኛ ድርሻ ካላቸው መካከል የጎልደን ድራገን ብራንዶችን ወደ ኢትዮጵያ በማምጣት እየተገጣጠመ ይገኛል ብለዋል። በ2015 ዓ.ም መገባደጃ የመጀመሪያዎቹን 216 የኤሌክትሪክ መኪኖችን በተለይም 15 ሰዎችን የሚጭኑ ሚኒባሶችን ማቅረብ መቻሉን ገልጸዋል።

‹‹የኤሌክትሪክ መኪና ፍላጎት በአሁኑ ወቅት በዓለም ደረጃ እያደገ የመጣበት የራሱ ምክንያት አለው›› ያሉት አቶ ሰጠኝ፤ ይህም ከከባቢ አየር ብክለት ነጻ የሆነን አካባቢ ለመፍጠር ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው ይላሉ። ሌላው በነዳጅ ተጽዕኖ ሥር ያለውን ዓለም ከነዳጅ ተጽዕኖ ማላቀቅ መሆኑን ጠቅሰው፣ ለእዚህም በትኩረት እየተሰራ ነው ብለዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ከታዳሽ ኃይል ኤሌክትሪክን ማምረት በሚችሉ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አገራት የኤሌክትሪክ መኪኖች ቢስፋፉ አዋጭ ነው። በተለይም አገሪቷ ከነዳጅ ጋር ተያይዞ የምታወጣውን ከ40 በመቶ በላይ ወጪም መቀነስ ያስችላታል። በዚህ ሁለት ዓመታት የነዳጅ ዋጋ በከፍተኛ መጠን እየናረ መጥቷል። በየነዳጅ ማደያዎች የሚታዩ ሰልፎችም ከነዳጅ ጋር ያለንን ጥገኝነት ያመለክታሉ።

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ደረጃ በኤሌክትሪክ መኪና ፍላጎት ከቀዳሚዎቹ አገራት ተርታ የምትገኝ መሆኗን የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተሩ አመልክተው፣ መኪና መገጣጠሚያም በዚህ ሂደት ውስጥ እንደ አገር የሚኖረው ድርሻ ከፍተኛ እንደሆነ አስታውቀዋል፤ ለዚህም የመኪና መገጣጠሚያዎቹ ምቹ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ መኪና መገጣጠሚያው በሕዝብ ትራንስፖርት ላይ አተኩሮ እየሰራ ነው ብለዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ኢትዮጵያ ትልቅ የኤሌክትሪክ አቅም ያላት አገር እንደመሆኗ ሕዳሴ ግድብን ጨምሮ ሌሎች የኤሌክትሪክ ማመንጫ ግድቦች አሏት። እነዚህም አገሪቷ ምትፈልገውን የኤሌክትሪክ ኃይል በመስጠት ረገድ ትልቅ ሚና አላቸው። የኤሌክትሪክ ኃይል ለመኪኖች ብቻ ሳይሆን ለፋብሪካዎችና ለአጠቃላይ ኑሮ ያስፈልጋል። ስለዚህ የኤሌክትሪክ መኪኖች ቻርጅ እየተደረጉ የሚሰሩ እንደመሆናቸውና በቀጣይም በብዛት መኪኖቹ የበለጠ ወደ ስራ ሲገቡ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦቱ የተሻለ መሆን ይኖርበታል።

አቶ ሰጠኝ እንዳብራሩት፤ የኤሌክትሪክ መኪኖቹ በሁለት አይነት መንገድ ቻርጅ ይደረጋሉ። አንደኛው ፋስት ቻርጅ የሚባለው ሲሆን፣ ይህም በፍጥነት ወይም ከ30 እስከ 45 ደቂቃ ቻርጅ ማድረግ የሚችል ነው። ሁለተኛው በቤት ውስጥ ቻርጅ የሚደረግና እንደ ሞባይል ረዘም ያለ ጊዜ ወስዶ ቻርጅ ማድረግ የሚያስችል ነው። ስለዚህ መኪኖቹ በሚቆሙበት ቦታ ቻርጅ መደረግ አለባቸው። ለዚህም የኤሌክትሪክ አቅርቦቱ ተደራሽ መሆን ይኖርበታል። መጠቀሙ በነዳጅ ላይ ጥገኛ የሆነን አገር በኤሌክትሪክ ወደሚሰሩ መኪኖችን ስናሸጋግር ለነዳጅ የሚወጣውን የውጭ ምንዛሬ ማዳን ይቻላል፤ ሊወጣ ይችል የነበረውን የውጭ ምንዛሬ ለሌሎች አገልግሎቶች በማዋል ትልቅ አበርክቶ ይኖረዋል።

ኩባንያው የሚያቀርባቸው በኤሌክትሪክ የሚሰሩ መኪኖች ለሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው። ሌሎች በግለሰብ ደረጃ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ በኤሌክትሪክ የሚሰሩ መኪኖች አሉ።

ከ80 ሺ በላይ የኤሌክትሪክ መኪኖች ኢትዮጵያ ውስጥ እንደገቡ የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ መረጃን ጠቅሰው ያብራሩት አቶ ሰጠኝ፤ እነዚህ መኪኖች የኤሌክትሪክ ኃይል የሚያስፈልጋቸው እንደመሆኑ መንግሥት መኪኖቹ ኃይል የሚያገኙበትን መንገድ ማመቻቸት እንዳለበት አስገንዝበዋል።

በላይነህ ክንዴ ግሩፕ የሚያቀርባቸው መኪኖች ከነቻርጀራቸው እንደሚቀርቡ የገለጹት አቶ ሰጠኝ፤ በአማካኝ ለአስር መኪኖች አንድ ቻርጀር እንደሚቀርብም አስታውቋል። ለአብነትም አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለገዛቸው 150 በኤሌክትሪክ የሚሠሩ ሚኒባስ ተሽከርካሪዎች ለአስር መኪኖች አንድ ቻርጀር በድምሩ ከ15 ቻርጀሮች በላይ ከመኪኖቹ ጋር አብሮ ተሰጥቷል ሲሉ አብራተዋል። የኢትዮጵያ ብሮድካስት ኮርፖሬሽንም እንዲሁ አስር መኪኖችን ገዝቶ አንድ ቻርጀር ወስዷል ያለው ዳይሬክተሩ፣ እነዚህ አስር መኪኖች ቢሮ ውስጥ ቻርጅ መደረግ የሚችሉ መሆናቸውን ነው ያስታውቁት።

ዳይሬክተሩ እንዳስታወቁት፤ ድርጅቱ መኪናውን ብቻ ሳይሆን የቻርጅ ችግር እንዳይፈጠር ጭምር ቻርጀሮችንም ያስመጣል። በተለይም በርካታ ቁጥር ያላቸውን የኤሌክትሪክ መኪኖች ለሚገዙ ድርጅቶች ቻርጀሮችን በመኪናው ዋጋ እንዲያገኙ ይደርጋል።

የኤሌክትሪክ መኪኖቹ ያለ ቻርጀር የሚሰሩ ባለመሆናቸው በየአካባቢው የኤሌክትሪክ መኪኖቹ ቻርጅ የሚያደርጉበት ቦታ ሊኖር ይገባል ያሉት አቶ ሰጠኝ፤ አሁን ላይ በ50 ኪሎ ሜትር ውስጥ ቻርጀሮች እንዲኖሩ፣ ነዳጅ ማደያዎች ቻርጀር እንዲኖራቸውና የጋራ መኖሪያ ቤቶችና ተቋማት አካባቢም እንዲሁ ቻርጀሩ እንዲኖር አስገዳጅ ሕጎች እየወጡ እንደሆነም አስታውቀዋል።

ለዚህም ድርጅቱ የኤሌክትሪክ መኪና አቅራቢ እንደመሆኑ በከተማዋ የኤሌክትሪክ ቻርጀር እጥረት እንዳይፈጠር እየሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤ ከትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ስታዲየም አካባቢ አምስት ቻርጀሮችን ለመትከል በራስ ተነሳሽነት እየሰራ ይገኛል ብለዋል።

መኪኖቹ በአገር ውስጥ መገጣጠማቸው መለዋወጫቸውን በቀላሉ ለማግኘት ይረዳል ያሉት አቶ ሰጠኝ፣ በአጠቃላይ የኤሌክትሪክ መኪኖች እንደ አገር ካላቸው ፋይዳ አንጻር በመንግስት ተገቢውን ትኩረት አግኝቶ መሰራት እንዳለበት አስገንዝበዋል።

ድርጅቱ ሥራ ሲጀምር ከባድ የደረቅና ፈሳሽ የጭነት መኪኖችን ይገጣጥም እንደነበር ያስታወሱት አቶ ሰጠኝ፤ ከዚህ ባለፈም በአሁኑ ወቅት የመኪና አካላትን በአገር ውስጥ ማምረት መጀመሩን ነው የገለጹት። አዳዲስ የኤሌክትሪክ መኪኖችንም እንዲሁ በአገር ውስጥ ገላን እና ደብረብርሃን በሚገኙ ሁለት መገጣጠሚያ ፋብሪካዎቹ እየተገጣጠመ መሆኑን አስታውቀዋል። በቀጣይም ከዚህ በተሻለ መንገድ የተለያዩ የመኪና አካላትን በአገር ውስጥ አምርቶ ከሕዝብ ትራንስፖርት በተጨማሪ በግለሰብ ደረጃ የሚያዙትን አውቶሞቢል መኪኖችንም በአገር ውስጥ የመገጣጠም ዕቅድ ይዞ እየሰራ ይገኛል።

ኩባንያው በደብረ ብርሃን የገነባውን የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ መገጣጠሚያ ፋብሪካ ሰሞኑን ማስመረቁም ይታወቃል።

# አብሮነት

ስምስም መንግሥቱ

ጠዋት አንዱ ቤት፣ ማታ ደግሞ ሌላኛው ቤት ከጎረቤት ጋር ቡና መጠራራት በኢትዮጵያውያን የተለመደ:: እንደ ባህልም ተደርጎ የሚወሰድ ነው ብሎ መናገርም:: ጎረቤቱ ብዙ ከሆነም ቡና መጠራራቱ ከሁለት ቤት ያልፋል:: በቡና መጠራራት ወንዶችም አብረው የሚሳተፉ ቢሆንም እናቶች ወይንም ሴቶች ግን ዋነኛ ተሳታፊዎች ናቸው::

የቡና ስነስርዓት፣ የቡና ቁርስ ስላለው በቤት ውስጥ ቁርስ የማይቀመስበት ጊዜ መኖሩ የተለመደ ነው:: አንዳንዶችም በቡና ጠጡ ላይ የሚነሳውን ጨዋታና ሳቅ እንደሚናፍቁ ይናገራሉ::

ከጎረቤት ጋር ቡና መጠራራቱ አብሮነት ያጠናክራል:: ማህበራዊ ትስስሩ ቡና ጠጡ ብሎ ጎረቤት ከሚላኩት ልጆች ይጀምራል:: የሚላኩት ልጆች የነማን እንደሆኑ በጎረቤትም ስለሚታወቁ ልጆቹ ከፋም ደግም ነገር እንኳን ቢያጋጥማቸው የእከሌ ልጅ ነው ወይንም ናት ብሎ ጎረቤቱ ይደርስላቸዋል:: ልጆች ሲላኩ የሚበሉት ነገር ስለሚሰጣቸውም ለመላክ ይሽቀዳደማሉ::

ቡና ጠጡ ብለው ጎረቤት እንዲጠሩ የሚላኩት ልጆችም የተለያየ ሰው ባህሪን ከልጅነታቸው ለማወቅ ዕድል ይሰጣቸዋል:: በዚህ መካከል ልጆች አብሮነትን፣ ማክበርን፣ መተሳሰብን እያዩ ያድጋሉ:: በዚህ መልኩ ከጎረቤት ጋር በሚፈጠር ግንኙነት አብሮነቱ ስለሚጠነክር ልጆች ከሥነምግባር ውጭ እንዳይሆኑ ድርሻው የጎረቤትም ጭምር ይሆናል::

መጥፎ ነገር አይቶ ልጆቹን አያልፋቸውም:: ከመጥፎ ሥነምግባራቸው እንዲመለሱም ጎረቤት ይገስፃል፤ ይቀጣል:: ልጆች በወላጆች ብቻ ሳይሆን በጎረቤትም ጭምር ነው የሚያድጉት:: ልጆቹም አድገው እራሳቸውን ሲችሉ የልጅነታቸውን ጊዜ በጥሩ ትውስታ ነው የሚያነሱት:: የጎረቤቶቻቸውን ውለታ ለመመለስ ጥረት ሲያደርጉም ይስተዋላል:: አንዳንዶችም የድሮውን ጉርብትና በማስታወስ ይጠይቋቸዋል:: በሚችሉት ሁሉ ለማገዝ ጥረት የሚያደርጉ ጥቂት አይደሉም::

እንዲህ ያሉ ማኅበራዊ ትስስሮች አሁን ላይ እንዴት ናቸው? ጭርሱ ነው የጠፋ ነው ባይባልም፤ ግን ደብዝዟል የሚለው ያስማማናል:: አሁን ላይ እንደ ሀገር የገጠመን አለመግባባት፣ ችግሮችንም ተቀራርቦ ለመፍታት ፍላጎት የማጣት ጉዳይ አብሮነትን የሚሸረሽሩ ነገሮች በመፈጠራቸው ምክንያት ነው::

በጉርብትና፣ በጋብቻ፣ በክርስትና፣ በአበልጅነት እየተሳሰርን አዳብረናቸው የነበሩ መልካም እሴቶች ቦታ አለማግኘታቸው፣ አለመግባባቱ፣ አንዱ ለሌላው አለማሰቡ፣ አለመከባበሩ፣ ወንድም በወንድሙ ላይ ቃታ እስከመሳብ የመድረሱ ጉዳይ የማኅበራዊ ግንኙነት እየላላ መምጣትን ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል::

ጎረቤታሞች በአንድ ተሰባስበው ቡና ሲጠጡ በአጋጣሚው የሚያነሷቸው ሀሳቦችም ሆኑ ማኅበራዊ ትስስራቸውን የሚያጠናክሩበት መንገድ እንደዋዛ የሚታይ እንዳልሆነ የነ ወይዘሮ ፋጤና ይመናሹ ግንኙነትም አንዱ ማሳያ ነው:: በሁዳዴ እና በረመዳን አጽዋማት ምክንያት ተቋርጦ የነበረው ቡና መጠራራቱ በቀጠለ ጊዜ ነበር በቡና ሰበብ በተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች ላይ ይጋሩት የነበረው ሀሳብ፣ ሳቅና ጨዋታ እንደቀረባቸው ያስተዋሉት:: በግል ጉዳያቸው የገጠማቸውን ችግር እንኳን ተገናኝተው ሲወያዩበት ትልቅ የሆነ እፎይታን ነው የሚያገኙት:: ከጾም በኋላ እንደቀደመው ቡና እየተጠራሩ የቡና ዋጋቸውን ቀጥለዋል::

ወይዘሮ ፋጤና ይመናሹ ስለ እለት ተእለት ኑሮአቸው መጉደልና መሙላት ብቻ ሳይሆን፣ የተለያዩ ማኅበራዊ ጉዳዮችን፣ ወቅታዊ የፖለቲካ ትኩሳትንም እያነሱ ይጨዋወታሉ፤ ሀሳብ ይለዋወጣሉ:: ጎረቤታሞቹ በሀገሪቱ ውስጥ የሚካሄዱትን ፖለቲካዊ ሁኔታዎችና ሌሎችንም እንቅስቃሴዎች ከመገናኛ ብዙሃን በመከታተል አንዳቻው ለሌላኛቸው ሀሳብ በማጋራት የሚያደርጉት ውይይት ጥሩ መረጃ ሰብሳቢዎች መሆናቸውን ያሳያል::

> **መመካከር ከግለሰብ አልፎ ለሀገር ፍቱን መድሃኒት ነው**

ቡና እየጠጡ ቢጫወቱም ቴሌቪዥን ወይንም ሬዲዮ ስለሚከፍቱ ጆሮአቸውን ጣል ያደርጋሉ:: አንድ ጆሮ የሚስብ ነገር ከገጠማቸው ጨዋታቸውን አቁመው መረጃውን ይሰማሉ:: የሰሙትንም ርዕስ አድርገው ይነጋገሩበታል:: እነ ወይዘሮ ፋጤንና ይመናሹን ለየት የሚያደርጋቸው ለመረጃ የሚሰጡት ትኩረት ነው::

ወይዘሮ ፋጤ ማልደው በመነሳታቸው የጠዋት ቡና ቀድመው ነበር ያፈሉት:: ወይዘሮ ይመናሹም ቡናው ቁርስ ስላለው ቁርስም ለማዘጋጀት ጉድ ጉድ አላሉም:: ወይዘሮ ፋጤና ወይዘሮ ይመናሹ እንደተለመደው የተለያዩ ርእሰ ጉዳዮችን አንስተው እያወጉ ነው:: ግን ሰፋ ያለ ጊዜ ወስደው ሲጨዋወቱ የነበረው አሁን ላይ ‹‹ኢትዮጵያ እየመከረች ነው!!›› በሚለው መሪ ቃል ላይ ነበር::

ሁለቱ ጎረቤታሞች በጋራ የተረዱት ነገር ቢኖር በተለያዩ አካባቢዎች ሰሞኑን የተጀመረው ሀገራዊ ምክክር መድረክ የሁሉንም ዜጎች ሀሳብ በማሰባሰብ አንድ መፍትሄ ላይ ለመድረስ መሆኑን ነው:: በኢትዮጵያ በዚህ ወቅት እየታዩ ያሉ አለመግባባበባቶች ይፈታል ተብሎ ተስፋ የጣለበት የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን በርካታ ሂደቶችን አልፎ አሁን አጀንዳ የማሰባሰብ ተግባር ውስጥ መግባቱን ተረድተዋል::

ወይዘሮ ፋጤ ይህን ርእሰ ጉዳይ ሲያነሱ ወይዘሮ ይመናሹ እጃቸውን ወደላይ በማድረግ ፈጣሪያቸውን ነበር የተማፀኑት:: ምክክሩ ውጤት እንዲያመጣ ነበር የተመኙት:: ኢትዮጵያን በትንሽ በትልቁ ወደ ግጭትና ወደ ጦርነት መግባታቸውና ይህም ለዓመታት መዘለቁ ምን ያህል ሀገርን ያስጨነቀ ጉዳይ እንደሆነም ሀሳብ ሰጡ::

ከልጅነት እስከ እውቀት መልካም ነገር አይተው መኖራቸውን ያስታወሱት ወይዘሮ ይመናሹ፤ ‹‹አንተ ዘርህ ምንድነው፣ ከየት መጣህ ሳንባባል የሰው ልጅ በመሆኑ ነው አብረን የኖርነው:: የነበረው አብሮነታችን ቀርቶ መከፋፈልን ምርጫችን ያደረግነው ለምንድነው›› በማለት በቁጭት ለጎረቤታቸው ሲናገሩ በአንድ አዳራሽ ውስጥ ብዙ ሰው ተሰብስቦ የሚናገሩ ነበር የሚመስሉት::

ሀገራዊ ለውጦች ሲኖሩ አለመረጋጋት፣ ለውጡን ላለመቀበል ማንገራገር የተለመደና ተፈጥሮአዊ ነገር አድርገው ቢቀበሉትም አሁን ላይ የሚስተዋለው ዘርን ማዕከል ያደረገ ነገር የእርስበርስ ግጭት፣ አልፎ ተርፎ ጦርነት ውስጥ እስከመግባት መድረሱ ጥያቄ ፈጥሮባቸዋል::

ወይዘሮ ይመናሹ ንግግራቸውን በመቀጠል እንዲህ ላለው ችግር ምክንያት ነው ያሉትንም ለጎረቤታቸው እንዲህ አጫወቷቸው፤ ‹‹አዎ ዛሬ ሰው እንደድሮ ቡና አብሮ መጠጣቱን እየቀነሰ ነው:: በበዓላት ጊዜም እየተጠራራ አብሮ መብላት፣ መጠጣትና ማሳለፉን ትቶታል:: ይህ ደግሞ ጉርብትናን እያስቀረ በመሆኑ ሰው ለጎረቤቱ ደንታ እንዳይሰጠው እያደረገው ነው›› አሉ::

በተለያየ መንገድ የሚደረገው ማኅበራዊ ትስስር ለአብሮነት ምን ያህል ዋጋ እንዳለው ነበር ያነሱት:: እርሳቸው ይህን ሲሉ ወይዘሮ ፋጤም አከሉበት::‹‹ ልክነሽ ዛሬ ለጎረቤቱ መልእክት የሚላክ ልጅ እንኳን እንደሌለ እያስተዋልን ነው:: በልጆቹም አይፈረድም:: ጎረቤት ሲላኩ፣ ጎረቤቱም ሲያዛቸው ነው በእድሜ የገፉትንም ሆነ ለታላላቆቻቸው መታዘዝና መከባበር ምን እንደሆነ የሚማሩት›› በማለት ሀሳባቸውን አጠናከሩ:: የሁለቱ እናቶች ወግ እንዲሁ ቡና ጠጡ ላይ የተነሳ ተራ ነገር ተደርጎ የሚወሰድ እንዳልሆነ ካነሱት ሀሳብ መረዳት ይቻላል::

ተራ ፀብ ቀርቶ ከባድ የተባለ ችግር በሰዎች መካከል ሲፈጠር እንኳን በአካባቢና በሀገር ሽማግሌዎች፣ ከፍ ካለም የኃይማኖት አባቶች ጣልቃ ገብተው ሰዎች ቁርሾአቸውን እንዲረሱ የሚደረግበትንም ጊዜ በእድሜያቸው ማየታቸውን ያነሱት ወይዘሮ ፋጤ ጉዳዩ በሀገር ሽማግሌ ወይንም በኃይማኖት አባት ሲያዝም ማኅበረሰቡ ትልቅ ቦታ በመስጠት ታዛዥ እንደሚሆንም ነው የገለጹት::

‹‹የአባት ገዳይ እንኳን ታርቆ ቂሙን ያነሳል›› በማለት ከደመኛው ጋር ቂሙን ባይረሳ እንኳን የአባቶችን ትእዛዝ አክብሮ የተባለውን ይፈጽማል እንጂ ለፀብ አይነሳሳም በማለት ነበር በጨዋታቸው ያነሱት:: እንዲህ ያለ መልካም የሆነ እሴት እያለ እዚህም እዚያም ብጥብጥ ተፈጥሮ አንዱ ወደሌላ አካባቢ ለመሄድ እስኪቸገር ድረስ ነገሩ ሥር መስደዱንም እግረመንገዳቸውን አነሱ::

መንግሥት መፍትሄ ያለውን ሀገራዊ ምክክር መድረክ እንዲዘጋጅ ማድረጉን ወይዘሮ ፋጤና ወይዘሮ ይመናሹ በእጅጉ ደግፈውታል:: ወይዘሮ ፋጤ እንደሚሉት ከሀገራዊ ለውጥ ጀምሮ በፊት ኢትዮጵያ ሰላም ርቋት ነው የቆየችው:: በጦርነትም አሸናፊና ተሸናፊ አልታየም:: ይልቁንም የሰው ሕይወት ነው የተቀጠፈው:: ሀብት ንብረት ነው የወደመው:: የሀገር ኢኮኖሚ ወደኋላ አሽቆለቆለ እንጂ እድገት አይደለም የተመዘገበው:: በሰዎች መካከልም ቁርሾና ቂም እንጂ መልካም የሆነ ነገር አልተዘራም:: አንዱ ሌላውን እንደጠላቱ እንጂ እንደወገኑ እንዲያየው አልሆነም::

ይሄ ከፋ የሆነ መንፈስ በመሆኑ ሊቆም ይገባል:: ይህን ማድረግ የሚቻለው ደግሞ ሰዎች በችግሮቻቸው ዙሪያ መክረውና ዘክረው የጋራ የሆነ መፍትሄ ማምጣት ሲችሉ ነው:: መመካከር ከግለሰብ አልፎ ለሀገር ፍቱን መድሃኒት ነው::

ወይዘሮ ይመናሹም በሀሳባቸው ይስማማሉ:: እርሳቸውም የተፈጠሩት ችግሮች መፍትሄ ሳያገኙ መራዘመቻው በእነርሱ የእለት ተእለት ኑሮ ላይ እንኳን ያሳደረውን ጫና በቀላሉ በምሳሌነት አንስተዋል:: ኢትዮጵያ ካላት የሰው ኃይል ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዘው ወጣት ዛሬ ስራ ይፈልጋል:: ከእራሱ አልፎ ቤሰተቡን መርዳት ይሻል:: ይህ የሚሆነው ደግሞ ሰላም ሲኖር ነው:: ወጣቱ ከጥንት ጀምሮ በጦርነት ውስጥ ማሳለፉ በእውቀቱና በጉልበቱ ለሀገር ሊያበርክት የሚችለውን መልካም ነገር እንዳያሳልፍ አድርጎታል::

ሀገራዊ ምክክሩ ይህን ዘመን የተሻገረ ችግር ለመቅረፍ እንደሚያስችልም ሁለቱም እምነት ጨብጠዋል:: በተለይም ወጣቱ ነገን በተሻለ እንዲመለከት እንደሚያስችለው ተስፋ ሰንቀዋል::

ሆኖም አንዳንድ ወገኖች ከራሳቸው ጥቅም በመነሳት የሀገራዊ ምክክሩ እንዳይሰምር ሲጣጣሩ መመልከታቸው ስጋት ፈጥሮባቸዋል:: ‹‹ሳይቃጠል በቅጠል›› እንዲሉ ለችግሩ ከቀወዲሁ መፍትሄ ማበጀት ካልተቻለ ሀገር ተረካቢ፣ ለሀገር እድገት የሚያስብና የሚቆረቆር ትውልድ እንዳይኖር የሚያደርግ ነገር እንዳይፈጠር ነው ስጋታቸውን የገለጹት::

ወይዘሮ ፋጤና ይመናሹ በውይታቸው ያነሱት የነበረው ሀሳብ ጠንከር ያለ ነበር:: እነዚህ እናቶች በሀገራዊ ምክክር መድረክ ላይ የመሳተፍ እድል ቢያገኙ ብዙ ሀሳብ እንዳላቸውም ከውይይታቸው መረዳት ይቻላል:: ወይዘሮ ፋጤና ወይዘሮ ይመናሹ ያነሱትን ሀሳብ በፀሎት ነበር የደመደሙት::ሀገራዊ ምክክሩ ውጤት እንዲያመጣ ትልቁ ምኞታቸው ነው::

ሰዎች በአንድ አዳራሽ ውስጥ ተሰባስበው የሚያደርጉት ውይይት ብቻውን በቂ እንዳልሆነ ያምናሉ:: ሁሉም በየእምነቱ ፀሎት በማድረግ የተጀመረው በጎ ነገር እንዲሳካ ማሰብ እንዳለበት ነው የሚስማሙት:: እነርሱም መልካም ምኞታቸውን ተመኝተው ወደ የእለት ተግባራቸው ተመለሱ::

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

## ከፊልሞቻችን ማጀት

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

ፊልምና የፊልም ጥበብ ከሀገርኛ አገልግል ውስጥ ሲበሉት ይጣፍጣል። መዓዛውም ያስጎመጃል። ከዚያ በፊት ግን ማጀቱንም ማየት ያስፈልጋል። ምስጋና ለፊልም ጠቢባኑ ይግባና አመስግነን ወደ ጎደለው ስንክሳር ውስጥ ልንገባ ነው። ጥሩ ነገሮች እንዳሉ ሆነው ለበለጠ ጥሩነት የጎደለንን ፍሊጋ ከኢንዱስትሪው ማጀት ስንገባ ለምን የሚያስብሉን ጉዳዮች ለጉድ ናቸው።

ከማጀቱ ከተያዘው የጥበብ አገልግል ውስጥ ላለው ለወጡ ጥፍጥና የጎደለው ከምኑ ላይ ነው? ከባለሙያው ወይንስ ከግብአት እጥረት? እንደ አንድ የፊልም ጥበብ ወዳጅ ሲያስደስቱን እጅ ስመን ሲያጠፉ ደግሞ እጅ ይዘን ከገባን ላይ ስናሳይ ለኢንዱስትሪው በሁለት እግር መቆም የሚገባንን እያደረግን ነው። ብዙውን ጊዜ ግን ከትችትና የማብጠልጠል ስሜት ሳንላቀቅ በግራ ነው የምናደርገው።

ትችት በወግ ወጉ ሲሆን ጥሩ መስመሮችን ያሰምርልናል። በግልም ሆነ በጋራ ውስጥ ውስጡን ከማንሾካሾክ ከሂሳዊ የቅንነት እሳቤ ጋር በግልጽ አውጥተን ብንማከርባቸው ኖሮ እስካሁንም ለመፍትሄዎች ባልዘገየንና በረሀውም በለመለመ ነበር። ከብዙ የሀሳብ ቃታ ትንሷን የጥበብ ጠብታ የለውጥ አድማስ ትሆናለች።

ከፊልም ወዳጆች የጎደለን ነገር ቢኖር በትችት የምናሳጣውን ያህል በሀሳብ ማዋጣቱ ላይ አለመኖራችን ነው። ስለ ፊልሞቻችን በተነሳ ቁጥር እንደ ሀሜት ጓዳ ጓዳውን ብቻ የሚያሳልጠው ብዙ ሆኖ ሳለ፤ እንዲህና እንዲያ ቢሆን እያሉና ከችግሩ ነቅሰው ከመፍትሄውም የሚያመላክቱ ግን ጥቂቶች ናቸው። ከፊልሞች ዳሰሳ ይልቅ ለአዳዲስ ሀሳብ አሰሳ መውጣትም ወሳኙ ነጥብ ነው። የፊልም ኢንዱስትሪውን ከፍ ለማድረግ ስናስብ ሁልጊዜም ጥቃቅን ከሚመስሉ ጉድለቶቻችን መጀመር ይኖርብናል፤ ነጠብጣቦች አንድነትን ፈጥረው እንከኖቹን ወደ አራት ነጥብነት ሳይቀይሩት።

ፊልም የማኅበረሰቡ የፊት መስታየት ነው እንላለን፤ ነገር ግን ፊልሞቻችንና ማኅበረሰቡ በቅጡ ይተዋወቃሉ? አንድም ከፊልም ኢንዱስትሪው ሁለትም ከማኅበረሰቡ ሁላችንም ከአንደኛው ጋር አንድ ነገር አጉድለናል። ከሁለት አቅጣጫ የሚሰነዘር ቡጢ እያረፈበትም ይመስለኛል።

እንደ ማኅበረሰብ ጫናው በዝቶበታል፤ ጥላቻ ባይኖርበትም በማኅበረሰቡ ውስጥ በነጻነት የመዘዋወሩ ጉዳይ ግን አጠያያቂ ነው። ከማኅበረሰብ አንጻር በሁለት ነገሮች የበደልነው ይመስለኛል። አንደኛ፤ ፊልሙ የወጣቱ ክፍል ብቻ ተደርጎ ከመቆጠሩም በአንዳንዱ ዘንድ እንደ አደንዛዥ እጽ መታየቱ ነው። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ፤ ለፊልሞች ያለው አመለካከት ለመዝናኛ ጥቅም ብቻ መዋሉ ይሆናል።

ፊልሞች የማኅበረሰቡ ነጸብራቅ ናቸው ካልን ታዲያ ማኅበረሰብ ማለት የወጣቱ ክፍል ብቻ ነው? በእድሜ የገፋው ክፍል ፊልምን መመልከት ሥራ እንደመፍታት ከመቁጠሩም የክብር ሚዛንን የሚቀንስም ሆኖ ይታያል። ታዲያ የላይኛውን ኅብረተሰብ ያማከሉ ፊልሞች ስለማይሰሩ ወይንስ እነርሱ እንደሚሉትም አላስፈላጊ ነገር ሆኖ ነው? በእርግጥ ባህላችን ቁጥብነት የበዛበት ከመሆኑ የተነሳ ወደ ማኅበረሰቡ የሚወስዱን አብዛኛዎቹ መንገዶች ዝግ መሆናቸውም አይጠፋንም።

ባህል አክባሪነት ከፊልም አያግደንም የበዛ ወግ አጥባቂነት ግን መፈናፈኛ ፋታም አይሰጡንም። ለሁሉም ነገሮች መጀመሪያው የግንዛቤ እጥረት መሆኑ ይታወቀናል። ከቤታቸው ቁጭ ብለው ድራማዎቹን የሚከታተሉ ነገር ግን ፊልም ሲባል ጥሩ ነገር የማይታያቸው ሰዎች በግሌ ገጥመውኛል። ከራሳቸው አልፎ ልጆቻቸውም ጭምር ፊልም የሚባል ነገር እንዳይመለከቱ የሚመክሩ ብዙ ወላጆችም አሉ።

እንዲህ አይነቶቹን ክፍተቶች አጥበን ከማኅበረሰቡ ጋር የምንገናኝበትን መስመር መቅደድ ይኖርብናል። ለማኅበረሰብ ተብሎ የሚሠራው ፊልም በየአጥሩ እየተንጠላጠለ የአይጥና የድመት ጨዋታ እየተጫወተ እስከመቼስ ሊዘልቅ...ወጣም ወረደም ያለውን ተቀባይነት ለማሳመር ካልቻለ ያለማኅበረሰቡ ኢኮኖሚያዊም ሆነ ምንም ዓይነት ለውጥ ለማምጣት አይችልም። በመሀከል የተፈጠረውን ፍራቻ በማስወገድ እራሱን የሚያይበትን የፊት መስታየት የመሰለ ፊልም ሥርተን ልናሳየውና ልናሳምነው ይገባል። ፊልሙን ለማነቃቃት ማኅበረሰቡን




ማንቃት ትልቁን ሸክም እንደማቅለል ነው።

ሁልጊዜም በየትኛውም ቦታና ማኅበረሰብ ውስጥ ፊልሞቻችን ለትውልዱ የመዳኛ መንገድ እንጂ የሞት መንኩራኩር ተደርገው መቆጠር የለባቸውም። አንዳንዴም የፊልሙን መልክ የሚያጠለሹት ቅጥ አልባ ግብርና እይታዎች ናቸው። ባህል ጥሶ ወግና ሥርዓትን ፈንቅሎ ማነውስ ተመልካቹ? መጽሐፍ ተመርጦ ይነበባል፤ የፊልምን ይዘት መምረጥ ግን የፊልም ባለሙያዎችም ኃላፊነትም ጭምር። ምክንያቱም ተመልካች ሁል ጊዜም እንደ ሕጻን ልጅ ነው፤ ድጋፍን ይሻል። ሁሉም ትዕይንቶች ለሁሉም አይቀርቡም፡፡

የሀገር ውስጥ ፊልም መመልከት የማይወደውን ወዳጃቹን ጠጋ ብላችሁ ለምንድነው? ያላችሁት እንደሆን የሚሰጣችሁ ምላሾች ተመሳሳይና ከብዙዎች የሰማችሁትን ዓይነት ነው። "ኤዲያ! ደግሞ የኢትዮጵያ ፊልም...ገና ፊልሙ ሲጀምር ሳላይ ከደራሲው እኩል ታሪኩን አውቄ ጨርሰዋለሁ።

መዋደድ...መጣላት እና መታረቅ..." ይላችሁ ይሆናል። በእርግጥ አሁን አሁን በቆንጆ የታሪክ ፍሰት ያማሩ ፊልሞችን ለመመልከት ብንችልም ነገሩን ግን ከእውነትነት የምናርቀው አይደለም። በፊልሞቻችን ውስጥ ያለው የተዋናይ መረጣስ? አንዳንድ ጊዜማ ለፊልሙ ታሪክ የሚሆን ተዋናይ ሳይሆን ለተዋናዩ የሚሆን ታሪክ የምንመርጥ ነው የሚመስለው። ትናንት በአንደኛው ፊልም ጎበዝ አባት ሆኖ የተወነው ሰው ሁሌም አባት ነው።

በኢትዮጵያ ፊልሞች ውስጥ የጨካኝነትና አስፈሪ ገጸ ባህሪያትን የሚጫወቱ ሰዎች በተለይ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ተሰፍረውና ተለክተው የተቀመጡ ተዋንያን አሉ። አስፈሪነትና ጭካኔን ባስታወሰን ቅጽበት ድቅን የሚልብን የጥቂት ሰዎች ፊት ነው። ሌላው ቀርቶ በአንደኛው ፊልም የበር ጠባቂ የነበረው ሰው የእውነትም እስኪመስለን በቀጣይም የምናገኘው እዚያው በር ላይ ይሆናል። ይህ እንግዲህ ተዋናይ መረጣ ላይ የሚሰሩ ባለሙያዎች ፍሊጋን የመሰልቸት ስንፍና አሊያም እይታ የመድገም አባዜ ነው። አንድ ቀን ከታክሲው ውስጥ ያነበብኩትን ቀልድ ቢጤ አሽሙር ትዝ አለኝ። እንዲህ የሚል ነበር፤ "የኢትዮጵያ ፊልሞች በሁለት ይከፈላሉ፤ እነርሱም እንትና ያለበትና የሌለበት" በማለት የአንድ ተዋናይ ስም ተጠቅሶበታል። ለማሳቅ የተጻፈ ቀልድ ቢመስልም የፊልም ባለሙያዎቹ ግን እንዲያስቡበት የሚያደርግ ነው።

በአንድ ሰሞን በሚወጡ ፊልሞች ውስጥ ተከታታይ ድራማ እስኪመስል ድረስ ተደጋግሞ የሚታየው የአንድ ሰው ፊት ነው። የፈለገውን ያህል ከሌላው በተሻለ ቢተውነውም ከዛ በበለጠ የፊልሙን ተአማኒነትና ውስጣዊ ኃይል ይቀንሰዋል። "ማርም ሲበዛ..." የምትለዋን ሕገ ደንብ ቢያደርጓት ጥሩ ነበር፡፡

የመገናኛው መንገድ ለምን ጠበብ? ካሉ የሚያነሷቸው እልፍ ነጥቦች አሉ። አንዳንዶቹ ነጥቦች ጠባሳም ፈጥረዋል። ከሀገራችን ፊልሞች እርቆ በባህር ማዶ ለከረመውም አይፈረድበትም እንድንል የሚያደርጉም አሉ። ስንት ሕብረ ብሔራዊ ባህልን ከታሪክ እንዲሁም ከተፈጥሮ ስነ ምህዳር ጋር በታደለች ሀገር ውስጥ የፊልሞቻችን መቼት አብዛኛዎቹ ከአንድ ወንዝ በቀር አይሻገሩም። ሌላውስ ይቅር፤ ፊልሞቻችን ሲጀምሩ ለማልበሻነት የምንጠቀመው ምስል ምንድነው? የአዲስ አበባ መከረኛ ሕንጻዎች ናቸው። ፊልሙን ልንሠራባቸው ባንችል እንኳን ቢያንስ ለማልበሻው ከታሪካዊ ስፍራዎች ብንጀምር አንድ ጥሩ ነገር ነው፡፡

በፊልም ውስጥ የቦታ መረጣ (ሎኬሽን) የፊልሙ ዋነኛ ውበት ነውና የራሱ የሆነ ባለሙያ አለው። ችግሩ ግን ለገንዘብ ቁጠባ እየተባለ አብዛኛዎቹ ከአዲስ አበባና ከዙሪያዋ በስተቀር የሚታያቸው ነገር የለም። 80 ፐርሰንት ያህሉ ማኅበረሰብ በገጠር ገጥሮ ሳለ ከግማሽ በላይ ፊልሞቻችን የሚሠሩት በከተሜነት ውስጥ ባለ በቅንጡ የአኗኗር ዘዬ ውስጥ ነው። ያ ሁሉ የአኗኗር መልኮች ክንፋቸውን ዘርግተው በጣት የሚቆጠሩት ብቻ የሚኖሩትን ኑሮ መደጋገምን ምን ይሉታል...አንድ ቀን በአጋጣሚ ካገኘሁት ሰው ጋር ስለዚሁ አንስተን ስንጨዋወት፤ ለፊልም ሥራ ተብለው የሚከራዩ ውስን ቪላና ቅንጡ መኪናዎች እንዳሉ ከነገረኝ በኋላ፤ በብዙ ፊልሞች ውስጥ አንድ ዓይነት ቤት ከአንድ ዓይነት መኪና ጋር የምንመለከተው ለዚሁ ነው አለኝ። ነገሩ ክፋት ባይኖረውም ለማኅበረሰቡ ግን ቅንጡ መኪናና ቪላ ከመመልከት ይልቅ የራሱን ደሳሳውን ጎጆና ጋሪ ቢያይ ይመርጣል።

ሁልጊዜ ያልኖሩትንና የሌለውን ከመሙላት ትንሽም ቢሆን ካለችው ላይ መቅዳት ይሻላል። ከራሱ ኑሮ እንዲማር ከማድረግ ይልቅ በሌላው እንዲጽናና ማድረጉ አይበልጥም። ኑሮ ወዲህ ማዶ ፊልሙ ወዲያ ማዶ ከሆነ ምን ሊረባ...እንዲህ ብቻ እንሥራ አይደለም፤ እንዲህም መሥራት እንዳለብን እናስብ ነው።

እርምትን የሚሹ የታሪክና የማንነት ውክልናዎችንም እንመለከታለን። ይህኛውን ነጥብ ተመልካቹም ሆነ ባለሂሱ ልብ ያላለው አሊያም አምኖ የተቀበለው ይመስላል። ለአብነትም የባላገር ገጸ ሰብና መቼት አንዱ ነው። ሙሉ ለሙሉ ለማለት በሚያስደፍር መልኩ ባላገርና ባላገርነት የሚገለጹት በአንድ ዓይነት መንገድ ነው። አለባበስና የቋንቋ አጠቃቀሙ ጭምር ከአንድ አካባቢና ማኅበረሰብ ጋር ብቻ ተጣብቆ የሙጥኝ ብሏል። አብዛኛው የማኅበረሰብ ክፍል ከባላገርነት ጋር ተቃቅፎ በሚኖርባት ሀገር ውስጥ፤ ባላገሩ በአንድ ውክልና ብቻ ማስቀረት ማንነትን ማራቆት ይሆናል። ይህ ብቻም ሳይሆን የጋራ መሆን የነበራቸው እሴቶቻችንም ከአንደኛው ጋር ብቻ በማያያዝ በፊልም ደረጃ መንጸባረቅ የሌለባቸው ጉዳዮችን እንመለከታለን፡፡

አንድን ባህል እንዲዳብር አድርጎ ማውጣቱ መልካም ሆኖ ሳለ በዚያው ልክ ደግሞ ጥንቃቄ የሚሹ ናቸው። እንዲህ ዓይነት ነገሮች ውለው አድረው ነገ ላይ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ መፍጠራቸው አይቀርም። ስንቱን ሕብር አዋህዳ በያዘች ሀገራችን ውስጥ ያሉትን ልዩ ልዩ ባሕልና እሴቶች እንኳንስ ለመደጋገምና ሠርቶ ለመጨረስ እንኳ ተዝቀው የማያልቁ ናቸው። ፊልም ማለት የማኅበረሰቡ የፊት መስታየት እስከሆነ ድረስ ባለሙያዎቹ መገኘት ያለባቸው እታች ነው።

ሁሌም አዲስ ነገርና አዲስ እይታ ለሚፈልገው ተመልካችም ስንቁ ከወዲያና ወዲያ ብቻ ነው። ከሚጠይቀው የአቅምና ከገንዘብ ሁኔታ ብቻ በመነሳት በኢንዱስትሪውም ሆነ በማኅበረሰብና ተመልካቹ ላይ በድግግሞሽ መፍረድ የለብንም። አንዱን ምስር በቀይ በሀልጫ እያደረጉ ቢወጠውጡት ያው ምስር ወጥ ነው፤ ለመልክ እንጂ ለሰውነት የተመጣጠነ ሊሆን አይችልም።

የኢትዮጵያ ፊልሞች የችግር ነጠብጣብ መጠንና ደረጃው ከፉ በማለት ከበርሜል የሚፈስባቸው ቦታዎችም ብዙ ናቸው። ከወደ መንግሥት በፊልም ቁሳቁስ ላይ የሚጣለው የግብር ጫና ሳያንሰው እዚሁ በዚሁ ደግሞ እንግልቶች ይስተናገዱበታል። በቀረጻ ወቅትም ያለው ደጅ ጥናት እንኳን ቀላል አይደለም። ፊልም ሠሪዎቻችንም ካለባቸው የገንዘብ እጥረትም ሆነ የምልከታ ጥራት ታሪክና ታሪካዊ ስፍራዎችን መጠቀም አዳጋች ሲሆን ይስተዋላል። ተመልካቹም ቢሆን የራሱን ጎራ የያዘ ነው የሚመስለው፡፡

ፊልም ግን የሚሠራው ለገንዘብና ተዝናኖት ብቻ ነው? የፊልም ባለቤቶች መሥራት ያለባቸውን ሠርተው ይክሰሩ አይባልም፤ ግን ደግሞ እንደ ቡና ንግድ ጥበብ በአህያ ተጭኖ ገበያ አይወጣም። ለሀገርና ለዘርፉ፤ ለታሪክና ኪነ ጥበብ መስዋዕትነት ለመክፈል ካልተቻለ ቢያንስ በእኩል ሚዛን ላይ ማስቀመጥ ያስፈልጋል። ከላይ ያነሳነው በየፊልሞቹ ውስጥ ተደጋጋሚ ፊት የመመልከት ችግር የሚመጣው አንድም ከዚህ የነጋዴነት መንፈስ የሚመነጭ ነው። አንዳንድ ጊዜ ከታሪኩ በላይ የምንወደው ታሪኩን የሚነግረን ሰው ሲሆን እንመለከታለን።

የሚወዱት ተዋናይ የሚተውንበትን ፊልም መምረጥ በየትኛውም ዓለም የፊልም ኢንዱስትሪ ውስጥ ያለ ቢሆንም አንዳንዶቻችን ጋር ደግሞ የበዛ ነው። አብዛኛዎቹ ሠሪዎችም ይህን የስነ አዕምሯዊ የፊልም ስበትን ስላወቁበት ይመስላል፤ በየፊልሞቻቸው ውስጥ ከፊት የሚያቆሙት ተወዳጅና ታዋቂዎቹን መሆኑ።

ከብቃቱ ጋር ኩርምት ብሎ የአንድ ቀን እድልና አጋጣሚውን የሚጠባበቅ ስንቱን ታዋቂ ማድረግ ስንችል አንዱን ይዞ እንደ ዳዊት መድገም ከንቱ ነው። ገና ለገና ተመልካች የሚወደውና ትርፍ የሚያስገኝበት መንገድ ነው ተብሎ በሰርጥና ሰንበሌጥ ውስጥ መሯሯጥ ለዘርፉ ጥበብ መዘዝ አለው። በፊልም ውስጥ ተመልካች ወሳኙ ነገር ቢሆንም፤ የደንበኛን ፍላጎት ብቻ መሠረት አድርጎ ማቅረብ ለሸቀጣ ሸቀጥ እንጂ ለፊልሙ ኢንዱስትሪ አይሆንም። ተመልካች ወደ ፊልም ይመጣል ወይንስ ፊልሙ ነው ወደተመልካች የሚሄደው? ተመልካችን ፍሊጋ ሰዶ ማሳደድ ከተያያዝንማ ብዙ መወላገድ ያመጣል። ነገሩ የሚያስፈልግ ቢሆንም ዘለቄታዊ ግን አይሆንም፡፡

በአንድ ሰሞን አብዛኛው ተመልካች የሚወደው እያፈቀረ መሳቅ ነው አሉ። እናም በዚያ ሰሞን የሚሠሩ ፊልሞች ሁሉ 'ሮማንቲክ ኮሜዲ' ነበሩ። ለምን ሲባል፤ ትራጄዲ የሆነ ኑሮ እየኖሩ ትራጄዲ ፊልም መመልከት በቃን የተባለ ዓይነት ድባብም ነበረው። የተመልካቹ ፍላጎት ወደ 'ሮማንቲክ ኮሜዲ' ማዘንበሉ ለዚህ ብቻም ሳይሆን በትራጄዲው ውስጥ ተመልካችን ይዞ ማቆየቱ ትልቅ ሙያዊ ብቃትን የሚጠይቅ መሆኑ ነው። ከማሳቅና ከማዝናናት ይልቅ እያስተማረ ገንቢነቱና ታሪክ ነጋሪነቱ ይጎላል። ታዲያ ይህን አጣፍጦ ተመልካቹ እንዲወደው ሳቢ ለማድረግ ካልቻሉ ከሁሉ ከመውጣት ቢያንስ ስቆ መዝናናቱን ይመርጣል።

ተመልካቹን ማስከተል የነበረበት የፊልሙ ማኅበረሰብ፤ ተመልካቹን ተከትሎ ሄደ። ከባለሙያው እስከ ተመልካቹ ድረስ የአንድ ዓይነት የድግግሞሽ አባዜ የተጸናወተንም የዚህን ጊዜ ይመስለኛል። ታሪካዊ ሳቅ ስቀን ታሪካዊ የሆነ ፍቅርም ተመልክተን ይሆናል፤ ታሪካዊ የሆነውን ማንነታችንን እንድንመለከት ያደረገን ግን አይመስለኝም። በዚህ ዓይነቱ ፊልሞች ላይ መጠመዳችን ሌላኛውን ጎን ቢያዳክመውም በተናጠል ግን ስኬታማ ነበር። ምክንያቱም እንደ 'ሮማንቲክ ኮሜዲ' ዓላማ፤ ተመልካቹ ተዝናንቶ የፊልም ባለቤቶችም የሚፈልጉትን አግኝተውበታል።

እኚህን መሰል ስንክሳሮችና መሰሎቻቸው ተደማምረው በመጨረሻም የፊልም ኢንዱስትሪውን ባይተዋር አድርገውታል። መቅደስ እንደገባ ውሻ ከየአቅጣጫው ሲያበራዩት መገኘት ከነበረበት ሙክራቡ ደንብሮ ጠፍቷል። ከፍትፍቱ ፊቱ ነውና ባናደርግለት እንኳን ቢያንስ ፊት አንንሳው። ከመዝናናት ያለፈ ቁም ነገር እንድናገኝበት ጆሮና ዓይን ሰጥተን ትኩረታችንን እንቸረው። ማጀቱን ባንሞላው እንኳን አናጉድለው። እኚህ ሁሉም ያነሱና የተጨመሩ እንጂ የፊልሞቻችን መልኮች ናቸው ማለት እንዳልሆነ ግን አንርሳ፡፡

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## የህልውና ስጋት ያንዣበበት ማህበር

**እየሩስ ተስፋዬ**

አቶ አስተራየ እንየው የሚኖሩት አዲስ አበባ አብነት አካባቢ ነው። የተስፋ ለዓይነ ስውራንና የአካል ጉዳተኞች ማቋቋሚያ ማህበር አባል ሲሆኑ የቤተሰብ ኃላፊና የሰባት ልጆች አባትም ናቸው። እይታቸውን ማጣታቸው ወፍራም ስጋጃ ጥንቅቅ አድርጎ ከመስራት አላገዳቸውም።

አቶ አስተራየ ዓይነ ስውራን እና ሌሎች የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች ከምንጣፍ በተጨማሪ ሌሎች ምርቶችን አምርተው ተጠቃሚ እንዲሆኑ የተቋቋመው ማህበርን ከተቀላቀሉ አርባ ዓመት ደፍነዋል። ወትሮውም ቢሆን ትንሽ የነበረው ደመወዛቸው አሁን ጭራሹን ቆሟል። እርሳቸው እና ሌሎች ባልደረቦቻቸው ከተከፈላቸው ስድስት ወራት ተቆጥሯል። ‹‹ለምን?›› ቢባል ማህበሩ የሚያመርተውን ምርት የሚገዛው አካል ባለመኖሩ ነው። የግብአት እጥረት መኖርም የማህበሩን ህልውና ካደከሙ ምክንያቶች ውስጥ ይጠቀሳል።

‹‹የኑሮ ውድነቱንና ሌሎች ምክንያቶች ተደማምረው በእኛ ላይ እንቅፋት ፈጥሯል›› የሚሉት አቶ አስተራየ፤ ደመወዝ እንደማይከፈላቸው እያወቁ እንኳን የማህበሩን ደጃፍ መርገጥ እንዳላቆሙ ይናገራሉ። ሥራ ከመፍታት እና ቤት ከመዋል ብለው ያገኙትን ሠርተው ወደ ቤታቸው እንደሚሄዱም ያስረዳሉ። ‹‹እቤት ላለመዋል ብለን ስንገላታ ውለን ነው ወደ ቤት የምንሄደው፤ ችግር ላይ ወድቀናል›› ሲሉ የደረሰባቸውን ችግር ያስረዳሉ።

እርሳቸውን ጨምሮ አብዛኞቹ የማህበሩ አባላት ሁለገብ ባለሙያም ናቸው። አቶ አስተራየም ብሩሽ፣ መጥረጊያ፣ መወልወያ ምንጣፍ እና ሌሎችንም በሚገባ ይሠራሉ። ከአብነት ስድስት ኪሎ ድረስ በመመላለስ ‹‹ነገ የተሻለ ይሆናል፡፡›› በማለት በተስፋ ወደ ማህበሩ ቅጥር ግቢ ዘወትር ይመላለሳሉ፡፡

አቶ አስተራየ መንግሥት በጀት መድቦ ድጋፍ ቢያደርግ ችግሩን እንደሚያቃልል ይናገራሉ። የሚያመርቱትን ምርት የሚሸጡበት ቦታ እና ሁኔታ ቢያመቻች መልካም እንደሆነም ይጠቅሳሉ። ግለሰቦች፣ የረድዔት ድርጅቶችና ሌሎችም ምርቶቻቸውን



**ማህበሩ 153 አባላት የነበሩት ሲሆን እንደልብ እየተንቀሳቀሰ ባለመሆኑ የአባላት ቁጥሩ በእጅጉ እየተመናመነ መጥቷል፤**

በመግዛት የቻሉትን ያህል ትብብር እንዲያደርጉም ይጠይቃሉ።

ማህበሩ ለአቶ አስተራየ ብዙ ነገራቸው ነው። በቂ የሚባል ገንዘብ ባያገኙበትም ሰው አትርፈውበታል። ከጓደኞቻቸው ጋር ያሻቸውን ተጫውተው ተደስተው እና የሆድ ሆዳቸውን እንዲያወጉ ዕድል ሰጥቷቸዋል። ይሁንና በአንድ ነገር ቅር መሰኘታቸው አልቀረም። እርሱም ለአካል ጉዳተኞች የሚሰጠው ትኩረት አናሳ መሆን ነው። በዚህ ችግር ሳቢያ በርካታ ማህበራት ለመዘጋት ጫፍ ላይ ደርሰዋል። ዛሬም ግን አልረፈደም፡፡

‹‹ አይዟችሁ የሚለን የለም። ቢቻል በገንዘብ ካልሆነም በሞራል አይዟችሁ ማለት ራሱ አንድ ድጋፍ ነው። በተጨማሪም የገበያ ትስስሮችን በመፍጠር እና በቂ ትኩረት በመስጠት አደጋ ላይ ያሉትን ማህበራት መታደግ ይገባል፡፡›› ይላሉ አቶ አስተራየ።

ወይዘሮ አየሁሽ ብላታ እንደ አቶ አስተራየ ዓይነ ስውር ናቸው። ማህበሩን የተቀላቀሉት ገና በአፍላ ዕድሜያቸው እንደሆነ ይናገራሉ። እርሳቸውንም ከሙያ ባልደረቦቻቸው ጋር ምንጣፍ ሲሰሩ ነበር ያገኘናቸው። የተቀጠሩበት ደመወዝ ክፍያው ትንሽ ቢሆንም ወቅቱ የኑሮ ውድነት ያልፈተነው ወቅት ነበርና በቂያቸው እንደነበር ያስታውሳሉ። አራት ልጆቻቸውንም በሚገባ አሳድገውበታል፡፡

ዛሬ ግን ማህበሩ ችግር ላይ በመሆኑ ደመወዝ እየከፈላቸው አይደለም። ቤት ከመዋል ብለው በማህበሩ ያገኙትን ሰርተው ወደ ቤታቸው ያቀናሉ። የጥሬ ዕቃ አለመኖር እና የገበያ እጥረት መኖር ማህበሩ ችግር ውስጥ እንዲዘፈቅ ማስገደዱንም አያይዘው ይገልጻሉ፡፡

ወይዘሮ አየሁሽ መንግሥት ቢደርስልን፤ እንዲሁም ድርጅቱ የጥሬ ዕቃ ድጋፍ ቢያገኝ እና በሙያ የሚያግዝ ሰው ቢገኝ ችግሩን መቅረፍ እንደሚቻል ይገልፃሉ። መጪው ትውልድ ምን ችግር እንደሚገጥመው አይታወቅም ያሉት ወይዘሮዋ፤ ማህበሩ ለመጪው ትውልድ የሚተርፍ ሊሆን ይችላልና ሁሉም ለራሱ ሲል የቻለውን ድጋፍ ቢያደርግ መልካም እንደሆነ ይናገራሉ፡፡

አቶ ዮሐንስ ግደይ የተስፋ ለዓይነ ስውራንና የአካል ጉዳተኞች ማቋቋሚያ ማህበር ሥራ አስኪያጅ ናቸው። እንደ እርሳቸው ገለፃ፤ ማኅበሩ የአካል ጉዳተኞችን ደህንነት ለማስጠበቅና መብታቸውን ለማስከበር ዓላማ ይዞ በ1972 ዓ.ም በድጋሚ ደግሞ በ1992 ዓ.ም ነበር የተቋቋመው። በዚህ ማህበር ዓይነ ሥውራን ብቻ ሳይሆኑ ሌሎች ጉዳት ያለባቸውም እንዲካተቱ ተደርጓል። ይህ ማህበር 153 አባላት የነበሩት ሲሆን፤ እንደልብ እየተንቀሳቀሰ ባለመሆኑ ዛሬ ላይ ወደ ድርጅቱ የሚያቀኑ አባላት ቁጥር በእጅጉ እየተመናመነ መጥቷል።

እንደ ምንጣፍ፣ የተለያዩ የስጋጃ አይነቶች፣ መጥረጊያ፣ ብሩሽ፣ መወልወያ እና ሌሎች ምርቶችን ዓይነ ስውራኑ እና ሌሎች አካል ጉዳት ያላቸው አባላት የአቅማቸውን እንዲሁም የፍላጎታቸውን ያህል እንዳይሠሩ የጥሬ ዕቃ እጥረት እንዲሁም የገበያ ትስስር ትልቅ እንቅፋት ሆኖባቸዋል። አባላቱ ደመወዝ ከተከፈላቸው አምስት ወራት ማለፉን የሚገልፁት፤ አቶ ዮሐንስ አሁን ላይ ለትራንስፖርት ብቻ ተብሎ ከሚሰጣቸው ገንዘብ ውጪ ምንም የሚያገኙት ገቢ የለም። እንደውም አንዳንዶቹ አካል ጉዳተኞች ከሥራ ገሸሽ እንዲሉ ተገደዋል።

ከዚህ ቀደም ድጋፎችን ከውጭ ድርጅቶች ፣ ከግለሰቦች እና ከድርጅቶች ያገኝ ነበር ። አሁን ግን ሁሉም ነገር ቀርቷል። ከሁሉም በላይ ደግሞ ያሉት አባላት እንዲቆዩ የሄዱትም ዳግም ተሰባስበው ምርቶችን በስፋት ለማምረት ሁሉም በቻለው መጠን ድጋፍ ቢያደርግ የተሻለ ይሆናል።

በአሁኑ ወቅት በሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እንዲሁም በሌሎች መንግሥታዊ ተቋማት በኩል የተለያዩ በጎ ሥራዎች እየተሠሩ ነው። ሥራው የሚበረታታ ነው። ይሁን እንጂ ከዚህ ቀደም ሞዴል የነበሩ የበጎ አድራጎት ማኅበራት ዛሬ ላይ ፈተና ውስጥ መሆናቸውን ታሳቢ በማድረግ እነርሱን ማጠናከር ይገባል። ‹‹የጎደላቸው ነገር ምንድ ነው?›› ብሎ በመጠየቅ ከመንግሥት በኩል መረዳት እና የገበያ ትስስር መፍጠር ያስፈልጋል።

አቶ ዮሐንስ እንደሚያስረዱት፣ ችግሩን ለመፍታት በተቻለው መጠን የተለያዩ ባለሙያዎችን እንዲሁም በጎ ፈቃደኞችን በማሰባሰብ በእነርሱ ታግዞ የበለጠ ለመሥራት ታቅዷል። በተለይም ምርቶችን በማስተዋወቅ በኩል ብዙ መሥራት ይገባል። የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመገኘት ለመሥራት ታስቧል፡፡

አካል ጉዳተኞቹ በትምህርት ብዙም ያልገፉ በመሆናቸው ሥራ የማግኘት ዕድላቸው ጠባብ ነው። እንዲህ በሚሆንበት ወቅት ወደ ልመና ለመሄድ ይገደዳሉ። ከዚህ በተጨማሪም መንግሥት ድህነትን ለመቀነስ በሚያደርገው ጥረት ውስጥ አካል ጉዳተኞችን ማበረታታት ይኖርበታል። የተለያዩ ምርቶችን በማምረት ለሚተዳደሩ ማህበራትም ዘመኑን በሚመጥን መልኩ ወይም በቴክኖሎጂ የታገዘ አመራረት እንዲከተሉ ማገዝ ብሎም ድጋፍ ማድረግ ከመንግሥት የሚጠበቅ ኃላፊነት ነው።

# ዓለም አቀፍ

## ስሎቬኒያ ለፍልስጤም የሀገርነት እውቅና ሰጠች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ስሎቬኒያ ለፍልስጤም የሀገርነት እውቅና ሰጠች። ሶሎቬኒያ ለፍልስጤም የነጻ ሀገርነት እውቅና የሰጠችው የሀገሪቱ ፓርላማ ከትናንት በስቲያ የመንግሥቷን ውሳኔ ካጸደቀው በኋላ ነው ተብሏል።

ሶሎቬኒያ ለፍልስጤም የነጻ ሀገርነት እውቅና የሰጠችው የሀገሪቱ ፓርላማ ባለፈው ማክሰኞ እለት የመንግሥትን ውሳኔው ካጸደቀው በኋላ ነው ተብሏል።

የስሎቬኒያ መንግሥት ለፍልስጤም የነጻ እና ሉአላዊ ሀገርነት እውቅና የሰጠው፣ ስፔን፣ አየርላንድ እና ኖርዌይ እስራኤል በጋዛ እያካሄደች ያለውን ጦርነት እንድታቆም ይረዳል በሚል እውቅና መስጠታቸውን ተከትሎ ነው።

“ለፍልስጤም የሉአላዊ እና የነጻ ሀገርነት እውቅና መስጠታችን በዌስትባንክ እና በጋዛ ላለው የፍልስጤም ህዝብ ተስፋ የሚሰጥ ነው” ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ሮበርት ጎሎብ በማህበራዊ የትስስር ገጻቸው አስፍረዋል።

በጉዳዩ ላይ ድምጽ ለመስጠት በትናንትናው እለት ቀጠሮ ተይዞ የነበረ ሲሆን የውጭ ጉዳይ የሚመለከተው የፓርላማ ቡድን መንግሥት ያቀረበውን ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ አጽድቆታል።

ቀደም ሲል የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ጃኔዝ ጃንሳ የሆነው ቀኝ ዘመሙ ስሎቬኒያን ዲሞክራቲክ ፓርቲ(ኤስዲኤስ) የእውቅና መስጠቱ ጉዳይ ውይይት እንዲደረግበት ጥያቄ በማቅረቡ ድምጽ የመስጠቱ ሂደት ቢያንስ በአንድ ወር እንዲዘገይ ማድረጉን ሮይተርስ ዘግቧል።

በሀገሪቱ ትልቁ ተቃዋሚ ፓርቲ ኤስዲኤስ “ሽብርተኛ



ድርጅት የሆነውን ሀማስን” ስለሚያበረታታ ለፍልስጤም የነጻ ሀገርነት ለመስጠት አሁን ጊዜው አይደለም የሚል መከራከሪያ አቅርቦ ነበር።

90 አባላት ባሉት የስሎቬኒያ ገዥ ፓርቲ ምርጫው እንዲካሄድ በማድረግ የመንግሥት እውቅና የመስጠት ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ ጸድቋል።

እስራኤል የፍልስጤምን ነጻ ሀገርነት አትቀበልም፣ እውቅና የሚሰጧትን ሀገራትም በጽኑ ትቃወማለች።

የአረብ ሀገራትና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በመካከለኛው ምሥራቅ ሰላም ሊሰፍን የሚችለው ከእስራኤል ጎን የፍልስጤም ሀገር መቋቋምን የሚደግፈው የ “ቱ ስቴት ሶሉሽን” ሲተገበር ነው ይላሉ።

## የታጠቀ ግለሰብ በሊባኖስ በሚገኘው የአሜሪካ ኤምባሲ ተኩስ ከፈተ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በሊባኖስ በሚገኘው የአሜሪካ ኤምባሲ ላይ ዛሬ ጠዋት ጥቃት የማድረስ ሙከራ ተደርጓል።

የሶሪያ ዜግነት አለው የተባለ የታጠቀ ግለሰብ ከኤምባሲው እና ከሊባኖስ የጸጥታ ኃይሎች ጋር ለግማሽ ስአት ያህል የተኩስ ልውውጥ ማድረጉንም ነው የሊባኖስ ጦር ያስታወቀው።

የሊባኖስ ወታደሮች ጥቃት አድራሹ ግለሰብ ላይ ተኩሰው ጉዳት አድርሰውበት ወደ ሆስፒታል መወሰዱ ተገልጿል።

የአሜሪካ ኤምባሲ በበሩ ዙሪያ በተካሄደው የተኩስ ልውውጥ በሰራተኞቹ ላይ ጉዳት እንዳልደረሰ መግለጹን አሶሼትድ ፕረስ ዘግቧል።

ሬውተርስ በበኩሉ አንድ የኤምባሲው የደህንነት ቡድን አባል በጥቃቱ መቁሰሉን ምንጮቹን ጠቅሶ አስነብቧል።

የሊባኖስ ጦር በኤምባሲው ዙሪያ ወታደሮችን በማሰማራት ተጨማሪ ጥቃት አድራሾች ካሉ በቁጥጥር ስር ለማዋል አሰሳ እያደረገ መሆኑን ባወጣው መግለጫ ጠቁሟል።

ከቤሩት በስተደቡብ ኡካር በተባለ ስፍራ የሚገኘው የአሜሪካ ኤምባሲ በርካታ የፍተሻ ጣቢያዎች ያሉትና ደህንነቱ አስተማማኝ እንደነበር ሲነገርለት ቆይቷል።

ዋሽንግተን በቤሩት የሚገኘውን ኤምባሲዋን ወደ ኡካር ያዛወረችው በፈረንጆቹ 1983 በኤምባሲው በተፈጸመ የአጥፍቶ መጥፋት ጥቃት 63 ሰዎች መገደላቸውን ተከትሎ ነበር።




በ1984ም ወደ ኡካር በተዛወረው ኤምባሲ ላይ የቦምብ ጥቃት መፈጸሙን አሶሼትድ ፕረስ አስታውሷል።

ለ1983ቱ ጥቃት የሊባኖሱን ሄዝብላህ ተጠያቂ ያደረገችው ዋሽንግተን ከቅርብ ጊዜ ወዲህም በእስራኤልና ሃማስ ጦርነት ያላት ድርሻ በሊባኖሳውያን ተቃውሞ አስነስቶባታል።

የጋዛው ጦርነት እንደተጀመረ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሊባኖሳውያን በአሜሪካ ኤምባሲ ዙሪያ በመገኘት ተቃውሟቸውን ሲያሰሙ ከሊባኖስ የጸጥታ ኃይሎች ጋር መጋጨታቸው ይታወሳል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

# ሐሙስ ስፖርት

ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ትኩረት የሚሻው የአሰላ አረንጓዴ ስታድየም የመሮጫ መም

ዓስማየሁ ግዛው

በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት አስተዳደር ውስጥ ከሚገኙና የመሮጫ መምን (ትራክን) አካተው ከተገነቡ ስታዲየሞች መካከል የአሰላ አረንጓዴ ስታድየም አንዱ ነው። ስታድየሙ ከተገነባ 20 ዓመት ሲሆነው፤ የመሮጫ መሙ (ትራኩ) ደግሞ ከ13 ዓመታት በላይ ማስቆጠሩን መረጃዎች ያመለክታሉ። የመሮጫ መሙ ከእድሜ እና ከአገልግሎት ብዛት ጋር ተያይዞ ከጥቅም ውጪ ወደሚሆንበት መንገድ ላይ ቢሆንም ለእድሳቱ ተገቢው ትኩረት እንዳልተሰጠው የአሰላ ከተማ ወጣቶችና ስፖርት ጽህፈት ቤት አስታውቋል፡፡

ስታድየሙን በበላይነት የሚያስተዳድረው ጽህፈት ቤቱ በአገልግሎት ብዛት የተጎዳውን የመሮጫ መም፣ ከቡር ትሪቡን እና አጥሩን አድሶ ለማጠናቀቅ እየሰራ መሆኑንም ገልጿል። የመሮጫ መሙ በየወቅቱ የሚካሄዱትን የክልል እና ሀገር አቀፍ የአትሌቲክስ ውድድሮችን እንዲሁም ልምምዶችን የሚያስተናግድ በመሆኑ፣ በሚደርስበት ጫና ምክንያት ከጥቅም ውጪ ወደ መሆን እየሄደ ይገኛል። ስፍራው በርካታ አትሌቶች የሚፈሩበት በመሆኑ ለልምምድ በርካቶችን ሲያስተናግድ ከተለያዩ የክልሉና የሀገሪቱ ክፍሎች የሚመጡ አትሌቶች፣ ፕሮጀክቶች እና ክለቦችም ይጠቀሙበታል። በዚሁ የአገልግሎት ብዛትና ከእድሜ ጋር የተያያዙ ጫናዎች ቢኖሩም እስከ አሁን ድረስ እድሳት አልተደረገለትም፡፡

የከተማው ወጣቶችና ስፖርት ጽህፈት ቤት የተጎዳውን የመሮጫ መም (ትራክ) ለማደስ፣ ከክልሉ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ እንዲሁም ከኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጋር ንግግሮችን ቢያደርግም በሚፈለገው ልክ ምላሽ አለማግኘቱን አስታውቋል። ታድሶ የተለመደውን አገልግሎት እንዲቀጥል የህዝብና መንግሥትን አፋጣኝ እገዛ እንደሚያስፈልግም ጠቁሟል። በርካቶች ውጤታማ የሆኑበትና ለተተኪ አትሌቶች መፈጠርም ምክንያት የሆነውን የመሮጫ መም እድሳት እገዛ እንዲያደርጉ ለአትሌቶችም ጥሪ የቀረበ ሲሆን፤ የተሰጠ ምላሽ ግን የለም። መሙ ትኩረት እንዲያገኝ በተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን ሽፋን ተሰጥቶት ቢዘገብም ምላሹ ግን ተመሳሳይ ነው፡፡

የአሰላ ከተማ ወጣቶችና ስፖርት ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ በዶ ዳባ፤ የስታድየሙ የመሮጫ መም ብዙ ጫናዎችን እያስተናገደ ያለ እድሳት በጽሕፈት ቤቱ ጥበቃና እንክብካቤ እስከ አሁን መቆየቱን ይገልጻሉ። ዓመታትን አስቆጥሮ እድሳት ያልተደረገለት ብቸኛ ስታድየም በመሆኑ በፍጥነት ጥገና ሊደረግለት ይገባል። ለክልሉ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮና እና ጉዳዩ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የሚመለከታቸውን አካላት እንዲሁም ከስፍራው የወጡ አትሌቶች ለእድሳቱ እገዛ የተጠየቁ ቢሆንም ምላሽ የሰጠ አካል አልተገኘም፡፡

ስታድየሙን ለማደስ በሚደረገው ጥረት ውስጥ የክልሉ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ፣ ባለሙያዎችን መድቦ የእድሳቱን ዋጋ አስጠንቶ ያጠናቀቀ ሲሆን፤ በአሁኑ የገበያ ዋጋ 18 ሚሊዮን ብር ተገምቷል። ይህንንም የኢትዮጵያ



**የአረንጋዴውን ስታድየም የመሮጫ መም ለማሳደስ 18 ሚሊዮን ብር እንደሚያስፈልግ ተጠቁሟል፤**

አትሌቲክስ ፌዴሬሽንን እና የክልሉን ወጣቶችና ስፖርት ቢሮን በደብዳቤ በመጠየቅ የፌዴሬሽኑ ፕሬዚዳንት እና የቢሮ ኃላፊው መሙ ያለበትን ደረጃ መመልከታቸውን ጠቁመዋል። ሁሉም ስታድየሙንና መሙን (ትራኩን) ለማደስ ቃል ገብተው የነበረ ቢሆንም አሁንም ድረስ ተግባራዊ ማድረግ አልተቻለም። የክልሉ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ግን የስታድየሙን እና የመሙን እድሳት ለማከናወን ባስጠናው የዋጋ ተመን መሰረት ለ2017 ዓ.ም እቅድ ይዞ እየሰራ መሆኑን አቶ በዶ ጠቁመዋል።

የከተማው ወጣቶችና ስፖርት ጽህፈት ቤት በበኩሉ፤ የስታድየሙን የዙሪያ አጥር ከባዛር በተሰበሰበ ገቢ አማካኝነት፣ ዘላቂ የገቢ ምንጭ ሊሆን በሚችልበት ሁኔታ ሱቆችና የተለያዩ አገልግሎቶችን መስጠት እንዲችል ተደርጎ እያሰራ ይገኛል። በዚህም መሰረት ፕሮጀክቱን በሶስት ወራት ለማጠናቀቅ ከተቋራጭ ጋር ውል የተገባ ሲሆን፣ 10 ሚሊዮን ብር በጀት ተመድቦ እየተሰራም ነው። የስታድየሙ እድሳት በሁለት ምዕራፍ የሚከናወንና ከአጥር እንዲሁም ከመሮጫ መም ውጪ የክቡር ትሪቡን ወንበሮች እድሳት ይገኝበታል።

አንገብጋቢውና ቅድሚያ ትኩረት ተሰጥቶ መታደስ የሚገባው የመሮጫ መም ግን በፍጥነት ታድሶ ወደ አገልግሎት መግባት እንደሚኖርበት ጽህፈት ቤት ኃላፊው አክለዋል። ለዚህም የከተማው ወጣቶችና ስፖርት ጽህፈት ቤት ከክልሉ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮና ከኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጋር በትብብር የሚሰሩ ከሆነ በፍጥነት ታድሶ የተለመደውን አገልግሎት መስጠት ይችላል። ጽህፈት ቤቱም የሚጠበቅበትን ለማድረግ ዝግጁ በመሆኑ ሌሎች ባለድርሻዎችም የበኩላቸውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። የክልል ሀብት የሀገርም ሀብት በመሆኑ እድሳትና እንክብካቤው በአፋጣኝ መፍትሔ ማግኘት እንደሚኖርበትም አሳስበዋል፡፡

በስታድየሙ አስተዳደር ስር የሚሰሩ የተወሰኑ የሜዳ ተንከባካቢዎች ያሉ ሲሆን፤ እድሳት ከተደረገለት በኋላ እንክብካቤውን እና ጥበቃውን አጠናክረው እንደሚሰሩም ኃላፊው ጠቁመዋል፡፡

## ከአዲስ አበባ ከተማ ፕላንና ልማት ኮሚሽን ጋር በመተባበር በየወሩ የሚታተም

# ፕላንና የፕላን ተዋረዶች

ባለፈው እትማችን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን እንደገና ለማቋቋም ባወጣው አዋጅ ቁጥር 84/2016 መሰረት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፕላንና ልማት ቢሮ 20(ሃያ) የተናጠል ስልጣንና ተግባር እንደተሰጡት በመጥቀስ፤ ሃያውን ዘርዝሩን ማስነበባችን የሚታወስ ነው።

በአሁኑ እትማችን ደግሞ ስለ ፕላን እና የፕላን ተዋረዶች ምንነት እናቀርባለን። በዚህ ጽሑፋችን ፕላን ምን ማለት እንደሆነ ከመግለጻችን በተጨማሪ ስለ ፕላን ተዋረዶችም እያነሳን ምንነታቸውን እናቀርባለን። የፕላን ተዋረዶች የሚባሉት ገጸ ምድራዊ ፕላን፣ መዋቅራዊ ፕላን፣ የአካባቢ ልማት ፕላን፣ የሰፈር ንድፍ ፕላን፣ የከተማ ንድፍ ፕላን እና ማጠቃለያ ሰነድ የሚባሉ ናቸው። እነሱም ከዚህ እንደሚከተለው ምንነታቸው ቀርቧል። መልካም ንባብ!

**ፕላን፡-** ማለት መዋቅራዊ ፕላንና የአካባቢ ልማት ፕላን እንዲሁም በህግ የተደነገጉ ሌሎች ፕላኖችን ያጠቃልላል።

**ገፀ-ምድራዊ ፕላን**፡- ማለት በመሬት ላይ፣ በመሬት ውስጥ እና ከመሬት በላይ ጊዜን ፣ ጉልበትን ፣ ዕውቀትን ፣ ክህሎትን ፣ ገንዘብን እንዲሁም ቁሳቁሳዊ ሀብቶችን በቁጠባ፣ በተሳለጠ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ በመጠቀም ልማትን ለማካሄድ እንዲቻል በሁለት እና/ወይም በሶስት ጎንዮሽ መለኪያ በስዕልና በጽሑፍ የሚዘጋጅ መሬት ልማት ተኮር ፕላን ሲሆን፤ መዋቅራዊ ፕላንን፣ የአካባቢ ልማት ፕላንን፣ የመሰረተ ልማት ቅንጅት ፕላንን፣ የውስጥ ለውስጥ መንገድ ፕላን/ ዲዛይንን እና የመሳሰሉትን ያካትታል፡፡

**መዋቅራዊ ፕላን**፡-ማለት በማህበራዊ፣ በምጣኔ ሀብታዊ እና በአካባቢያዊ ዘርፎች የተመጣጠነ የከተማ ልማት ለማስገኘት በሚያስችል መልኩ የከተማን ፊዚካላዊ ዕድገት እና ልማት በተመለከተ መሟላት የሚገባቸው ጉዳዮችን የሚዘረዝር እና ህጋዊ ተፈጻሚነት ያለው አብይ የከተማ ፕላን ነው፡፡

**የአካባቢ ልማት ፕላን**፡- ማለት በስልታዊ ባህሪያቸው ምክንያት በተመረጡ አካባቢዎች ላይ በማተኮር የከተማውን አንድ አካባቢ ለማሻሻል፣ ለማደስና ለማስፋፋት በመካከለኛ የዕቅድ ዘመን በጊዜ እየተከፋፈሉና እየተቀናጁ የሚከናወኑ የልማት ሥራዎችን የሚያሳይና መዋቅራዊ ፕላኑን በተመረጡ አካባቢዎች ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ የልማት ግቦችን፣ አበይት ተግባራትን፣ የአፈጻጸም ስልቶችን፣ የፈጻሚ አካላትን ሚና እና ተፈላጊ ተቋሞችን፣ የአካባቢ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴን፣ የከተማ ዲዛይን መርሆዎችን፣ ተጨባጭ መስፈርቶችን፣ የአካባቢ ማዕቀፍን፣ በጀትን እና ጊዜን በዝርዝር የሚያሳይ ህጋዊ ተፈጻሚነት ያለው እንዲሁም መዋቅራዊ ፕላኑ ተግባራዊ የሚደረግበት ፕላን ነው፡፡

የሰፈር ንድፍ ፕላን # ማለት በአንድ አካባቢ ወይም ሰፈር የመኖሪያ ስብስብ ውስጥ መሰረታዊ አገልግሎቶችን በማካተት ከአካባቢ ልማት ፕላን ቀጥሎ የሚመጣ በፕሮጀክት ደረጃ የሚዘጋጅ ፕላን ነው፡፡

**የከተማ ንድፍ ፕላን**፡- ማለት መዋቅራዊ ፕላን ወይም የአካባቢ ልማት ፕላን ወይም አካባቢ መሰረት በማድረግ መሬት አጠቃቀምን ሳይቀር ፕላንን ወደ መሬት ለማውረድ የሚያስችል ዝርዝር የህንጻ ግንባታ የሚያርፍበትን ቦታ ነው። በአካባቢው የሚገነቡ ግንባታዎች የሚኖራቸውን መስተጋብር እና የፊት ለፊት ገጽታ ወስኖ የሚያስቀምጥ፣ መሰረተ ልማት መስፈርቶችን የማከፋፈያ ቦታዎችን የሚያመለክትና የሚያስፈልገውን የአገልግሎት መጠን ጨምሮ መግለጽ የሚችል ሲሆን፤ የቦታ ስፋቱ በአንድ የአካባቢ ልማት ፕላን የተዘጋጀ የቦታ ስፋትን የሚያጠቃልል ወይም እንደአስፈላጊነቱ ባነሰ የቦታ መጠን ሊዘጋጅ የሚችል ፕላን ነው፡፡

**ማጠቃለያ ሰነድ**፡-ማለት የመዋቅራዊ ፕላኑን የጥናት ውጤቶችና ልዩ ልዩ ክፍሎችን እንዲሁም የፕላኑን የመሬት አጠቃቀም አመዳደብ መፍቻ የያዘ የፕላን ማጠቃለያ መድብል ነው፡፡